# ኅብረተሰብ ሳይንስ

# 5ኛ ክፍል

# የመምህር መምሪያ

አዘጋጅ፡-
ብርሃኑ ለሜሶ

አርታኢ፡-
ወንድማገኝ ገብረሕይወት

ገምጋሚዎች፡-
ዘላለም አላጋው
ዘሪሁን ጌታቸው
ይታገሱ አጥናፉ

AL GHURAIR
PRINTING AND PUBLISHING LLC

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

## ምስጋና

የዚህ መጽሐፍ ዲዛይን ህትመትና ስርጭት ማከናወኛ ገንዘብ የተገኘው በአጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ኘሮጀክት (GEQIP) አማካኝነት ነው:: የሮጀክቱ ዋና ዓላማ በአገሪቱ በሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ከ1ኛ-12ኛ ክፍሎች የሚሰጠውን የትምህርት ጥራት ማሻሻል ነው::

የኢትዮጵያ ፌዲራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ለGEQIP የዋለውን ገንዘብ ያገኘው በብድር/በእርዳታ ሲሆን ብድሩን/ እርዳታውን የሰጡት ዓለምአቀፍ የልማት ማህበራት (IDA)፣ ፋስት ትራክ ኢንሼትብ ካታሊቲክ ፈንድ (FTI CF) እና ሌሎችም የልማት አጋሮች ማለት የፊንላንድ፣ የኢጣሊያ የልማት ማህበር፣ የኔዘርላንድና የታላቋ ብሪታኒያ የእርዳታ ድርጅት አለምአቀፍ የልማት ዋና ክፍል (DFID) ናቸው::

ሁሉንም በዝርዝር መጥቀስ የማይቻል በርካታ ግለሰቦችና ድርጅቶች ይህ የመምህር መምሪያና የተማሪ መጽሀፍ እውን እንዲሆኑ ያልተቆጠበ ድጋፍቸውን ሰጥተዋል:: በዚህም ትምህርት ሚኒስቴር ምስጋናውን ያቀርባል::

© በኢትዮጵያ ፌዲራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር

1ኛ እትም፣ 2004 ዓ.ም

ISBN 978-99944-2-083-4

**የአል-ጉሬር አታሚና አሳታሚ ድርጅት**
**የፖ.ሳ.ቁጥር 5613**
**ዱባይ፣**
**የተባበሩት የአረብ ኤሚሬት**

**ከኩራዝ ኢንተርናሽናል አሳታሚ ኃ/የተ/የግ/ማህበር**
**የፖ.ሳ.ቁጥር 100767**
**አዲስ አበባ**
**ኢትዮጵያ**

ጋር በመተባበር ይህን መጽሐፍ ለኢፌዴሪ የትምህርት ሚኒስቴር አዘጋጅተው አትመው፣ አሰራጭተዋል::

ሁሉም የህትመት መብቶች ተከብረዋል::
የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም እንደማይቻል የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዲራል ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 410/2004 የኮፒራይትና የተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ 10ኛ አመት ቁጥር 55 አዲስ አበባ ጁላይ 19, 2004 ይከለክላል::

የስዕሎችን የኮፒ ራይት መብቶች ለማክበር በተቻለን መጠን የሚፈለግብንን ጥረት ሁሉ አድርገናል:: ሳናውቅ በስህተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥሉት ህትመቶች አስፈላጊውን እውቅና እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን::

# መቅድም

ትምህርት እና ልማት እጅግ የተቆራኙና አስፈላጊ ነገሮች ናቸው:: ለዚህም ነው ትምህርት በኢትዮጵያ ልማት ውሰጥ ዋንኛውና ቁልፍ መሳሪያ ነው ተብሎ የሚነገረው:: በዚህ ፈጣን ዓለም አቀፋዊነት በሚታይባት ዓለማችን ውስጥ ለመኖር አዲስ እውቀት፣ ክህሎት፣ አመለካከቶች እና እሴቶችን እያንዳንዱ ሰው ማዳበር ይጠበቅበታል:: እንግዲህ በዚህ ዓላማ መሰረት ነው የአንድ ሃገር የትምህርት ሂደት ነፀብራቅ የሆነው ስርዓተ ትምህርት ለለውጥ ምላሽ በሚሰጥ መልኩ መቀረፅ ያለበት::

ሃገራችን ኢትዮጵያ አዲስ የትምህርት እና ስልጠና ፖሊሲ አዘጋጅታ መተግበር ከጀመረች ከአስራ አምስት አመታት በላይ ሆኗታል:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ ተደራሽ፣ ፍትሃዊ እና ተገቢነት ያለው እመርታ በትምህርቱ መስክ  አስመዝግባለች:: የትምህርትንም ጥራት ለማሻሻል ከፍተኛ ጥረት ሲደረግ  የቆየ ሲሆን ጥረቱ ወደፊትም ይቀጥላል::

ይህን ሂደት ለመቀጠልም የትምህርት ሚኒስቴር የስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ማዕቀፍ አዘጋጅቷል:: ማዕቀፉም ሁሉንም  የትምህርት ደረጃ፤ የአፀደ ህፃናት፣ የመጀመሪያ ደረጃ፣ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ እና የመሰናዶ ክፍሎች ትምህርቶችን ያጠቃልላል:: የማዕቀፉም አላማዎች  የሚያተኩሩት በትምህርት እና ስልጠና ፖሊሲዎች ላይ ያሉትን መሰረታዊ ሐሳቦችና መርሆዎች ለማጠናከር፤ እንዲሁም ወደፊት ለሚዘጋጁት፣ የስርዓተ ትምህርት መጻሕፍት፣ ለዚህ የመምህር መምሪያና ለተማሪ መጽሀፍት አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴንና የመማር ብቃት አቀራረብን ያቀፉ ሆነው እንዲዘጋጁ ማስቻል ነው::

አዲስ ማዕቀፍ ማዘጋጀት እንዲሁም፣ የተከለሱና የተሻሻሉ የመምህር መምሪያና የተማሪ መጻሕፍት ማዘጋጀት የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል በየትኛውም ሀገር ቢሆን ብቸኛ መፍትሔ አይደሉም:: ነገር ግን ቀጣይነት ያለው ማሻሻያ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ይጠበቃል:: የመምህራን ሚናም ከገለፃ ሰጭነት  እስከ አነቃቂነት፣ መሪነት እና አመቻችነት ዘላቂ እንዲሆን  ያስፈልጋል:: ይህንንም ለማገዝ በማዕቀፉ ላይ እና በመምህር መምሪያው ላይ የተቀመጡትን ማስተማሪያ ዘዴዎች በተመለከተ መምህራን ስልጠና የተሰጣቸው ሲሆን ወደፊትም ስልጠናው መሰጠቱ ይቀጥላል::

መምህራን ይህን መምሪያ በጥንቃቄ እንዲያነቡ እና የተቀመጡትን የማስተማሪያ ዘዴዎች በመተግበር ተማሪዎቻቸውን መደገፍ ይጠበቅባቸዋል::

በተማሪ መጽሐፍ በየምዕራፉ መጨረሻ ለተቀመጡት የማጠቃለያ ጥያቄዎች መልሶቻቸው በመምህር በመምሪያ ውስጥ የተቀመጡ ቢሆንም፣ ይህ ተማሪዎችን አማራጭ መልሶችን ከመፈለግ ሊያግዳቸው አይገባም:: ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት መጽሐፋቸውን አንብበው አማራጭ መልሶችን እንዲያገኙ ማስቻልም ይጠበቃል::

# ማውጫ


ገፅ

መግቢያ ........................................................................................ i

**ምዕራፍ አንድ፡- የኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት መገኛና የሕዝቦች አሠፋፈር**

1.1 የአፍሪካ ቀንድ ሀገራትና መገኛቸው .......................................... 2

1.2 የኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ሕዝቦች ታሪክና አሰፋፈር .... 4

1.3 አንድነትና ዘመናዊነት ....................................................................8

1.4 የሕዝብ አሰፋፈርና የባህል ልዩነት እንዲፈጠር ጉልህ ሚና ያላቸው ምክንያቶች ..................................................................11

**የምዕራፍ አንድ የክለሳ ጥያቄዎች መልስ ..............................................14**

**ምዕራፍ ሁለት፡- መሬትና አካባቢዋ**

2.1 መገኛችን ........................................................................... 16

2.2 የመሬት ቅርጽ፣ እንቅስቃሴዋና እና የእንቅስቃሴዋ ውጤቶቹ .......19

2.3 የወቅቶች መፈራረቅ በእርሻና በከብት እርባታ ላይ ያለው ተፅዕኖ ....................................................................22

**የምዕራፍ ሁለት የክለሳ ጥያቄዎች መልስ ..............................................25**

**ምዕራፍ ሦስት፡- አካባቢያችን**

3.1 ዋና ዋና የእፅዋት ዓይነቶችና የዱር እንስሳት ............................ 27

3.2 የዱር እንስሳትና እፅዋት የሚሰጡት ጥቅም ................................ 31

3.3 ከኢኮኖሚ እድገት ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር እፅዋት ላይ የሚያመጣው አሉታዊ ተጽእኖ.................34

3.4 የተፈጥሮ እፅዋትና የዱር እንስሳት እንክብካቤ .............................37

**የምዕራፍ ሦስት የክለሳ ጥያቄዎች መልስ ........................................... 41**

**ምዕራፍ ኣርባዕተ፡- ሕዝባዊ ጉዳዮች**

**4.1** ሕዝብ ነክ ጉዳዮች ........................................................................ 42

**4.2** ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገትና አሉታዊ ተፅዕኖዎቹ ......................46

**4.3** መልካም አስተዳደር፣ የሕፃናት መብትና ደኅንነት ...................... 49

**የምዕራፍ አራት የክለሳ ጥያቄዎች መልስ** ............................................. **54**

**ዋቢ መጻሕፍት** ...........................................................................**56**

**አጥጋቢ የመማር ብቃት** ..................................................................... **57**

**መርሃ ትምህርት** ...........................................................................**61**

# መግቢያ

የመምህር መምሪያ የትምህርት ርዕሶችንና ከእነዚሁ ጋር ተጎዳኝተው የሚሄዱትን የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶችን፣ የክፍለ ጊዜ ሥርጭትን፣ የትምህርት አቀራረብ ዘዴዎችንና የተከታታይ ምዘና ስልቶችን ያካተተ በመሆኑ ለመምህር በጣም ጠቃሚ መሣሪያ ነው፡፡ መምህር ከተመደበው ጊዜ ጋር አገናዝቦ ለሚያዘጋጀው የትምህርት እቅድ ተሟልቶ የቀረበ የጽሑፍ ማስረጃ ነው ማለትም ይቻላል፡፡

ስለዚህ የ5ኛ ክፍል የኅብረተሰብ ሳይንስ መምህር መምሪያ አራት ምዕራፎችን ያካትታል፡፡ እያንዳንዱ ምዕራፍ በንዑሳን ምዕራፎች የተከፋፈለ ነው፡፡ እያንዳንዱ ንዑስ ምዕራፍ ደግሞ ለማስተማሩ ሥራ ምቹ የሆኑ የትምህርት ርዕሶች አሉት፡፡ እያንዳንዱ ንዑስ ምዕራፍ ደግሞ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች፣ ዝርዝር ይዘቶች፣ የትምህርቱ አጭር መግለጫዎች፣ ለትምህርቱ አቀራረብ የሚጠቅሙ ዘዴዎች፣ የማስተማሪያ መሣሪያዎች፣ የትምህርቱ ቅድመ ዝግጅቶች አቀራረብና የምዘና ስልቶች ያጠቃለለ ነው፡፡ ከእነዚህ ዝርዝር መረጃዎች አኳያ የትምህርቱ አሰጣጥ ተማሪ ተኮር ስለመሆኑ መምህራን ሊገነዘቡ ይገባል፡፡ ስለዚህ የእርስዎ ዋነኛ ተግባር ለተማሪዎች መመሪያ መስጠት፣ አሠራሩን ማሳየትና ያላሰለሰ ክትትል ማድረግ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የተማሪው ተግባር "እየሠሩ መማር" ከሚለው መርህ አንፃር በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ ነው፡፡ የምዘና ስልቶችም እየሠሩ መማር የሚለውን መርህ ከሚያካትቱት አሳታፊ ዘዴዎች ጋር የተገናዘቡ ናቸው፡፡

መምህር በማስተማር ሥራ ላይ ተሠማርተው እንደተገነዘቡት ሁሉ የመማር ማስተማር ዘዴዎች ተለዋዋጭ ናቸው፡፡ የተመረጠው የትምህርት ርዕስ በዚህ መመሪያ ውስጥ ከተጠቆሙት የመማር ማስተማር ዘዴዎች በአንዱ፣ በሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑት

ሊቀርብ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ የሚጠቀሙበት የመማር ማስተማር ዘዴ ወይም ዘዴዎች አሳታፊ የትምህርት አቀራረብ ስልትን የማያጎለብቱ መሆናቸውን በአግባቡ መገንዘብ ይገባዎታል፡፡ የምዘና ስልቶቹም በእነዚሁ ዘዴዎች ላይ የተመሠረቱ መሆን አለባቸው፡፡ አሳታፊ ዘዴዎችን ለምን እንጠቀማለን? ምክንያቱም እነዚህ ዘዴዎች በየንዑስ ርዕሱ መጨረሻ በተማሪው/ዋ ላይ እንዲያመጣ የተተለመውን የባህርይ ለውጥ የሚያጎለብቱ በመሆናቸው ነው፡፡

ከላይ ከቀረበው ዝርዝር ሃሳብ አነፃር የኅብረተሰብ ሳይንስን በመጀመሪያ ደረጃ በምን እንደምናስተምር የሚገልጹትን ጠቅላላ ዓላማዎችና አጥጋቢ የመማር ብቃቶች ማወቅ ይኖርቦታል፡፡ ከዚህም በላይ በ5ኛ ክፍል ኅብረተሰብ ሳይንስን በማስተማር መገኘት ያለበትን ውጤት፣ የተከታታይ ምዘናንና በየርዕሱ ማጠቃለያ ላይ መሰጠት ያለበትን ሙከራ(ቴስት) ትርጉም መገንዘብ አለብዎት፡፡

**የኅብረተሰብ ሳይንስ አጠቀላይ ዓላማዎች**

የኅብረተሰብ ሳይንስ ትምህርት በኢትዮጵያ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሁለተኛው እርከን ከሚሰጡት የትምህርት ዓይነቶች አንዱ ነው፡፡

- የኅብረተሰብ ሳይንስ ተማሪዎች ስለአገራቸው፣ ስለአካባቢያቸው ከዚያም አልፎ ስለ ዓለም ምጣኔ ሀብት፣ ፓለቲካዊና ሕጋዊ ሥራዓቶችና ተቋማት እንዲያውቁ ያደርጋል፡፡
- ተማሪዎች ኃላፊነት ተሰምቷቸው በማኅበረሰብ ሕይወት ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ እኩልነትን፣ ፍትህን እንዲያከብሩ፣ መቻቻልንና አርበኝነትን እንዲያጎለብቱ፣ ለአገራቸው ታማኝ ሆነው የአገር ፍቅር ስሜት እንዲኖራቸው የአመለካከት ባህርይ ለውጥን ያዳብራል፡፡
- ተማሪዎች የአፍሪካ ቀንድንና የምሥራቅ አፍሪካን ጥንታዊ መንግሥታትን፣ የተፈጥሮ ሀብቶች አያያዝንና የዘመናዊነት ዕድገትን እንዲያውቁና እንዲረዱ ያደርጋል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

የመማር ማስተማር ዘዴዎች መምህር የሚያስተምሩትን ትምህርት ወደ ተማሪዎች ለማስተላላፍ ወይም ተማሪዎች በመሳተፍ እንዲማሩ የሚደረጉባቸው ዘዴዎች ናቸው፡፡ በመሠረቱ የመማር ማስተማር ዘዴዎች መምህራን የሚያቀርቡትን ትምህርት ከሚያዘጋጁበት፣ የትምህርቱን ግቦች ለመምታት ከሚጠቀሙባቸው ስልቶች ወይም ክህሎት፣ የትምህርት ዓይነት፣ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ወይም ከማንኛውም የትምህርቱን ግብ ሊያንፀባርቁ ከሚችሉ አግባብ ካላቸው ጠቃሚ ነገሮች ጋር የተቆራኙ ናቸው፡፡ ዘዴዎች ለማስተማር የሚያስፈልጉ አጠቃላይ ዓላማዎችንና ግቦችን፣ የትምህርት ርዕስ መረጣን፣ ግቦችን ለማስፈጸም የሚረዱ የትምህርት ርዕሶችንና የተግባር ቅደም ተከተሎችን፣ የመማር ተግባር ስኬትን፣ የስኬቱ ግብ መምታትን ወይም አለመምታትን መገምገምን ያጠቃልላሉ፡፡

## የማስተማር መማር ዘዴዎች ጠንካራና ደካማ ጎኖች መግለጫ ሠንጠረዥ

| ዘዴ | ጠንካራ ጎን | ደካማ ጎን |
|---|---|---|
| ጥያቄና መልስ (Question & Answer) | - የሚከተሉትን የሚያጠቃልሉ ልዩ ልዩ ዓይነት ጥያቄዎች ለመጠቀም ይረዳል። እነሱም፡-<br>• ጠቅላላ ጥያቄዎች(general questions)<br>• ከተለያዩ አማራጭ መልሶች አሰጣጥ ጋር የተጎዳኙ ጥያቄዎች(Divergent questions)<br>• ከማነፃጸር ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች(Probing questions)<br>• ከምክንያታዊነት ጋር የተገናዘቡ ጥያቄዎች<br>- ጥያቄዎቹ ትምህርት ከመጀመሩ በፊትና ትምህርቱ ቀርቦ ከተገባደደ በኋላ በአግባቡ ጥቅም ላይ ይውላሉ። | - መምህራን ከበቂ በላይ በጥያቄዎች መጠቀም መቻላቸው<br>- በእውቀት፣ በግንዛቤና በመሳሰሉት ላይ የሚመሠረቱት ጥያቄዎች ውስን አለመሆናቸው<br>- ጥያቄዎቹን መመለስ የሚያቅታቸው ተማሪዎች ቅር መሰኘት ወይም መሸማቀቅ |
| ገለፃ (explanation) | - የትምህርት ርዕሱን የሚገልጹ በቂ ቃላት መጠቀም ያስችላል።<br>- ተማሪዎች ትኩረት በተሰጠው የትምህርት ርዕስ ላይ አስፈላጊውን መረጃ ማግኘት ይችላሉ። | - ሁልጊዜ ተማሪዎች ከመምህር መረጃ እንዲጠብቁ ማድረጉ<br>- ተማሪዎች በአብዛኛው አዳማጮች እንዲሆኑ ማድረጉ። |
| ውይይት (discussion) | - የሀሳብ ልውውጥ እንዲኖር ያደርጋል።<br>- እያንዳንዱ ተማሪ በንቃት እንዲሳተፍ እድል ይሰጣል<br>- ተማሪዎች የማገናዘብና ምክንያታዊ የመሆን አቅም እንዲኖራቸው ያደርጋል።<br>- ማስተማር የሁለትዮሽ ግንኙት መሆኑን ያረጋግጣል | - ደካማ ተማሪዎች ላይ ትኩረት አለማድረጉ<br>- በጣም ጥቂት ፈጣን ተማሪዎች ውይይቱን መቆጣጠራቸው<br>- ደከም ያሉት ተማሪዎች |

| ዘዴ | ጠንካራ ጎን | ደካማ ጎን |
|---|---|---|
| | | በመምህር ካልተጎተጎቱ በስተቀር መዳከማቸውና መፍዘዛቸው |
| ምልከታ (demonstration) | - የሚቀርበው ትምህርት ተጨባጭ እንዲሆን ይረዳል<br>- የተመረጠና ለእይታ የሚበቃ መረጃ ላይ በመመሥረት የትምህርቱን ርዕስ በቀላሉ ለማቅረብ ያስችላል፡፡ | - የትምህርቱ ርዕስ የሚያጠቃልላቸውን በሙሉ አለማካተቱ<br>- ተማሪዎች ለእይታ በቀረበው ማቴሪያል ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ ማድረጉ |
| እውነትን ፈልጎ የማግኝት ዘዴ (Inquiry teaching learning method) | - በመማር ማስተማሩ ወስጥ ተዋናይ የሆኑትን ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ እንዲሳተፉ ያደርጋል<br>- እንደ ሳይንሳዊ ዘዴ ግትር ባይሆንም በስልት መልስ ለማግኘት ጥረት የሚያደርግ ዘዴ ነው፡፡ ይኸውም ተማሪዎች ለጥያቄዎች ወዲያውኑ መልስ ከመስጠት ይልቅ ሌሎች ጥያቄዎች በማንሳት የበለጠ እንዲመራመሩ ያደርጋል፡፡ ተማሪዎች ወድያውኑ እውነት ነው ብለው ከሚያረጋግጡ ይልቅ እውነትን ፈልገው ማግኘቱ ላይ እንዲያተኩሩ መንገድ ይከፍታል፡፡<br>- ተማሪዎችን ችግርን ለመፍታት የተለያዩና በርካታ አማራጮችን እንዲጠቀሙ ነፃ ያደርጋቸዋል፡፡<br>- ተማሪዎች ከፍተኛ የውስጥ መነሳሳት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ ትምህርትን እየተደሰቱና እየጓጉ እነዲቀስሙ በር ይከፈታል፡፡ | - ተማሪዎችን ከእውነታው ጋር ለማገናኘት ያለው ብቃት አዝጋሚ መሆኑ<br>- በተወሰነ ጊዜ ሊሸፈን የተያዘ የትምህርት ርዕስ እንዳይሸፈን ማንተቱ<br>- ዘዴው ለየት ያለ እውቀት መጠየቁ፣ ይኸውም የመመራመር የመተንተን፣ የማጠቃለልና የመዘገብ ክህሎት እንዲኖር መፈለጉ:: |

| ዘዴ | ጠንካራ ጎን | ደካማ ጎን |
|---|---|---|
| ችግር ፈቺ የማስተማር ዘዴ (Discovery teaching method) | - ከፍተኛ የተማሪዎች ተሳትፎ ይታይበታል<br>- ሰፊ ጽንሰ ሃሳቦችንና መርሆችን ለመገንዘብ ከማበረታታቱም በላይ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር አብሮ የመሥራት ችሎታን ያጎለብታል፡፡<br>- ችግር ፈቺ የማስተማር ዘዴ የመምህሩን ድጋፍ የሚፈልግ ሲሆን ተማሪዎች አብሮ የመሥራትና ችግር የመፍታት ዘዴን እንዲለማመዱ ያደርጋል | - ሰፊ የትምህርት ርዕስ ለመሸፈን ያለው ብቃት ደካማ መሆኑ<br>- የመወዳደር ስሜትን ስለሚቀንስ ተማሪዎች ፍዝ እንዲሆኑ ማድረጉ<br>- አብሮ ከመሥራት ባሻገር በተማሪዎች መካከል የውድድር ወይም የመፎካከር ስሜት አለመፍጠሩ |
| የቡድን ኘሮጀክት ዘዴ(የመተባበርና የመፎካከር የማስተማር ዘዴ) (Group project method) | - ለቡድን ሥራ መነሳሳትንና መሳተፍን ያበረታታል ወይም ሁኔታዎችን ያመቻቻል<br>- በተማሪዎች መካከል የመደጋገፍ መንፈስን ያጠናክራል<br>- ተማሪዎች የሥራቸውን የመጨረሻ ውጤት ለማወቅ የበለጠ ጥረት እንዲያደርጉ ያበረታታል፡፡ | - ጊዜ መፍጀቱ<br>- የገንዘብ ወጪ መጠየቁ<br>- እጅግ አስተማማኝ የክፍል አመራር ከሌለ በርካታ የሥነ ምግባር ጉድለት መፍጠሩ |

## ተከታታይ ምዘናና መኩራ

### ተከታታይ ምዘና

ተከታታይ ምዘና ስለተማሪዎች እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ከተለያዩና ከበርካታ ምንጮች መረጃ የመሰብሰብና የመተንተን ሂደት ነው፡፡ ተከታታይ ምዘና የሚከናወነው ተማሪዎች የሚያውቁትን፣ በአንድ ነገር ላይ ያላቸውን ጥልቅ ግንዛቤና ከቀሰሙት እውቀት አንፃር ሊተገበሩ የሚችሉትን ለማወቅና ለማጎልበት ነው፡፡ ተከታታይ ምዘና ግቡን የሚመታው የተከታታይ ምዘናው ውጤቶች የትምህርቱን ሂደት ማሻሻል ሲያስችሉ ነው፡፡ ስለዚህ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎች የመማር ሂደት አካል ሲሆን የሚከተሉትን ያካትታል፡-

- ስለተማሪዎች የትምህርት ክትትል መረጃ ይሰጣል፣
- የማስተማር መማሩን ሂደት ለማሻሻልና ለማረጋገጥ ይቻሉ ዘንድ መረጃዎችን በመተንተን ላይ እንድታተኩሩ ያደርጋል፣
- ተማሪዎች የሚጠበቁባቸውን ግቦች ማሳካታቸው መረጃ ይሰጣል፣
- ትምህርታዊና ተቋማዊ መሻሻል እንዲደረግ ፍንጭ ይሰጣል
- የተደረጉት ለውጦች በተማሪዎች የመማር አቅም ላይ ያመጡትን መሻሻል መገምገም ያስችላል::

በአጠቃላይ የመማር ሂደት የተማሪ ተኮር ሥነ ዘዴ የመጨረሻ ትኩረትና ግብ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ተከታታይ ምዘና ተማሪ ተኮር የትምህርት ሥነ ዘዴ እንዲዳብር ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡

የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሲከታተሉ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ማተኮር አለብዎት፡-

- ተማሪዎች ምን ተምረዋል፣ ከተማሩት ውስጥ ምን ያህል አውቀዋል? ምን ክህሎትን አዳብረዋል? ምንስ ያህል የአስተሳሰብ ወይም የአመለካከት ለውጥ አምጥተዋል?
- አስተምሬ ለመድረስ ያሰብኩበትን ግብ ከመምታት አኳያ ምን ያህል ተሳክቶልኛል?

በርካታ ዓይነት ተከታታይ ምዘናዎች ቢኖሩም አሁን የምናተኩረው በተማሪ ተከታታይ ምዘና ላይ ነው፡፡ የተማሪ ተከታታይ ምዘና የሚከተሉትን ለማወቅ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

- ተማሪዎች ምን ያህል እውቀት እንደቀሰሙ፡፡
- የተማሪዎች ክህሎት ምን ያህል መሻሻሉንና መጎልበቱን፡፡
- ተማሪዎች ሥራ ለመሥራት ስላላቸው አቅምና በአቅማቸው ምን ያህል መጠቀም እንደሚችሉ፡፡

- ተማሪዎች ስለሥራ ትጋታቸው ያላቸው ስሜት ወይም ተነሳሽነት ወይም በአጠቃላይ ስላሳዩት የአመለካከት ለውጥ፡፡

**የተከታታይ ምዘና ተግባራት ምን ምን ናቸው?**

- ለተማሪዎች ምን ያህል መማር እንዳለባቸው ማሳወቅ
- ተማሪዎች ምን ያህል ጠንክሮ በመሥራት ላይ ስለመሆናቸው ማስገንዘብ
- በትምህርቱ ምዕራፍ መገባደጃ ላይ ተማሪዎች ጠንክረው ስለመሥራታቸው ማመልከት
- የተማሪዎች ክህሎትና የአመለካከት ለውጥ የደረሰበትን ደረጃ መጠቆም

**እርስዎ የትምህርቱን ሂደት እንዴት መከታተል ይችላሉ?**

- ዕለት በዕለት በሚያደርጉት ምልከታ
- ተከታታይና ዱብዳ ሙከራዎች (ቴስቶች) በመስጠት
- የፕሮጀክት ሥራና የመሳሰሉትን በማዘጋጀት ተማሪዎች በቡድን ሆነው እንዲሠሩ በማድረግና ያገኙትን ውጤት በመገምገም

**በተከታታይ ምዘና እነማን መሳተፍ አለባቸው?**

- መምህራን
- ተማሪዎች
- ወላጆች
- የትምህርት ባለሙያዎች

**ሙከራ/ፈተና**

ከትምህርት አንፃር ሙከራ ሥርዓት ባለው መንገድ የአንድን ሰው እውቀት፣ ክህሎት፣ አመለካከትና ሌሎች ተጓዳኝ የባህርይ ለውጦችን የመለካት ሂደት ማለት ነው፡፡ በርካታ የሙከራ ዓይነቶች አሉ፡፡ መምህራን የተማሪዎቻቸውን የመማር ችሎታ ለመቃኘት ሙከራዎች ይሰጣሉ፡፡ ከዚህም በላይ ተማሪዎች አንዱን የትምህርት ርዕስ ምን ያህል

በብቃት ተምረው መገንዘባቸውን ለማወቅ ሙከራዎች እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

**ደረጃቸውን የጠበቁ ሙከራዎች/ፈተናዎች**

አብዛኞቹ በጽሑፍ የሚቀርቡና ተማሪዎች የሚወስዷቸው ሙከራዎች ደረጃቸውን የጠበቁ ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ አንድ ሙከራ ጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ ተከልሶና በድጋሚ ጥቅም ላይ ውሎ ተመሳሳይ ውጤት ሲያስመዘግብ እንዲሁም የወሰዱት ተማሪዎች ተመሳሳይ አማካይ ውጤት ሲያስመዘግቡ ሙከራው ደረጃውን የጠበቀ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የአንድ ሙከራ ጥራት በሦስት ዋና ዋና ደረጃዎች ይወሰናል፡፡ እነሱም፡-

- ሙከራው የትምህርቱን ግብ የመምታት አቅሙ(Validity)
- ተአማኒነቱ (reliability)
- ተፈጻሚነቱ (practicality) ናቸው

**የትምህርቱን ግብ የመምታት አቅሙ፡-** አንድ ሙከራ ሊለካው የተገመተውን ግብ መለካት ሲችል፤

**ተአማኒነት፡-** በሙከራው ላይ የተገኘው ተከታታይ ውጤት ተመጣጣኝ ሲሆን ተአማኒነትን ለማረጋገጥ አንድ ሙከራ ለአንድ ቡድን በተደጋጋሚ ሊሰጥ ይችላል፡፡ በተሰጠበት ጊዜ ሁሉ በጣም የተቀራረቡ ውጤቶች ሊመዘገቡ ከቻሉ ሙከራው በጣም ተአማኒ ወይም አስተማማኝ ነው ማለት ይቻላል፡፡

**ተፈጻሚነት፡-** ሙከራው የሚጠይቀው ወጪ ከአቅም ጋር መገናዘብንና የሚሰጥበት አካባቢን ምቹነት ይመለከታል፡፡ በአንፃሩ ሙከራው ከፍተኛ ወጪና ትጋት የማይጠይቅ ከሆነ ተፈጻሚነቱ ከፍተኛ ይሆናል፡፡ ሙከራውን ለማዘጋጀት ብዙ ወጪና ትጋት የሚጠይቅ ከሆነ ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም፡፡ የሚመዘገበው ውጤትም ለመተንተን አስቸጋሪ ከሆነ የሙከራው ተፈጻሚነት አስተማማኝ አልነበረም ማለት ይቻላል፡፡

**የሙከራ ዓይነቶች**

አብዛኞቹ ሙከራዎች አንድ ወይም ከአንድ በላይ ባህሪያት እንዲለኩ ተደርገው ይዘጋጃሉ፡፡ እነዚህ ባህሪያት የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡፡

- የመማር ችሎታ
- የትምህርት ውጤት
- ዝንባሌና ፍላጎት

**በመማር ሂደት ላይ የተመሠረቱ ሙከራዎች፡-** በአቅም ላይ የተመሠረቱ ሙከራዎች ሲሆኑ አንድ ተማሪ የማወቅ ብቃቱን ተጠቅሞ ወደፊት ምን ያህል መሥራት እንደሚችል የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ እነዚህ ሙከራዎች አንዳንድ ጊዜ የብስለት ሙከራዎች፣ የአእምሮ ችሎታ ሙከራዎች፣ የአከዳሚክ ዝንባሌ ሙከራዎች በመባል ይታወቃሉ፡፡

**የመማር ብቃት ሙከራ፡-** ይህ ዓይነቱ ሙከራ ደረጃቸውን በተጠበቁ ተግባራት ወይም ጥያቄዎች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ተማሪው/ዋ በሕይወት ዘመኑ/ኗ በመደበኛ ትምህርት ወይም ከመደበኛ ትምህርት ውጭ ያገኘውን እውቀትና ክህሎት እንዲያሳይ/ እንድታይ ይረዳል፡፡

**ውጤት ላይ ያተኮረ ሙከራ፡-** አንድ ተማሪ ካለው ካላት ጠቅላላ እውቀት ይልቅ አንድ የትምህርት ርዕስ በክፍል ውስጥ ተምሮ ምን ያህል እውቀት እንዳገኘ/ች ይለካል፡፡ ከሌላው የሙከራ ዓይነት በበለጠ ትምህርት ቤቶች ውጤት ላይ ባተኮረ ሙከራ ይጠቀማሉ፡፡

አብዛኞቹ በአንደኛ ደረጃም ሆነ በሁለተኛ ደረጃ ወይም በኮሌጅ የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪዎችን የትምህርት ክትትል ለማወቅ ውጤት ላይ ያተኮሩ ሙከራዎች ይሰጣሉ፡፡

# የትምህርት እቅድ ናሙና

የትምህርት ቤት ስም ______________________ የትምህርቱ ክ/ጊዜ 45 ደቂቃዎች

ክፍል 5ኛ ትምህርቱ የሚሰጥበት ቀን ____________________

የመምህሩ ስም ____________________ የትምህርቱ ንዑስ ርዕስ ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ

ከትምህርቱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች፡ የርዕሱን ትምህርቱን ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፣

- ስኤች አይ ቪ/ኤድስ ስሚያጋልጡ ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ሳይ ማብራሪያ ይሰጣሉ::
- ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ስምሳሌ ጠለፋ፣ የሴት ልጅ ግርዛት እና ንቅሳት የሚያመጡትን አሉታዊ ተጽእኖ ተንትነው ያስረዳሉ::

| ጊዜ | ይዘቶች | የመምህሯ/ሩ ተግባር | የተማሪዎች ተግባር | የትምህርት መርጃ መሣሪያ |
|---|---|---|---|---|
| 4 | • ኤች አይ ቪ/ኤድስና ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶች<br>• ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና የኤች አይ ቪ/ኤድስ መስፋፋት | **መግቢያ:-** ትምህርቱን ለማስተዋወቅ የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ማቅረብ<br>• ልማዳዊ ድርጊቶች ምንድን ናቸው?<br>• ኤች አይ ቪ እና ኤድስ ልዩነታቸው ምንድን ነው? | • ለጥያቄዎች ምላሽ በመስጠት ይሳተፋሉ:: | • ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን የሚያሳዩ ፎቶ ግራፍ ወይም<br>• ፓስተሮች |

| ጊዜ | ይዘቶች | የመምህሯ/ሩ ተግባር | የተማሪዎች ተግባር | የትምህርት መርጃ መሣሪያ |
|---|---|---|---|---|
| 21 | • የኤች አይ ቪ/ኤድስ መስፋፋት መንስኤና የሚያስከትለው ተጽእኖ ለጕዳና ተዳዳሪነት መጋለጥ፣ ወላጅ ማጣት | **የትምህርቱ አቀራረብ፡-** የክፍሉን ተማሪዎች በቡድን ከፋፍለው በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይተው ለክፍል ዘገባ እንዲያቀርቡ ማድረግ፣<br>• በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ በስፋት የሚፈፀሙ ጕጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን የሚያሳዩ ፎቶግራፎችና ፖስተሮች በመጠቀም ለይታችሁ ዘርዝሩ፡፡<br>• ኤች አይ ቪ/ኤድስ እንዴት ለኢኮኖሚያዊና ለማህበራዊ ችግሮች መንስኤ ይሆናል? | • በየቡድናቸው ርዕስ ላይ ይወያያሉ፡፡<br>ከየቡድኑ የተመረጡ ተማሪዎች የየቡድና ቸውን ዘገባ ያቀርባሉ፡፡ | |
| 16 | | **ማጠናከሪያ፡-** የቡድኖች ዘገባ እንዲቀርብ በማድረግ ዘገባው ከተደመጠ በኋላ ጕጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በመግለጽ የዕለቱን ርዕስ ትምህርት ማጠቃለል፡፡ | • የማጠቃለያ ማብራሪያ ይከታተላሉ፡፡<br>• ለግምገማ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት ይሳተፋሉ፡፡ | |

| ጊዜ | ይዘቶች | የመምህሯ/ሩ ተግባር | የተማሪዎች ተግባር | የትምህርት መርጃ መሣሪያ |
|---|---|---|---|---|
| 4 | | **ግምገማ፡-** የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማቅረብ ተማሪዎች የዕለቱን ትምህርት ምን ያህል እንደጨበጡ መገምገም ይቻላል፡፡<br>• ከጋብቻ ሥርዓት ጋር የተያያዙ ጐጂ ለማዳዊ ድርጊቶች ምንድን ናቸው?<br>• ከሕፃናት አስተዳደግና እንክብካቤ ጋር የተያያዙ ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ምንድን ናቸው?<br>• ኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚያስከትለው ኢኮኖሚያዊ ጫና ምንድን ነው?<br>• ኤች አይ ቪ/ኤድስ ምን ዓይነት ማህበራዊ ጫና ያስከትላል? | | |

የመምህሯ/ሩ ፊርማ ______________________

የርዕሰ መምህሯ/ሩ ፊርማ ______________________

# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
# ትምህርት ሚኒስቴር

# ህብረተሰብ ሣይንስ በመማር ከየክፍል ደረጃው የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት ደረጃ
# 5ኛ ክፍል

## የህብረተሰብ ሣይንስ የ5ኛ ክፍል አጥጋቢ የመማር ብቃት

| | 5ኛ ክፍል |
|---|---|
| **ህዝብ** | • በአፍሪካ ቀንድ ያሉ ሀገሮችን መገኛ መናገር፣ |
| | • የኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ ህዝቦችን ታሪክ፣ቋንቋ እና ሐይማኖቶች መግለፅ፣ |
| | • የኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ ጥንታዊ ሥልጣኔን፣ ቅርስን እና ባህል ማድነቅ፣ <br>• ጥንታዊ የኢትዮጵያ ግዛቶች ያከናወኗቸውን ዋና ዋና ታሪካዊና ፖለቲካዊ ክንውኖች መለየት፣ <br>• ቅኝ ገዥነትን በመዋጋት ረገድ አንድነት ያለውን አስፈላጊነት መገንዘብ እና ዘመናዊነት በኢትዮጵያ እንዴት እንደተጀመረ መወያየት፣ |
| | • በኢትዮጵያ እና በአፍሪካ ቀንድ ለህዝቦች አሰፋፈር፣ አኗኗር እና ሥርጭት ልዩነት ምክንያት የሆኑ እንደ መሬት ገፅታ፣ የተፈጥሮ ሃብትና የአየር ንብረት ወዘተ መዘርዘር፣ |
| | • በኢትዮጵያ ለህዝቦች አሰፋፈር፣አኗኗር እና ሥርጭት ልዩነት ምክንያት የሆኑ ሁኔቶችን/ምክንያቶችን/ ለማመልከት የሚያስችል ንድፍ ካርታ ማዘጋጀት፣ |
| **መሬት** | • የመሬትን ቅርፅና መጠን መግለፅ፣ <br>• የመሬትን ሽክርክሪትና የመሬትን መዞር መገንዘብ፣ ወቅቶችን መሰረት በማድረግ በሀገራችን የሚካሄደውን የእርሻ እንቅስቃሴ መፈረጅ፣ |

| | 5ኛ ክፍል | |
|---|---|---|
| ሥነ ምህዳር እና ተግዳሮቶቹ (ፈታኝ ሁኔታዎች) | ሥነ ምህዳር እና ተግዳሮቶቹ | • በኢትዮጵያ እና በአፍሪካ ቀንድ የተፈጥሮ ዕፅዋት እና የዱር እንስሳት ሥርጭት ላይ ተፅዕኖ የሚየሳድሩ ዋና ዋና ሁነቶችን/ምክንያቶችን/ መለየት |
| | | • የኢትዮጵያ እና የአፍሪካ ቀንድ የተፈጥሮ ዕፅዋት እና የዱር እንስሳትን ጠቀሜታ መገንዘብ፤ |
| | | • በኢትዮጵያ እና በአፍሪካ ቀንድ ህዝብ፣ የተፈጥሮ ዕፅዋት እና የዱር እንስሳትመካከል ያለውን መስተጋብር ማብራራት፤ |
| ሥነ ምህዳር እና ተግዳሮቶቹ (ፈታኝ ሁኔታዎች) | | • የአየር ንብረት በኢትዮጵያ እና በአፍሪካ ቀንድ ህዝብ ፣የተፈጥሮ ዕፅዋት እና የዱር እንስሳት ሥርጭት ላይ ያለውን ተፅዕኖ መተንተን፤ |
| | | • ፈጣን የህዝብ ዕድገት ፣በኢትዮጵያ እና በአፍሪካ ቀንድ የተፈጥሮ ዕፅዋት እና የዱር እንስሳት የሚያስከትለውን ተፅዕኖ መገንዘብ፤ |
| | | • በኢትዮጵያ እና በአፍሪካ ቀንድ ፣የተፈጥሮ ዕፅዋት እና የዱር እንስሳትን በአግባቡ ለመጠቀም በሚያስችሉ መንገዶች ላይ ዕብረቃ ማድረግ፤ |

| | 5ኛ ክፍል | |
|---|---|---|
| **ህዝባዊ ጉዳዮች** | ሥነ ህዝብ ነክ ጉዳዮች | • ኤች አይቪ/ኤድስ በኢትዮጵያ ላይ ሥለሚያስከትለው ተፅዕኖ ዕብረቃ ማድረግ፤<br>• ፈጣን የህዝብ ዕድገት ሥለሚያስከትለው ጉዳት መግለፅ፤ |
| | የደህንነትና የመብት ጉዳዩች | • በዋና ዋና የህፃናት መብት ይዘቶች ላይ ውይይት ማድረግ<br>• በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ የሚታየውን መልካም አስተዳደር መገንዘብ<br>• የአደጋና ደህንነት ጥበቃ አይነቶችን መዘርዘር |
| | አጋርነትን የማጠናከር ፕሮግራም | |

# የሕብረተሰብ ሣይንስ መርሃ ትምህርት
# 5ኛ ክፍል

## የአምስተኛ ክፍል ሕብረተሰብ ሣይንስ ትምህርት መማር ውጤቶች

1. ***ዕውቀትና ግንዛቤን ማዳበር***
   - የአፍሪካ ቀንድ ሀገራትን አንፃራዊ የመገኛ እና በእነዚህ ሀገራት የሚነገሩ ዋና ዋና የቋንቋ ቤተሰቦች
   - የኢትዩጵያና የአፍሪካ ቀንድ ጥንታዊ መንግስታትእና ዋና ዋና ታሪካዊና ፖለቲካዊ ክንዋኔዎቻቸው
   - በከፍተኛና ዝቅተኛ ስፍራዎች በሚኖሩ የኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል የአሰፋፈር፣ የባህልና የአኗኗር ዘይቤ መለያየት ዋና ዋና ምክንያቶችን መለየት
   - ዋና ዋና የእፅዋትና የዱር አራዊት አይነቶችና እነዚህን የመንከባከቢያ መንገዶች
   - በኢትዮጵያ ለኤች አይ ቪ /ኤድስ የሚያጋልጡ ኋላቀር ባህላዊ ድርጊቶችና አሉታዊ ተፅዕኖ
   - ከኢኮኖሚ እድገት ጋር ያልተመጣጠነ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር መጨመርና የሚያስከትለው አሉታዊ ተፅዕኖ
   - የመልካም አስተዳደር መገለጫዎችና የሕፃናት መብት
   - የመሬት ቅርጽ፣ እንቅስቃሴና የእንቅስቃሴው ውጤቶች

2. ***ክህሎትንና ችሎታን ማዳበር***
   - በአፍሪካ ካርታ ላይ የኢትዮጵያን አንጻራዊ መገኛ መጠቆም
   - ንድፈ /ግርድፍ/ ካርታን መሳልና መረዳት፡፡
   - በኢትዩጵያ የሚገኙ የተፈጥሮ እጽዋትንና የዱር እንሰሣት መንከባከብ
   - ከግብርና ጋር በተያያዘ ወቅትን የጠበቀ የክንውን መርሃ ግብር /እቅድ/ ማዘጋጀት
   - ለኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚያጋልጡ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ላይ ጥናታዊ ዳሰሳ ማድረግና በሽታውን እንዴት መከካል እንደሚቻል ግንዛቤ መጨበጥ፡፡

3. ***አመለካከትና ዝንባሌ ማዳበር***
   - በኢትዮጵያ ውስጥ ዘመናዊነት /እድገትን/ለማምጣት/ በሚደረጉ ተግባራት ተሣትፎ ማድረግ፡፡
   - ፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር በእፅዋትና በዱር አራዊት ላይ የሚኖረውን ተጽእኖ ማቀናጀት
   - አደጋዎችን ለመከላከል የጥንቃቄ ዘዴዎችን መከተል፡፡
   - ዘመናዊነትን ለማስተዋወቅና ለማስፋፋት የተደረጉትን ጥረቶችና ውጤታቸውን ማድነቅ፡፡

## ምዕራፍ አንድ፦ የኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት መገኛና የሕዝቦች አሰፋፈር
*(23 ክፍለ ጊዜያት)*

***አጠቃላይ የሚጠበቅ ውጤት፦*** ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፦

- የአፍሪካ ቀንድ ሀገራትን ስምና አንፃራዊ መገኛቸውን ይገልፃሉ፡፡
- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ የነበሩ ጥንታዊ መንግስታትን ይጠቅሳሉ፡፡
- በኢትዮጵያ ውስጥ የተከናወኑ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ክዋኔዎችን /ስኬቶችን/ ያደንቃሉ፡፡
- የዘመናዊነት ዋና ዋና ክንዋኔዎች ያደንቃሉ፡፡
- በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጥረው የነበሩ ጥንታዊ መንግስታትና ዋና ዋና ስኬታማ ክንዋኔዎቻቸውን ያብራራሉ፡፡
- በከፍተኛና ዝቅተኛ ስፍራዎች በሚኖሩ የኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል የአሰፋፈር የባህልና የአኗኗር ዘይቤ ልዩነት መንስኤዎችን ይለያሉ፡፡

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦*<br>• የአፍሪካ ቀንድ መገኛን ይገልፃሉ፡፡<br>• ሰላጤ መገኛን (ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምዕራብ፣ ምስራቅ) በመጠቀም የአፍሪካ ቀንድ መገኛን ይገልፃሉ፡፡ | ***1. የአፍሪካ ቀንድ ሀገራትና መገኛቸው***<br>**1.1. የአፍሪካ ቀንድ ሀገራትና መገኛቸው**<br>(4 ክፍለ ጊዜ)<br>• የአፍሪካ ቀንድ አንፃራዊ መገኛ | • የተጠቀሰውን ይዘት በቀላሉ ሊያሳይ የሚችል የአፍሪካ ካርታ በጥቁር ሰሌዳ ላይ መሳል ወይም ሌላ ዘዴን ተጠቅሞ አፍሪካን |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ ሀገራትን ስም ይጠቅሣሉ፡፡<br>• የአፍሪካን ካርታ በመጠቀም የኢትዮጵያን አንፃራዊ መገኛን ያሣያሉ፡፡<br>• ሰላጤ (Cardinal) መገኛን (ሰሜን ደቡብ፣ ምዕራብና ምስራቅ አቅጣጫዎችን) በመጠቀም የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ዋና ዋና ከተሞችን ይገልፃሉ፡፡ | • የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት | ማመልከት፡፡ ተማሪዎቹ የተሳለውን ነገር በማየት የመሰላቸውንና የገባቸውን ያህል እንዲገልፁ ማድረግ፡፡ በመቀጠል ተማሪዎች የአፍሪካ ቀንድ አቅጣጫና መገኛን ከአጠቃላይ አፍሪካ አንፃር እንዲገልፁ ጥያቄዎችን ማንሳት፡፡ ከተማሪዎች መካከል አንዳንድ ተማሪዎችን በማስነሳት በጥቁር ሰሌዳው ላይ በተሳለው የአፍሪካ ካርታ ላይ የኢትዮጵያን ካርታ እንዲያነሱና የአዲስ አበባንም መገኛ እንዲጠቁሙ ማድረግ፡፡<br><br>• ከዚህ በመቀጠል ተማሪዎች የኢትዮጵያ አጎራባች የሆኑትን ሀገራት እንዲጠቅሱ ማድረግ ለምሳሌ እንደ ሱዳንና ኬንያና የመሳሰሉትን አጎራባች ሀገራት በጥቁር ሰሌዳው ላይ በተሳለው የአፍሪካ ካርታ ላይ እንዲስሉ ማድረግ፡፡ ከዚህ በኋላ ተማሪዎች የአፍሪካ ቀንድን የሚያዋስኑ የውሃ አካላትን ለምሳሌ  ቀይ ባህር፣ የኤደን ባህረ ሰላጤ እንዲሁም የሕንድ ውቅያኖስን ስም እንዲጠቅሱ ማድረግ፡፡<br>• በመጨረሻም ተማሪዎች የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ዋና ዋና ከተሞችን ስም እንዲዘረዝሩ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| | | ማድረግና በካርታ ላይ መገኛቸውን እንዲያመለክቱ ማድረግ፡፡<br>• በተማሪዎች የመማሪያ መፅሐፍ ላይ የሚገኘውን የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ የበረራ ስርጭትና መዳረሻ በመጠቀም ከአዲስ አበባ አንፃር የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ዋና ዋና ከተሞች በየት አቅጣጫ እንደሚገኙ ተማሪዎች እንዲመልሱ ጥያቄ መጠየቅ ለዚህም ምሳሌ ይሆን ዘንድ አንድ ከተማ ለምሳሌ ሞቃዲሾ በደቡብ ምስራቅ እንደምትገኝ መንገር ሌላውን ተማሪዎች እንዲሰሩ ማድረግ<br>• በመጨረሻም ተማሪዎቹ በጥቁር ሰሌዳው ላይ የተሳለውን የአፍሪካ ካርታና በውስጡ የያዘውን ስለ አፍሪካ ቀንድ ጠቃሚ መረጃዎች በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ እንዲገለብጡ ማድረግ፡፡ በማጠቃለያም ለተማሪዎች አንድ ምሳሌ በመስራት የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ዋና ከተሞች ከአዲስ አበባ ምን ያህል ኪሎ ሜትር ርቀው እንደሚገኙ በክፍል ስራ መልክ ተማሪዎች እንዲያሰሉ ማድረግ፡፡ ከዚያም የአየር መጓጓዝ ምን ያህል ለውጥ ማምጣት እንደቻለ እንዲወያዩ ማድረግ፡፡ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| | | • *በተቻለ መጠን ከላይ የተዘረዘሩትን ግልፅ ማድረግ የአየር ትራንስፖርት አቅጣጫና መዳረሻን የሚያሳይ ትክክለኛውን ካርታ ወይም አስመስሎ የተሰራውን መጠቀም* |
| • በአፍሪካ ቀንድና በኢትዮጵያ የሚገኙትን ዋና ዋና ቅሬተ አካልና ቅሬተ ቁስ መገኛ ስፍራዎችን ይለያሉ፡፡<br>• የግኝቶችን የጊዜ ቅደም ተከተልና ጥቅማቸውን ለይተው ያውቃሉ፡፡ | **1.2. የኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ ሕዝቦች ታሪክና አሰፋፈር**<br>*(11 ክ/ጊዜ)*<br>• የሰው ልጅ ዘር መገኛና ጥንታዊ ቅሪተ አካልና ቅሬተ ቁስ መገኛዎች ኢትዮጵያና ኬንያ<br>*(3 ክ/ጊዜ)* | • ዋናውን ትምህርት ከማብራራትና ዘለቅ ያለ እውቀት ከማስያዝ በፊት መምህሩ/ሯ ተማሪዎች የሚያውቋቸውንና የሰሟቸውን ረጅም ዓመታት ያስቆጠሩ ቅሬተ አካላትን ስም እንዲጠሩ መጋበዝ ለምሳሌ<br>    • አውስትረሎፒቲክስ አፋራንሲስ (ሉሲ)እና<br>    • ሆምነፒያንስኢደልቱ (ሰላም)፡፡<br>• በነዚህ ቅሪተ አካላት ላይ መምህራን ጠለቅ ያለ ማብራሪያ ከመስጠታቸው በፊት ተማሪዎች የቻሉትን ያህል በእነዚህ ቅሪተ አካል ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡ ማድረግ፡፡ ከዚህ በኋላ የእነዚህን ቅሬታ አካላት ስም በጥቁር ሰሌዳ ላይ መፃፍ ተማሪዎችም እንዲፅፉ ማድረግ፡፡ ቀጥሎም በካርታ በመታገዝ የት እንደተገኙ መቼ እንደተገኙ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ ዋና ዋና የሀይማኖቶችን አመጣጥና ሽፋንን ይገልጻሉ፡፡<br>• በአፍሪካ ቀንድና በኢትዮጵያ ያለው የሀይማኖት መቻቻል የረጅም ጊዜ ታሪክ መሆኑን በመገንዘብ አድናቆታቸውን ይገልጻሉ፡፡<br>• ኢትዮጵያ የብዙ እምነት ተከታይ ሀገር መሆኗን መገንዘባቸውን ይገልፃሉ፡፡ | • የክርስትናና የእስልምና ሀይማኖቶች/አመጣጥ በአፍሪካ ቀንድ ሀገራት *(2 ክ/ጊዜ)* | ማብራሪያዎችን መስጠት ተማሪዎችም እነዚህን መረጃዎች በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ እንዲፅፉ ማድረግ፡፡ ከዚህ በኋላ የእነዚህን ቅሬት አካል ግኝት ቅደም ተከተል እንዲወያዩ መርዳትና በውይይታቸው መጨረሻ ላይ ተማሪዎችን ተራ በተራ በመጥራት የቅሬተ አካሎቹን ስም በቅደም ተከተል ጥቁር ሰሌዳ ላይ እንዲፅፉ ማድረግ፡፡ ስህተት ካለም ማስተካከያ ማድረግ፡፡<br>• *ስለ አንድ ኢትዮጵያዊ አርኪዎሎጂስትና ስለአከወናቸው ተግባራት ታአማኒነት ያለው በፎቶ የተደገፈ ውሱን ጥናት ማካተት*<br>• ትምህርቱን ለመጀመር ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል የውይይት ጥያቄዎችን ጥቁር ሰሌዳው ላይ መፃፍ፡፡ ለምሳሌ በአፍሪካ ቀንድ የክርስትናና የእስልምና አመጣጥ መቼ፣ እንዴትና በማን እንደመጣ በቡድን እንዲወያዩና የተወያዩትን በተወካያቸው አማካኝነት በክፍል ተማሪዎች ፊት እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡ ከዚህ በመቀጠል ለአቅራቢ ተማሪዎች የቃላት ማበረታቻ መስጠት የተማሪዎቹን ማብራሪያ ለማጠናከር |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| | | ተጨማሪ ማስታወሻ በጥቁር ሰሌዳ ላይ መፃፍ ተማሪዎችም እንዲፅፉ መርዳት ከዚህ በመቀጠል ከተለያዩ መፅሐፍትና አፈታሪኮች በመውሰድ ለተማሪዎች ስለ ሀይማኖት አመጣጥ እውቀታቸውን ሊያዳብር የሚችል መረጃ መስጠት፡፡ አሁን በሀገራችን ስለ ሀይማኖት መቻቻል ያለው ተጨባጭ ሁኔታና ከዚህ በፊት የነበረው ሁኔታ ተመሳሳይነትና ልዩነት ላይ ተማሪዎች የራሳቸውን ሀሳብ እንዲገልፁ ማድረግ፡፡ ኢትዮጵያውያኖች የሀይማኖት ልዩነታቸውን አቻችለውና አንድነታቸውን በልዩነታቸው አጠናክረው /ሳይለያዩ/ እንዴት መኖር እንደቻሉ ተማሪዎች እንዲወያዩ ማድረግ፡፡<br>• *በተጨባጭ የመረጃ ምንጭ ማቴሪያል ላይ ተመርኩዘው ውስን ጥናቶች* |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • ለጥንታዊ የአፍሪካ ቀንድና የኢትዮጵያ መንግስታት ያላቸውን አድናቆት ያሣያሉ፡፡ | **1.3. ቀደምት የኢትዮጵያና የምሥራቅ አፍሪካ መንግስታት**<br>*(3 ክ/ጊዜ)*<br>▪ ፑንትና ዳዓማት<br>▪ አክሱም<br>▪ ዛግዌ<br>▪ የሙስሊም ሱልጣኔቶች<br>▪ ወላይታ<br>▪ ዳሞት<br>▪ ኢናሪያ<br>▪ ከፋ | • በአፍሪካ ቀንድና በኢትዮጵያ ስለተፈጠሩ የጥንት መንግስታት አጠር ያለ ማብራሪያ መስጠት ለምሳሌ ስለፑንትና ዳማት፡፡ መጀመሪያ መንግሥት ምን እንደሆነ ትርጉሙን መንገር፡፡<br>• ተማሪዎች የኢትዮጵያን ካርታ በመጠቀም በኢትዮጵያ ውስጥ ስለተፈጠሩ ዋና ዋና የጥንት መንግስታት መገኛዎች እንዲያሳዩ ማድረግ<br>• ሶስት ሶስት ተማሪዎች የሚይዙ ቡድኖች በመፍጠር የጥንት መንግስታት በኢትዮጵያ የት የት እንደተፈጠሩ በወረቀት ላይ ጽፈው በቡድን ተወካያቸው አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡ ለዚህ ያመች ዘንድ የኢትዮጵያ ካርታን ለተማሪዎች ሁሉ በሚታይ መልኩ በጥቁር ሰሌዳው ላይ በተዘጋጀው መስቀያ ላይ መስቀል፡፡ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • ጥንታዊ የኢትዮጵያ መንግስታት ታሪካዊና ፖለቲካዊ ክንዋኔዎች ይለያሉ፡፡ | **1.3.1.ታሪካዊና ፖለቲካዊ ክዋኔዎቸ *(3 ክ/ጊዜ)*** <br>▪ የአክሱማውያን ዘመን <br>▪ የዛግዌ ስርወ-መንግስት ዘመን <br>▪ የኮንሶዎች ስኬት /ውጤታማነት/ <br>▪ የሀረሪዎች ተግባራት <br>▪ የገዳ ስርዓት (ኦሮሞዎችና ሲዳማዎች) | በመጀመሪያ ተማሪዎች አክሱማውያን፣ ጎንደራዊያን፣ አገዎች፣ ኮንሶዎች፣ ሀረሪዎችና፣ የገዳ ስርዓት ተከታይ የሆኑት ኦሮሞዎችና ሲዳማዎች ያከናወኗቸውን ዋና ዋና ክንዋኔዎችን በተመለከተ ሪፖርት ፅፈው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ መጋበዝ ለምሳሌ <br>• አክሱማውያን — • ዛሬ የአክሱም ሀውልት እያልን የምንጠራውን መስራታቸው <br>• አገዎች — • የዛሬውን የላሊበላ ውቅር አቢያተ ክርስቲያናት ማነፃቸውን <br>• ጎንደራውያን — • የጎንደር ቤተ መንግስታትን ማነፃቸውን <br>• ሀረሪዎች — • ዛሬ የጀጎል ግንብ እያልን የምንጠራውን መገንባታቸውን <br>• ኦሮሞዎችና ሲዳማዎች — • በአፍሪካ በከፊልም ቢሆን ከዘመኑ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ጋር የሚመሳሰል የገዳ ስርዓት መጀመራቸውን |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • የኢትዮጵያውያን ልበ ሙሉነትና አንድነት ለአድዋ ድል የነበረውን ጠቀሜታ ያብራራሉ፡፡<br><br>• በኢትዮጵያ ዘመናዊ የአኗኗር ዘይቤ መጀመር ስላበረከተው አስተዋፅኦ ይወያያሉ፡፡ | **1.3.2. የኢትዮጵያ አንድነትና ዘመናዊነት**<br>*(5 ክ/ጊዜ)*<br>• የኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድነት ለአድዋ ድል የነበረው ጠቀሜታ *(3 ክ/ጊዜ)*<br>• በኢትዮጵያ የዘመናዊነት አጀማመር (የትምህርት አሰጣጥ፣ የባንክ፣ የጤና፣ የስልክ፣ የትንስፖርት /መጓጓዣዎች/፣ የፖስታ አገልግሎትና የወታደራዊ አደረጃጀት) *(2 ክ/ጊዜ)* | • የኢትዮጵያ ሕዝቦች የጣሊያንን ወራሪ ሀይል አድዋ ላይ ለማሸነፍ እንዴት ሕብረት እንደፈጠሩ የሚያብራራ አጠር ያለ ፅሑፍ ፅፈው በዛ ላይ እንዲወያዩ ማመቻቸት፡፡ ይህንንም በቡድን እንዲያደርጉት ማድረግ፡፡ ለዚህ ማጠናከሪያ ይሆን ዘንድ የአፄ ሚኒልክን የክተት አዋጅ ማንበብ፡፡ እያንዳንዱ ቡድን ስለ ድሉ ግጥምና ዜማ ለመፃፍ እንዲሞክሩ ማበረታታት፡፡<br>• በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻና በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ ዘመናዊነት በኢትዮጵያ እንዴት እንደተጀመረ የሚያውቁትን ነገር በአጭሩ እንዲገልፁ ማበረታታት፡፡ ከዚህ በመቀጠል ተማሪዎች ዘመናዊነት በኢትዮጵያ መጀመሩ ያመጣውን ለውጥና ስኬት በቡድን ሆነው እንዲወያዩ ማድረግ፡፡ የተወያዩትን ሀሳብ በወረቀት ፅፈው ለክፍል ጓደኞቻቸው በተወካያቸው አማካይነት እንዲያቀርቡ ማድረግ<br>• በመጨረሻም ዘመናዊነት በኢትዮጵያ መጀመር ያለውን ጥቅምና ጉዳት በተመለከተ የሀሳብ ልዩነት ካለ ተማሪዎች እንዲከራከሩና መተማመን ላይ እንዲደርሱ ማድረግ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል የሕዝብ አሰፋፈር ልዩነት እንዲፈጠር ጉልህ ሚና ያላቸውን ምክንያቶች ይጠቅሣሉ፡፡<br>• አፍሪካ ቀንድና በኢትዮጵያ የሕዝብ አሰፋፈር ከአኗኗር ዘይቤ ጋር ያለውን ግንኙነት ያብራራሉ፡፡<br>• በኢትዮጵያ በከተማና በገጠር፣ በከፍተኛና ዝቅተኛ ስፍራዎች በሚኖሩ ሕዝቦች መካከል ያለውን የባህልና የአኗኗር ዘይቤ ተመሳሳይነትና ልዩነት ይገልጻሉ፡፡ | **1.4. የሕዝብ አሰፋፈርና ባህል ልዩነት እንዲፈጠር ጉልህ ሚና ያላቸው ምክንያቶች** (3 ክ/ጊዜ)<br>• የአሰፋፈር ልዩነት፡- አየር ንብረት፣ የተፈጥሮ ሀብት ክምችትና የደህንነት ሁኔታ<br>• በኢትዮጵያ በከተማና በገጠር፣ በከፍተኛና ዝቅተኛ ስፍራዎች በሚኖሩ ሕዝቦች መካከል የባህልና የአኗኗር ዘይቤ ልዩነት | • አራት ቡድን መፍጠርና የቡድን ሥራ ማሰራት<br>  • ቡድን ሀ - በከፍታ ስፍራ የሚገኙ የገጠር አካባቢዎች (ነዋሪዎች)<br>  • ቡድን ለ - በከፍታ ስፍራ የሚገኙ የከተማ አካባቢዎች (ነዋሪዎች)<br>  • ቡድን ሐ - በዝቅተኛ ስፍራ የሚገኙ የገጠር አካባቢዎች (ነዋሪዎች)<br>  • ቡድን መ - በዝቅተኛ ስፍራ የሚገኙ የከተማ አካባቢዎች (ነዋሪዎች)<br>• እያንዳንዱ ቡድን በመማሪያ መፃፋቸው ላይ ያለውን ወይም በጥቁር ሰሌዳው ላይ የተሳለውን የኢትዮጱያ ካርታን በመመልከት የተሰጣቸው ርዕሰ የት የት እንደሚገኝ ወይም የትኛውን አካባቢ እንደሚያካትት እንዲለዩ ማድረግ፡፡<br>• ከዚህ በመቀጠል ካርታው ላይ በገለፁት አካባቢ የሕዝብ አኗኗር ምን እንደሚመስል ማለትም የመሬት አቀማመጥና የአየር ፀባዩ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| | | በቤት አሰራራቸው ላይ፣ በአለባበሳቸው ላይ ፣ በአስተራረስ ዘዴያቸው ላይ በንግድ እንቅስቃሴያቸውና በአጠቃላይ፣ ባህላቸው ላይ ምን አይነት ተፅእኖ እንዳለው እንዲያብራሩ ማድረግ፡፡ በመጨረሻም የተለያዩ ቡድን አባላት አንድ ላይ እንዲቀመጡ ማድረግ ቀደም ብለው በያዙት የተለያዩ ርዕሰ ላይ ውይይት እንዲያደርጉ ማድረግና በተለያዩ አካባቢዎች ያለውን አጠቃላይ ልዩነት እርስ በርስ እንዲነጋገሩ ማድረግ *(ከላይ የተገለጸውን ውስን ጥናት ናሙና ይመልከቱ)* |

## *ምዘናና ግምገማ*

*መምህራን ከምእራፍ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን የተማሪዎች ተግባራት ተከታታይነት ባለው መልኩ ሊመዘኑና ሊገመግሙ እንዲሁም ያላቸውን ጠንካራና ደካማ ጎን አንጥረው ሊያወጡ ይገባል፡፡ ለዚህ ምዘናና ግምገማ መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ ከምእራፍ ይዘቶች ጋር የተዘረዘሩ የሚጠበቁ የብቃት መለኪያዎች ሊሆኑ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመማር ማስተማር ሂደቱ ከትምህርት ይዘቶችጋር አብረው የተዘረዘሩት አላማዎች ከግብ መድረሳቸውን ሊያንፀባርቅ በሚችል መልኩ ማሳካት አለ ማሳካቱን ሊያሳይ የሚችል ምዘናና ግምገማ ሊካሄድ ይገባል፡፡*

*ሀ. የምእራፍን ይዘቶች ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች ቢያንስ የሚከተሉትን ብቃቶችሊያሳዩ ይገባል፡፡*

- *የኢትዮጵያን አንፃራዊ መገኛ መግለፅ*
- *የአፍሪካ ቀንድ ሀገራትን ስም መዘርዘር*

- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ ዋና ዋና ሀይማኖቶች እንዴት ወደ ክፍለ አህጉሩ እንደገቡ መግለፅ
- በኢትዮጵያና አፍሪካ ቀንድ ተፈጥረው ለነበሩ ጥንታዊ መንግስታትና ክዋኔያቸው አድናቆታቸውን መግለፅ
- የኢትዮጵያ ሕዝቦች ልበ ሙሉነትና አንድነት ለአድዋ ድል የነበረውን ጠቀሜታ ማብራራት
- ዘመናዊነት በኢትዮጵያ እንዴት እንደተጀመረና የነበረውንም አሉታዊና አዎንታዊ ተፅዕኖ ማብራራት
- በአፍሪካ ቀንድና በኢትዮጵያ የሕዝብ አሰፋፈር ከአኗኗር ዘይቤ ጋርያለውን ግንኙነት ማብራራት
- በኢትዮጵያ በከተማና በገጠር፣ በከፍተኛና ዝቅተኛ ስፍራዎች በሚኖሩ ሕዝቦች መካከል ያለውን የባህልና የአኗኗር ዘይቤ ተመሳሳይነትና ልዩነት መግለፅ፡፡
- ከላይ የተጠቀሰው አኗኗርና የባህል ልዩነት እንዲኖር ያደረጉ ምክንያቶችን መዘርዘር ለምሳሌ የአየር ፀባይ፣ የተፈጥሮ ሀብት ክምችት እንዲሁም የደህንነት ሁኔታና ወዘተ

ለ. በ "ሀ" ስር ከተዘረዘሩት ብቃቶች ያለፈ ብቃትና ባህሪ ያሳዩ ተማሪዎች ከተገኙ መምህራንና የሚመለከተው አካል ለነዚህ ተማሪዎች እውቅና ማበረታቻ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ በተጨማሪም እነዚህ ተማሪዎች ይህንን ብቃታቸውን ይዘው እንዲዘልቁ ተገቢው ማበረታቻ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

ሐ. በ "ሀ" ስር ከተዘረዘሩት ያነሰ ብቃት ያሳዩ ተማሪዎች ከተገኙ መምህራን ለእነዚህ ተማሪዎች የተለየ ድጋፍ በማድረግ ከጓደኞቻቸው ጋር ተመሳሳይነት ያለው የትምህርት ብቃት እንዲኖራቸው ሊረዷቸው ይገባል፡፡ ለምሳሌ የክፍለ ትምህርቱን ይዘቶች ተጨማሪ ሰዓታት በመውሰድ መከለስ፣ ከጎበዝ ተማሪዎች ጋር የሚያጠኑበትን መንገድ ማመቻቸት፣ ከቤተሰቦቻቸው ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር ያለባቸውን ችግር ለይቶ በማወቅ የተማሪዎቹን ችግር ሊያቃለል የሚችል እርምጃ መውሰድ፡፡

መ. በተጨማሪም ከዚህ ሌላ ለየት ያለ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ የተለየ ትኩረት መስጠት፡፡ ለምሳሌ አካለ ጉዳተኞች ለነዚህ ተማሪዎች በግምገማና ምዘና ወቅት ተገቢ የሆነ ድጋፍ ማድረግ፡፡

## ምዕራፍ ሁለት፦ መሬትና አካባቢዋ *(10 ክፍለ ጊዜያት)*

**አጠቃላይ የሚጠበቅ ውጤት፦** ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፦

- በትምህርት ቤታቸው ዙሪያ ያሉትን ነገሮች የሚያሳይ ካርታ ደረጃ በደረጃ ያዘጋጃሉ /ይስላሉ/፡፡
- የመሬት መሽከርከር የሚያመጣውን ውጤት /ለውጥ/ ያብራራሉ፡፡
- ጊዜያዊና /ወቅታዊና/ ቋሚ የውሃ ህብቶች የሚባሉትንይለያሉ፡፡

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦*<br><br>• የካርታን ጠቀሜታ ያብራራሉ፡፡<br>• የንድፍ ካርታ እንዴት እንደሚዘጋጅና እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል ያብራራሉ፡፡<br>• የትምህርት ቤታቸውን መገኛ አቅጣጫዎች የሚሳይ ንድፍ ካርታ ያዘጋጃሉ፡፡ | 2. **መሬትና በመሬት ዙሪያ የሚገኙ አካላት**<br>2.1. **መገኛችን** *(4 ክ/ጊዜ)*<br>• አቅጣጫንና መገኛን ለማሳየት ንድፍ ካርታ መጠቀም<br>• ተራ ንድፍ ካርታ ማዘጋጀት | • በጥቁር ሰሌዳው ላይ የመማሪያ ክፍሉን የውስጥ ገፅታ የሚያሳይ ንድፍ መሳል፡፡ የግድግደውን ወርድና ርዝመት መለካት በመቀጠል መለኪያ /ስኬል/ በመጠቀም የመማሪያ ክፍሉ በጥቁር ሰሌዳው ላይ መሳል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ተማሪዎች የክፍሉን በር፣ መስኮት እንዲሁም በክፍል ውስጥ የሚገኙትን መቀመጫና ጠረጴዛ የመማሪያ ክፍላቸውን በመመልከት ጥቁር ሰሌዳው ላይ በተሳለው ንድፍ ላይ በተገቢው ስፍራ እንዲያስቀምጧቸው /እንዲስሏቸው/ ማድረግ በመጨረሻም አንድ ምናባዊ ትምህርት ቤት የሚያሳይ የናሙና ካርታን በመሳል በውስጡም የተለያዩ ገፅታዎችን |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| | | ለምሳሌ ክሊኒክ የሰሜን አቅጣጫን የሚያሳይ ቀስት ማካተት፡፡ በናሙናው ካርታ ላይ ተማሪዎች እንዲወያዩ ማድረግ፡፡<br>• በመቀጠልም ተማሪዎች በማስታወሻ ደብተራቸው በጥቁር ሰሌዳው ላይ የተሳለውን የናሙና ካርታ እንዲያነሱ ማድረግ፡፡ በመቀጠልም ሰሜን/ደቡብ አቅጣጫን የቀኑን የቀትር ሰዓት የፀሀይ አቀማመጥ ተመርኩዘው እንዲያመለክቱ ማድረግ፡፡ ከዚያም ተማሪዎች የመንገዶች፣ ወንዞች ወይም ጠቃሚ ህንጻዎችን ያካተተ ካርታ እንዲስሉ መጠየቅ፡፡ በሚስሉት ካርታ ላይም ማንኛውንም አይነት ነገሮች ስም በመስጠትና የሰሜን አቅጣጫ ቀስትን እንዲያካትቱ ማድረግ፡፡ |
| • የመሬትን ቅርፅና እንቅስቃሴ አይነቶችን ይለያሉ፡፡<br>• የመሬት መሽከርከር የሚያመጣውን ለውጥ /ውጤት/ ያብራራሉ፡፡ | **2.2.የመሬት ቅርፅ፣ እንቅስቃሴና የእንቅስቃሴዋ ውጤቶች** *(4 ክ/ጊዜ)*<br>• የመሬት ቅርፅ<br>• የመሬት እንቅስቃሴና ውጤት | • የመሬት ቅርፅና እንቅስቃሴ ውጤት የሆኑትን የቀንና የሌሊት መለዋወጥ እንዲሁም የወቅቶች መፈራረቅን (በጋ፣ ክረምት፣ በልግና ፀደይ) በቀላሉ ለተማሪዎች ለማሳየት ሉልና የእጅ ባትሪ መጠቀም |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • የወቅቶች መፈራረቅ በአርሶ አደሩ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ የሚያመጣውን ተፅዕኖ ያዛምዳሉ፡፡ | • የቀንና ሌሊት መፈራረቅ<br>• የወቅቶች መፈራረቅ<br>• የመሬት 23½$^{0}$ ማጋደልና የወቅቶች መፈራረቅ | • በደቡብና ሰሜን ንፍቀ ክበብ ከመሬት እንቅስቃሴ ጋር በተያያዥነት የወቅቶች መፈራረቅን የሚያሳዩ ካርታን ተማሪዎች እንዲስሉ በማድረግ በክፍል ውስጥ እርስ በርሳቸው እንዲወያዩ በማድረግ ለሚቀጥለው ክፍል ጊዜ በቡድን ሆነው በተወካያቸው አማካኝነት እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡ |
| • የወቅቶች መፈራረቅ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ (በእርሻና በከብት እርባታ) ያለው አሉታዊና አዎንታዊ ተፅእኖ ያዛምዳሉ፡፡ | 2.3. **የወቅቶች መፈራረቅ በእርሻና በከብት እርባታ ላይ ያለው ተፅዕኖ**<br>*(2 ክ/ጊዜ)*<br>• ወቅቶች በኢትዮጵያ<br>• የወቅቶች መፈራረቅ በእርሻና በከብት እርባታ እንቅስቃሴ ላይ ያለው አሉታዊና አዎንታዊ ተፅእኖ | • ተማሪዎች ከወረቀትና ከመሳሰሉት ነገሮች የመሬት ቅርፅን ሊያሳይ የሚችል ምስል ሰርተው ለመምህራቸው እንዲያቀርቡ ማድረግ በተጨማሪም ከፀሐይ አንፃር መሬት የት እንደምትገኝና 23½$^{0}$ ማጋደሏ የወቅቶችን መፈራረቅ እንዴት እንደሚያስከትል እንዲያሳዩ መርዳት<br>• በመጀመሪያ በከፍተኛ ስፋራ በበጋና በክረምት የሚተገበሩ ተግባራትን ለማወዳደር ውስን ጥናት እንዲያደርጉ ማድረግ ተመሳሳይ የሆነ ተግባር ዝቅተኛ ስፍራ በተመለከተ እንዲያከናውኑ ማድረግ፡፡ ንጽጽሩን አስመልክቶ በክፍል ውስጥ ውይይት እንዲያካሂዱ ማድረግ፡፡ |

## ምዘናና ግምገማ

*መምህራን ከምእራፍ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን የተማሪዎች ተግባራት ተከታታይነት ባለው መልኩ ሊመዘኑና ሊገመግሙ እንዲሁም ያላቸውን ጠንካራና ደካማ ጎን አንጥረው ሊያወጡ ይገባል፡፡ ለዚህ ተከታታይ ምዘናና ግምገማ መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ ከምእራፍ ይዘቶች ጋር የተዘረዘሩት ዝርዝር አላማዎች ሊሆኑ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመማር ማስተማር ሂደቱ ከትምህርት ይዘቶች ጋር አብረው የተዘረዘሩት አላማዎች ከግብ መድረሳቸውን ሊያንፀባርቅ በሚችል መልኩ ማሳካት አለ ማሳካቱን ሊያሳይ የሚችል ምዘናና ግምገማ ሊካሄድ ይገባል፡፡*

*ሀ. የምእራፍን ይዘቶች ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች ቢያንስ የሚከተሉትን ባህሪያት /ለውጦች/ ሊያሳዩ ይገባል፡፡*

- *ትምህርት ቤታቸውንና በትምህርት ቤታቸው ዙሪያ የሚገኙ ነገሮችን የሚያሳይ ንድፈ ካርታ መሳል*
- *የመሬት ቅርፅና የእንቅስቃሴ አይነቶችን መለየት፡፡*
- *የወቅቶች መፈራረቅ በአርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ ያለውን ተፅዕኖ ያገናኛሉ /ያዛምዳሉ/፡፡*

*ለ. በ "ሀ" ስር ከተዘረዘሩት ብቃቶች ያለፈ ብቃትና ባህሪ ያሳዩ ተማሪዎች ከተገኙ መምህራንና የሚመለከተው አካል ለነዚህ ተማሪዎች ማበረታቻ ሊያዘጋጅ ይገባል ለምሳሌ ሽልማት፡፡ በተጨማሪም እነዚህ ተማሪዎች ይህንን ብቃታቸውን ይዘው እንዲዘልቁ ተገቢው ማበረታቻ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡*

*ሐ. በ "ሀ" ስር ከተዘረዘሩት ያነሰ ብቃት የሚያሳዩ ተማሪዎች ከተገኙ መምህራን ለእነዚህ ተማሪዎች የተለየ ድጋፍ በማድረግ ከጓደኞቻቸው ጋር ተመሳሳይነት ያለው የትምህርት ብቃት እንዲኖራቸው ሊረዷቸው ይገባል፡፡ ለምሳሌ የምእራፎን ይዘቶች ተጨማሪ ሰዓታት በመውሰድ መከለስ፣ ከጎበዝ ተማሪዎች ጋር የሚያጠኑበትን መንገድ ማመቻቸት፣ ከቤተሰቦቻቸው ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር ያለባቸውን ችግር ለይቶ በማወቅ የተማሪዎቹን ችግር ሊያቃልል የሚችል እርምጃ መውሰድ፡፡*

*መ. በተጨማሪም ከዚህ ሌላ ለየት ያለ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ የተለየ ትኩረት መስጠት፡፡ ለምሳሌ አካል ጉዳተኞች ከነዚህ ተማሪዎች በግምገማና ምዘና ወቅት ተገቢ የሆነ ድጋፍ ማድረግ፡፡*

## ምዕራፍ ሦስት፡- አካባቢያችን *(19 ክፍለ ጊዜያት)*

**አጠቃላይ የሚጠበቅ ውጤት፡-** ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- በአካባቢያቸው የሚገኙ ዋና ዋና እፅዋትና የዱር አራዊትን ያውቃሉ፣ ተገቢውን ጥበቃም ያደርጋሉ፡፡
- ከኢኮኖሚ እድገት ጋር ተመጣጣኝ ያልሆኑ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር በአካባቢያችን በሚገኙ እፅዋትና የዱር አራዊት ላይ ያለውን አሉታዊ ተፅዕኖ ይገነዘባሉ፡፡

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-*<br><br>• በአፍሪካ ቀንድና በኢትዮጵያ የሚገኙ ዋና ዋና እፅዋትንና የዱር አራዊትን ይለያሉ፡፡<br>• በኢትዮጵያ የሚገኙ ዋና ዋና የዱር እንስሳትን ስም ይዘረዝራሉ፡፡ | ***3. አካባቢያችን፡*** በአካባቢያችን የሚገኙ ዋና ዋና እፅዋትና የዱር አራዊቶች የሚሰጡት ጥቅም<br>**3.1. ዋና ዋና የእፅዋት አይነቶች** *(4 ክ/ጊዜ)*<br>• ደን፣ በሳር የተሸፈነ ምድርና የበረሀ ቁጥቋጦ<br>• በአፍሪካ ቀንድና በኢትዮጵያ የሚገኙ እፅዋት<br>• ዋና ዋና የዱር እንስሳት (በሁሉም የአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ የዱር እንስሳት፣ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ | • በመጀመሪያ ጥቁር ሰሌዳው ላይ ባዶ/ ወይም ምንም የማያሳይ የአፍሪካ ካርታ መሳል፡ በመቀጠል ስለ ባዶው ካርታ ምንም ውይይት /ገለፃ/ ሳይደረግ ተማሪዎች የደን፣ የሳር ምድርና የበረሀ ቁጥቋጦ ምን ማለት እንደሆኑ ማብራሪያ ከነምሳሌያቸው እንዲሰጡ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • በአፍሪካ ቀንድ በሁሉም ሀገሮች የሚገኙ እንስሳትንና በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙትን ይለያሉ፡፡ | ብርቅየ የዱር እንስሳት፣ የመጥፋት አደጋ የተጋረጠባቸው በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ የዱር እንስሳት መጠለያቸው) | መጋበዝ፡፡ ከተወሰነ ደቂቃ በኋላም ሁሉንም ተማሪዎች ሊያሰማማ በቂ ዕውቀት ማስጨበጥ የሚችል ገለፃ ማድረግ፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎች ከመማሪያ መፅሐፋቸው በማየት በጥቁር ሰሌዳው ላይ በተሳለው የአፍሪካ ካርታ ላይ የደን፣ የሳር ምድርንና የበረሀ ቁጥቋጦ ስፋራዎችን እንዲያመለክቱ ማድረግ፡፡ ይህንንም በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ እንዲተገብሩት ማድረግ፡፡ በመጨረሻም ከላይ የጠቀስናቸውን ገፅታዎች የሚያሳየውን ካርታ ደብተራቸው ላይ እንዲስሉት ማድረግ /ማበረታታት/<br>• በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ ብርቅየ የዱር እንስሳትን ስምና የት የት እንደሚገኙ ሰንጠረዥ በመሙላት እንዲመልሱ በመጠየቅ እንዲገልፁ ማድረግ፡፡ በተጨማሪም የመጥፋት አደጋ የተጋረጠባቸው የዱር እንስሳትን በተመሳሳይ መልኩ እንዲለዩ ማድረግ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| | | • በመቀጠል ተማሪዎች ስለ አንድ በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ለሚገኝ የዱር እንስሳ አጠር ያለ ፅሑፍ /አንቀፅ/ ፅፈው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ መርዳት |
| • በአፍሪካ ቀንድና በኢትዮጵያ የተፈጥሮ እፅዋትና የዱር እንስሳት ጥቅም ያስረዳሉ፡፡<br>• ለዱር እንስሳት የተፈጥሮ መኖሪያቸው ጥበቃ ማድረግ ያለውን ጥቅም ይረዳሉ፡፡<br>• የዱር እንስሳት እፅዋትን መንከባከብ ለምን ጠቃሚ እንደሆነ በዙሪያቸው ለሚገኙ ማህበረሰቦች ያብራራሉ፡፡ | 3.2. **የዱር እንስሳትና እፅዋቶች የሚሰጡት ጥቅም**<br>*(4 ክ/ጊዜ)*<br>• በዱር እንስሳትና እፅዋት መካከል ተፈጥሮአዊ ሚዛንን መጠበቅ<br>• አርሶ አደሮችና የዱር እንስሳት ተስማምተው መኖር<br>• ቱሪዝም ለኅብረተሰቡ፣ ለእንስሣትና አርሶ አደሮች ያለው ጥቅሙ | • የዱር እንስሳት መጠለያቸውንና የሚመገቡት ነገር ቢያጡ ምን ሊከሰት እንደሚችል ሰፋ ያለ ውይይት ማድረግ፡፡ ተማሪዎች እንዲህ ያለ የሰሙት ክስተት ካለ እንዲያብራሩ መጋበዝ፡፡ ከዚህ ጋር በማያያዝም ተማሪዎች ለዱር እንስሳት ጥበቃ ማድረግ ለሌሎች ቅርሶች ጥበቃ ከማድረግ እኩል ጠቀሜታ እንዳለውና እንደሌለው እንደሚገነዘቡና እንደማይገነዘቡ ማብራሪያ እንዲሰጡ ማድረግ<br>• **ሚና ጨዋታ፡-** በአንድ መንደር የሚኖሩ አርሶ አደሮች በተደጋጋሚ በሰብሉ ላይ ጉዳት የሚያደርሰውን |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| | | ዝሆን ለመግደል የሚያደርገውን ሙከራ በድራማ መልክ ለክፍል ጓደኞቻቸው በማቅረብ የአርሶ አደሮች ፍላጎትና በዱር እንስሣት (ዝሆን) መካከል ያለውን ሚዛን ለመጠበቅ ምን ማድረግ እንደሚገባው ውይይት ማድረግ፡፡<br>• በአፍሪካ ቀንድና በኢትዮጵያ የተፈጥሮ እፅዋትና የዱር እንስሳት ለቱሪስት መስህብነት የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ላይ ተማሪዎች ውይይት እንዲያደርጉ ማድረግ<br>• በአንድ የቱሪስት መዳረሻ ላይ የዳሰሳ ጥናት በማድረግ ቱሪዝም ለኢትዮጵያ የሚያበረክተው ጥቅም ላይ ሰፋ ያለ ውይይት በክፍል ውስጥ ማድረግ፡፡ |
| • ከኢኮኖሚ እድገት ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር በአካባቢያችን በሚገኙ እጽዋትና የዱር እንስሳት ላይ | 3.3. **ከኢኮኖሚ እድገት ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር እፅዋትና የዱር እንስሳት ላይ የሚያመጣው አሉታዊ ተፅዕኖ** *(4 ክ/ጊዜ)* | • በጥቁር ሰሌዳው ሶስት ርዕሶችን ማለትም የደን መጥፋት፣ የዱር እንስሳት መሰደድ እና የደን መመናመን መፃፍ፡፡ በመቀጠል ተማሪዎች ስለነዚህ የሚያውቁትን እንዲናገሩ ማበረታታት፡፡ በመጨረሻም |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| የሚያመጣውን አሉታዊ ተፅዕኖ ተንተነው ያስረዳሉ፡፡ | • የፅፅዋት መመናመን<br>• የዱር እንስሳት መሰደድ<br>• የደን ሀብት መመናመን | ከላይ በሶስት ርዕስ የጠቀስናቸው ችግሮች እንዳይከሰቱ ምን ማድረግ እንደሚችሉና እንደሚገባ አጭር ፅሑፍ እንዲፅፉ ማበረታታት፡፡ |
| • የዱር እንስሳትንና እፅዋትን እንዴት መንከባከብ እንደሚችሉ ይገነዘባሉ፡፡<br><br>• የዱር እንስሳትንና እፅዋን የመንከባከቢያ ዘዴዎችን ይገልጻሉ፡፡<br>• ከላይ የጠቀስናቸውን ዘዴዎች ከአካባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማዛመድ የዱር እንስሳትንና እፅዋትን ለመጠበቅ በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ በንቃት ይሣተፋሉ፡፡<br>• በአፍሪካ ቀንድና በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ የዱርት የእንስሳት ለሚሰጡት ጥቅም አድናቆታቸውን ይገልጻሉ፡፡ | **3.4. የተፈጥሮ እጽዋትና የዱር እንስሳት እንክብካቤ**<br>*(7 ክፍለ ጊዜ)*<br>• ድነና፣ መልሶ ድነና፣ የደን ቃጠሎን መቆጣጠር *(3 ክፍለ ጊዜ)*<br>• ሕገ ወጥ የሆነ አደንን ማስቆም *(1 ክፍለ ጊዜ)*<br><br>• የኢትዮጵያ ብሔራዊ ፓርኮችና ተንከባካቢ ተቋማት *(3 ክፍለ ጊዜ)* | • በአካባቢያቸው በቅርቡ በደን የተሸፈነ አዲስ አካባቢና መልሶ እንዲያንሰራራ የተደረገ የደን ስፍራ አውቀው በዛ ላይ ውይይት እንዲያደርጉ ማድረግ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በአካባቢያቸው በሚደረግ የዛፍ ተከላ፣ የብሔራዊ ፓርክና እንክብካቤ እንዲሁም የደን ቃጠሎን የመከላከል ዘመቻ ላይ እንዴት መሳተፍ እንደሚችሉ በክፍል ውስጥ ሰፊ ውይይት እንዲያደርጉ ማድረግ፡፡<br>• አንድ ብሔራዊ የደን ፓርክን በተመለከተ የዳሰሳ (ውስን) ጥናት ማድረግ<br>• **የሚና ጨዋታ፡-** በድራማ መልክ የተወሰኑ ተማሪዎች አንድ በብሔራዊ ደረጃ እንዳይታደን የተከላከለን እንስሳ እንደ አዳኝ ሆነው የተወሰኑ ተማሪዎች |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| | | አዳኞቹን ስራቸው ትክክል አለመሆናቸውን በማሳመን እንስሳውን እንዳይገድሉ የሚያሳይ ክርክር ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እንዲያሳዩ ማድረግ፡፡ በመጨረሻም ቡድን እንዲፈጥሩ በማድረግ በዱር እንስሳት ላይ የሚደረግ አደን ጠቀሜታና ጉዳት ላይ ክርክር እንዲገጥሙ ማድረግ፡፡<br>• ተማሪዎች ህገወጥ አደንና የደን ውድመት የሚቃወም ስእላዊ መግለጫ (ፖስተሮችን) በመዘጋጀት በአካባቢያቸው ይለጥፉ፡፡<br>• ተማሪዎች የኢትዮጵያን ካርታ በደብተራቸው ላይ ስለው በካርታው ላይ የሀገሪቷ ዋና ዋና ብሔራዊ ፓርኮችን መገኛቸውን በትክክል እንዲያስቀምጡና ለዱር እንስሳት የተፈጥሮ መጠለያቸውን እንዴት አመቺ ማድረግ እንደሚቻል እንዲወያዩ ማበረታታት<br>• በሀገርና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚንቀሳቀሱ ለተፈጥሮ አካባቢና |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| | | እንስሳት ጥበቃ እንዲደረግ የሚተጉ ድርጅቶችን (የኢትዮጵያ የዱር እንሰሣት ማህበር፣ የተባበሩት መንግሥታት የአካባቢ ጥበቃ) መጥቀስ፡፡<br>• **የሚና ጨዋታ፡-**በድራማ መልክ አራት በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ሁለቱ የደን የዱር እንሰሣት መታደን አለባቸው ብለው የሚያምኑና ብርቅዬ የዱር እንስሳትን አድነው የሚፈልጉ ሁለት ደግሞ ይህንን የሚቃወሙ ናቸው፡፡ ከተማሪዎች መካከል አራቱን ሰዎች የሚወክሉ ተማሪዎች በመምረጥ ክርክር እንዲያደርጉ ማድረግ በመጨረሻም ተማሪዎች በሚኖሩበት አካባቢ የዱር እንስሳትን እንዴት መንከባከብ እንደሚችሉና እንደሚገባቸው ውይይት ማድረግ፡፡ የአካባቢ ጥበቃ ክበባትን እንዲያቋቁሙ ወይነንም በተቋቋሙ ክበባት ውስጥ በአባልነት መሣተፍ እንዲችሉ ያበረቷቷቸው፡፡ |

## ምዘናና ግምገማ

መምህራን ከምእራፍ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን የተማሪዎች ተግባራት ተከታታይነት ባለው መልኩ ሊመዘኑና ሊገመገሙ እንዲሁም ያላቸውን ጠንካራና ደካማ ጎን ለይተው ሊያወጡ ይገባል፡፡ ለዚህ ተከታታይ ምዘናና ግምገማ መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ ከምእንፍ ይዘቶች አንፃር አላማዎች ሊሆኑ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመማር ማስተማር ሂደቱ ከትምህርቱ ይዘቶችጋር አብረው የተዘረዘሩት አላማዎች ከግብ ለመድረሳቸው ሊያንፀባርቅ በሚችል መልኩ ምዘናና ግምገማ ሊካሄድ ይገባል፡፡

ሀ. የምእራፍን ይዘቶች ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች ቢያንስ የሚከተሉትን ባህሪያት /ለውጦች/ ሊያሳዩ ይገባል፡፡

- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ ዋና ዋና እፅዋትን መለየት
- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ ዋና ዋና የዱር እንስሳትን ስም መጥቀስ
- በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ ብርቅዬ የዱር እንስሳትን ለይተው መገንዘብ
- የዱር እንስሳትና እፅዋት ለኢትዮጵያና አፍሪካ ቀንድ የሚሰጡትን ጥቅም ማብራራት
- የሕዝብ ቁጥር መጨመር በእፅዋትና በዱር እንስሳት ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተፅዕኖ መተንተን፡፡
- የዱር እንስሳትንና እፅዋትን የእንክብካቤ መንገዶችን መዘርዘር፡፡
- የዱር እንስሳትና እፅዋትን ለመንከባከብና ለመጠበቅ ተነሳሽነትን ማሳየት፡፡

ለ. በ "ሀ" ስር ከተዘረዘሩት የብቃት መለኪያዎች መለኪያ ያሳዩ ተማሪዎች ከተገኙ መምህራንና የሚመለከተው አካል ለነዚህ ተማሪዎች ማበረታቻ ይህንን ብቃታቸውን ይዘው እንዲዘልቁ ተገቢው ማበረታቻ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

ሐ. በ "ሀ" ስር ከተዘረዘሩት ያነሰ የብቃት መለኪያዎች የሚያሳዩ ተማሪዎች ከተገኙ መምህራን ለእነዚህ ተማሪዎች የተለየ ድጋፍ በማድረግ ከጓደኞቻቸው ጋር ተመሳሳይነት ያለው የትምህርት ብቃት እንዲኖራቸው ሊረዷቸው ይገባል፡፡ ለምሳሌ የክፍለ ትምህርቱን ይዘቶች ተጨማሪ ሰዓታት በመውሰድ መከለስ፣ ከጎበዝ ተማሪዎች ጋር የሚያጠኑበትን መንገድ ማመቻቸት፣ ከቤተሰቦቻቸው ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር ያለባቸውን ችግር ለይቶ በማወቅ የተማሪዎቹን ችግር ሊያቃልል የሚችል እርምጃ መውሰድ፡፡

መ. በተጨማሪም ከዚህ ሌላ ለየት ያለ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ የተለየ ትኩረት መስጠት፡፡ ለምሳሌ አካል ጉዳተኞች ለነዚህ ተማሪዎች በግምገማና ምዘና ወቅት ተገቢ የሆነ ድጋፍ ማድረግ፡፡

## ምዕራፍ አራት፦ ስነ ሕዝብ ጉዳዮች *(16 ክፍለ ጊዜያት)*

***አጠቃላይ የሚጠበቅ ውጤት፦*** ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፦

- በኢትዮጵያ ለኤች አይ ቪ /ኤድስ የሚያጋልጡ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና የሚያመጡትን አሉታዊ ተፅዕኖ ያብራራሉ፡፡
- ከኢኮኖሚ እድገት ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር ያለውን ተፅዕኖ ይተነትናሉ፡፡
- የመልካም አስተዳደርና የሕፃናት መብት መከበር መገለጫዎችን ይገልፃሉ፡፡
- የአደጋ መከላከያና የጥንቃቄ መርሆዎችን ይገነዘባሉ፡፡

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦*<br>• ለኤች አይ ቪ /ኤድስ የሚያጋልጡ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ላይ ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡<br>• ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ለምሳሌ ጠለፋ፣ የሴት ልጅ ግርዛት እና ንቅሳት የሚያመጡትን አሉታዊ ተፅዕኖ ተንትነው ያስረዳሉ፡፡ | ***4. ስነ ሕዝብ ጉዳዮች***<br>**4.1. ሕዝብ ነክ ጉዳዮች**<br>*(4 ክፍለ ጊዜ)*<br>• ኤች አይ ቪ ኤድስና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች | • በአካባቢያቸው ስለሚተገበሩ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ረዘም ላለ ጊዜ እንዲወያዩ ማድረግ<br>• ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዴት ለኤች አይ ቪ ኤድስ ሊያጋልጡ እንደሚችሉ ተማሪዎች ለሁለት ተከፋለው እንዲጣራ ክርክር እንዲገጥሙ ማድረግ<br>• በጉዳና ተዳዳሪነት ላይ አንድ ውሱን ጥናት ማቅረብ ይህንን ውስን ጥናት እንደ መነሻ በመውሰድ ተማሪዎች በአካካበያቸው የሚያውቋቸው ያላሳዳጊ የቀሩና የጎዳና ሕይወት የሚመሩ ካሉ ምሳሌ እንዲጠቀሙ ማድረግ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • ኤች አይ ቪ ኤድስ ለጎዳና ተዳዳሪነትና ያለአሳዳጊ መቅረት መንስኤ እንዴት ሊሆን እንደሚችል በመገንዘብ ያብራራሉ፡፡ | • ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና የኤች አይ ቪ ኤድስ መስፋፋት<br>• የኤች አይ ቪ ኤድስ መስፋፋት መንስኤና የሚያስከትለው ተጽእኖ ለጎዳና ተዳዳሪነት መጋለጥ ወላጅ ያጡ | • **የሚና ጨዋታ፦**የጎዳና ሕይወት እንዴት ለኤች አይ ቪ/ኤድስ ሊያጋልጥ እንደሚችል ተማሪዎች በድራማ መልክ እንዲያሳዩ ማበረታታት |
| • የኢትዮጵያ የሕዝብ ቁጥር እድገት ለእርሻ መሬትና ለማህበራዊ ግልጋሎቶች እጥረት እንዴት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ይገልጻሉ፡፡ | 4.2. **ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገትና አሉታዊ ተፅዕኖዎቹ**<br>*(4 ክፍለ ጊዜ)*<br>• የማህበራዊ ግልጋሎቶች እጥረት<br>• የእርሻ መሬት እጥረት | • አሁን እየተማሩ ባሉበት ት/ቤት የየክፍሉ ተማሪ ብዛትና አጠቃላይ የትምህርት ቤቱ ዓመታዊ ቅበላ ከዛሬ 10 ዓመት በፊት ከነበረው አጠቃላይ የቅበላ አቅም ጋር ተማሪዎች እንዲያነፃፅሩ ማድረግ፡፡<br>• በመቀጠልም ልዩነቱን ካወጡ በኋላ በት/ቤቱ ውስጥ ያለው የቅበላ አቅም ምን ዓይነት ተፅዕኖ ሊኖረው እንደሚችል ተማሪዎች እንዲወያዩ ማድረግ፡፡<br>• ለሕዝብ ቁጥር እድገት ምክንያት ተማሪዎች ቤተሰቦቻቸውንና በአካባቢያቸው የሚገኙ ሰዎችን ቃለ መጠይቅ በማድረግ በአካባቢያቸው የማህበራዊ ግልጋሎቶች እጥረት እንዴት ሊያጋጥም እንደሚችል እንዲያጠኑና |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| | | የጥናታቸውን ውጤት ለክፍል ጓደኞቻቸው ዘገባ እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡<br>• የሕዝብ ቁጥር መጨመር በግጦሽና በእርሻ መሬት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዴት ሊያስከትል ሊያመጣ እንደሚችል ተማሪዎችን መጠየቅ በመቀጠልም ተማሪዎች የሚጠቅሷቸውን አሉታዊ ተፅዕኖዎች ጥቁር ሰሌዳው ላይ መዘርዘር<br>• በመጨረሻም ተማሪዎች ከዚህ ጋር በተያያዘ አንድ አካባቢን በተመለከተ አጠር ያለ ዘገባ እንዲያቀርቡ መርዳት፡፡ |
| • የትምህርት ቤታቸውን ሕግጋት ደንቦችንና አላማዎች መገንዘብ፡፡<br>• የመልካም አስተዳደር መገለጫዎች ማብራራት<br>• የግልፀኝነት፣ ተጠያቂነት፣ የሀላፊነትና ከሙስና የፀዳ አሰራር ትርጉምን መግለፅ፡፡ | 4.3. **መልካም አስተዳደር፣ የሕፃናት መብትና ደህንነት**<br>4.3.1. **መልካም አስተዳደር** *(2 ክፍለ ጊዜ)*<br>• የመልካም አስተዳደር መገለጫዎች (ተጠያቂነት፣ ግልፀኝነት፣ የሀላፊነት ስሜት፣ ሕግን ማክበር፣ ከሙስና የፀዳ አሰራር) | • የትምህርት ቤቶች አስተዳደር በርዕሰ መምህሩ፣ በመምህራንና በተማሪዎች እንዴት እንደሚዋቀር ውይይት ማድረግ፡፡<br>• ተማሪዎች የትምህርት ቤታቸውን የአስተዳደር መዋቅር ስዕላዊ መግለጫ ስለው እንዲያሳዩ ማድረግ ጥቁር ሰሌዳውን ለሁለት ዓምድ መክፈል፡፡ አንደኛው የሰሌዳው አምድ ላይ መብት የሚለውን መፃፍ ሁለተኛው ላይ ደግሞ ግዴታ የሚለውን መፃፍ በሁለቱም አምድ ስር ተማሪዎች መብትና ግዴታ የሚሏቸውን እንዲዘረዝሩ ማድረግ፡፡ |

| **የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች** | **ይዘቶች** | **ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች** |
|---|---|---|
| | | • ተማሪዎች የትምህርት ቤታቸው ጥበቃ መቼና በምን አይነት ሁኔታዎች ላይ እንደሚያስፈልጋቸውና ትምህርት ቤታቸው እንዴት ሊረዷቸው እንደሚችል እንዲገልፁ ማድረግ፡፡ በዚህ ላይም አጭር ውሱን ማድረግ፡፡<br>• በአካባቢያቸው ያሉ ተቋማት እንዴት እንደተደራጁ /እንደተዋቀሩ/ ተማሪዎች እንዲወያዩ ማድረግ፡፡ ለምሳሌ ቀበሌዎች፣ ወረዳ ጽ/ቤቶች እንዲሁም የፖሊስ ጽ/ቤት ሚና በሚለው ላይ ሀሳባቸውን እንዲገልፁ መርዳት፡፡ ለዚህም ማጠናከሪያ ይሆን ዘንድ ውሱን ጥናት እንደሚያካሂዱ  የዳሰሳ ጥናት መጠቀም፡፡ |
| • የተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ ሳይንስና የባህል ድርጅት ለሕፃናት መብት ጥበቃ እንደሚያደርግ መረዳት<br>• መሰረታዊ መብታቸውን ማወቅ፡፡ | **4.3.2. የሕፃናት መብት**<br>*(3 ክ/ ጊዜ)*<br>• የህጻናት መብት (የማንነትና የመጠሪያ ስም መያዝ፣ የመማር መብት፣ ከአደጋ በሕግ የመጠበቅ መብት) | • ስለ ሕፃናት መብት አለም አቀፍ ስምምነት እንዳለ ለተማሪዎች መንገር፡፡ በጥቁር ሰሌዳው በግራ አምድ ላይ መዘርዘር ሊኖራቸው በሚገቡ መብቶች ላይ ውይይት እንዲያደርጉ ማበረታታት ለውይይት የሚመቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፡፡<br>• በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል  ድርጅት ላይ የተዘረዘሩ የሕፃናት መሰረታዊ መብቶች ላይ ማብራሪያ መስጠት |

| **የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች** | **ይዘቶች** | **ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች** |
|---|---|---|
| | | • በመቀጠል በጥቁር ሰሌዳው የቀኝ አምድ ላይ ለተማሪዎች ግዴታ የሚሆን አንድ ሀሳብ መፃፍ ለምሳሌ የትምህርት ቤቱን ሕግና ደንቦችን ማክበር፡፡በተጨማሪም ተማሪዎች ሌሎች ምሳሌዎችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ፡፡<br>• አንድ አደጋ ስለደረሰበት ሕፃን አጭር ውሱን ጥናት ማድረግ<br>• ሕፃናት በቤታቸውና በአካባቢያቸው ሊገጥማቸው የሚችሉ አደጋዎችና መፍትሔዎቻቸው ላይ እንዲወያዩ ማበረታታት፡፡ |
| • በአካባቢያቸው ሊከሰቱ የሚችሉ ከባድ አደጋዎችን መለየት<br>• የጥንቃቄ ደንቦችን ዕፊው ማብራራት<br>• በአካባቢያቸው የሚገኙ ሰዎች እራሳቸውን እንዴት ከአደጋ መከላከል እንደሚችሉ የምክር አገልግሎት መስጠት፡፡ | 4.3.3. **ድንገተኛ አደጋና ደህንነት** *(3 ክ/ ጊዜ)*<br>• የመኪና አደጋ<br>• የእንስሳት ትንኮሳ<br>• ድንገተኛ ጎርፍና የእሣት አደጋ | • ተማሪዎች ከዚህ በፊት ስላዩዋቸው የመኪና አደጋዎች ካሉ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ማድረግ፡፡ በተጨማሪም እንዲህ አይነት አደጋ እንዳይከሰት ምን ዓይነት ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት ከተማሪዎች እየጠየቁ ጥቁር ሰሌዳ ላይ መዘርዘር፡፡ በመቀጠልም የትራፊክ ደህንነትን የሚያሳይ ሰንጠረዥ በቡድን ሰርተው ትምህርት ቤታቸው ግድግዳ ላይ እንዲለጥፉ ማበረታት፡፡<br>• ስለ ጎርፍና እሳት አደጋ ተማሪዎች እንዲወያዩ ማድረግ፡፡ በቡድን ሆነው ጎርፉንና የእሳት |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| | | አደጋን እንዴት መከላከል እደሚቻል እንዲወያዩ መርዳት<br>• በመጨረሻም የተወያዩትን በወረቀት ዘገባ እንዲያቀርቡ ማበረታታት |

## ምዘናና ግምገማ

መምህራን ከምእራፎ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን የተማሪዎች ተግባራት ተከታታይነት ባለው መልኩ ሊመዘኑና ሊገመግሙ እንዲሁም ያላቸውን ጠንካራና ደካማ ጎን አንጥረው ሊያወጡ ይገባል፡፡ ለዚህ ተከታታይ ምዘናና ግምገማ መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ ከምእራፎ ይዘቶች ጋር የተዘረዘሩት ዝርዝር አላማዎች ሊሆኑ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመማር ማስተማር ሂደቱ ከትምህርት ይዘቶች ጋር አብረው የተዘረዘሩት አላማዎች ከግብ መድረሳቸውን ሊያንፀባርቅ በሚችል መልኩ ማሳካት አለ ማሳካቱን ሊያሳይ የሚችል ምዘናና ግምገማ ሊካሄድ ይገባል፡፡

ሀ. የምእራፉን ይዘቶች ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች ቢያንስ የሚከተሉትን ባህሪያት /ለውጦች/ ሊያሳይ ይገባል፡፡

- ለኤች አይ ቪ ኤድስ የሚጋለጡ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ላይ ማብራሪያ መስጠት
- ኤች አይ ቪ ኤድስ ለጎዳና ተዳዳሪነትና ወላጅን ለማጣት  መንስኤ ሊሆን እንደሚችል ማብራራት
- በኢትዮጵያ የሕዝብ ቁጥር እድገት ለእርሻ መሬትና ለማህበራዊ ግልጋሎቶች እጥረት እንዴት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ማስረዳት፡፡
- የመልካም አስተዳደር መገለጫዎችን መገንዘብ
- በአካባቢያቸው የሚከሰቱ አደጋዎችንና ሊወሰዱ የሚገቡ ጥንቃቄዎችን መለየት
- በአካባቢያቸው ስለሚከሰቱ አደጋዎችና የጥንቃቄ መንገዶች እውቀት መጨበጥ፡፡

ለ. በ "ሀ" ስር ከተዘረዘሩት ብቃቶች ያለፈ ብቃትና ባህሪ ያሳዩ ተማሪዎች ከተገኙ መምህራንና የሚመለከተው አካል ለነዚህ ተማሪዎች ማበረታቻ ሊያዘጋጅ ይገባል ለምሳሌ ሽልማት በተጨማሪም እነዚህ ተማሪዎች ይህንን ብቃታቸውን ይዘው እንዲዘልቁ ተገቢው ማበረታቻ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

ሐ. በ "ሀ" ስር ከተዘረዘሩት ያነሰ ብቃት የሚያሳዩ ተማሪዎች ከተገኙ መምህራን ለእነዚህ ተማሪዎች የተለየ ድጋፍ በማድረግ ከጓደኞቻቸው ጋር ተመሳሳይነት ያለው የትምህርት ብቃት እንዲኖራቸው ሊረዷቸው ይገባል፡፡ ለምሳሌ የክፍለ ትምህርቱን ይዘቶች ተጨማሪ ሰዓታት በመውሰድ መከለስ፣ ከጎበዝ ተማሪዎች ጋር የሚያጠኑበትን መንገድ ማመቻቸት፣ ከቤተሰቦቻቸው ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር ያለባቸውን ችግር ለይቶ በማወቅ የተማሪዎቹን ችግር ሊያቃለል የሚችል እርምጃ መውሰድ፡፡

መ. በተጨማሪም ከዚህ ሌላ ለየት ያለ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ካሉ የተለየ ትኩረት መስጠት፡፡ ለምሳሌ አካል ጉዳተኞች ከነዚህ ተማሪዎች በግምገማና ምዘና ወቅት ተገቢ የሆነ ድጋፍ ማድረግ፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## የኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት መገኛና የሕዝቦች አሠፋፈር

**ስምዕራፉ የተመደበው ጠቅላላ ክፍለ ጊዜ:-** 23

***የምዕራፉ ትምህርት ሲጠናቀቅ የሚጠበቁ ውጤቶች***

**ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ይዘቶች ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

- የአፍሪካ ቀንድ ሀገራትን ስምና አንፃራዊ መገኛቸውን ይገልፃሉ፡፡
- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ የነበሩ ጥንታዊ መንግሥታትን ይጠቅሳሉ፡፡
- በኢትዮጵያ ውስጥ የተከናወኑ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ክንዋኔዎችን /ሰኬቶችን/ ያደንቃሉ፡፡
- የዘመናዊነት ዋና ዋና ክንዋኔዎችን ያደንቃሉ፡፡
- በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጥረው የነበሩ ጥንታዊ መንግሥታትና ዋና ዋና ስኬታማ ክንዋኔዎቻቸውን ያብራራሉ፡፡
- በከፍተኛና ዝቅተኛ ስፍራዎች በሚኖሩ የኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል የአሰፋፈር፣ የባህልና የአኗኗር ዘይቤ ልዩነት መንስኤዎችን ይለያሉ፡፡

**ርዕሶች**

- የአፍሪካ ቀንድ ሀገራትና መገኛቸው
- የኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ሕዝቦች ታሪክና አሰፋፈራቸው
- አንድነትና ዘመናዊነት
- የሕዝብ አሰፋፈርና የባሕል ልዩነት እንዲፈጠር ጉልህ ሚና ያላቸው ምክንያቶች

## 1.1 የአፍሪካ ቀንድ ሀገራትና መገኛቸው

*የተመደበው ክፍለ ጊዜ 4*

### ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

*ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦*

- የአፍሪካ ቀንድ መገኛን ይገልጻሉ፡፡
- ስላጤ መገኛን (ሰሜን፣ ደቡብ ምዕራብ ምስራቅ) በመጠቀም የአፍሪካ ቀንድ መገኛን ይገልፃሉ፡፡
- በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ ሀገራትን ስሞች ይጠቅሣሉ፡፡
- የአፍሪካን ካርታ በመጠቀም የኢትዮጵያን አንፃራዊ መገኛን ያሣያሉ፡፡
- ሰላጤ (cardinal) መገኛን (ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምዕራብና ምስራቅ አቅጣጫዎችን) በመጠቀም የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ዋና ዋና ከተሞችን ይገልጻሉ፡፡

### ለ. ይዘቶች

- የአፍሪካ ቀንድ አንፃራዊ መገኛ
- የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት

### ሐ. የትምህርቱ ጭብጥ

የአፍሪካ ቀንድ የሚገኘው በምሥራቅ አፍሪካ ነው፡፡ ይህ ሥፍራ እስከ ደቡብ አረብ ባህር ይዘልቃል፡፡ የአፍሪካ ቀንድ አራት ሀገሮችን ያካትታል፡፡ እነርሱም ኢትዮጵያ፣ ጅቡቲ፣ ሶማሊያና ኤርትራ ናቸው፡፡ ሱዳን የአፍሪካን ቀንድ በስተምዕራብ ሲያዋስን ኬንያ ደግሞ ከአፍሪካ ቀንድ በስተደቡብ ይገኛል፡፡

### መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ

1. *የተጠቆሙ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች*
    - የአፍሪካ ተፈጥሮአዊና ፓለቲካዊ ካርታ
    - ንድፍ ካርታዎች

## 2. የተጠቆሙ የማስተማር ሥነ ዘዴዎች

- የቡድን ውይይት
- ጥያቄና መልስ
- ሠርቶ ማሳየት

## 3. ቅድመ ዝግጅት

- የሚነበቡ ጽሑፎችን አስቀድሞ ለተማሪዎች መስጠት፡፡
- የማጣቀሻ መጻሕፍትና መርጃ መሣሪያዎችን ለተማሪዎች እይታ በሚያመች ቦታ ማስቀመጥ፡፡
- የየእለቱን የትምህርት እቅዶች ማዘጋጀት፡፡

## ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት

### 1. መግቢያ

ለተማሪዎች ሊቀርቡ የሚችሉ ጥያቄዎች

- የአፍሪካ ቀንድ የሚባለው ሥፍራ ይህንን ስያሜ ያገኘው ለምን ይመስላችኋል?
- በአፍሪካ ቀንድ ከሚገኙት ሀገሮች ሁለቱን ጥቀሱ፡፡

### 2. የትምህርቱ አቀራረብ

የአፍሪካን ንድፍ ካርታ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ሳሉና ለተማሪዎች የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች አቅርቡ፡፡

- የአፍሪካን ቀንድ አንፃራዊ መገኛ አሳዩ፡፡
- የአፍሪካ ቀንድ ሀገራትን አመልክቱ፡፡
- የአፍሪካ ቀንድ ጎረቤት ሀገራትን ለይታችሁ በካርታው ላይ አስፍሩ፡፡
- ኢትዮጵያና አዲስ አበባን በካርታው ላይ በማመልከት በአፍሪካ ቀንድ ጠረፍ ላይ የሚገኙ ባሕሮችና ውቅያኖሶችን ሰይሙ፡፡

ተማሪዎች የኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ መስመሮች ካርታ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ካርታ በመጠቀም የአፍሪካን ቀንድ ዋና ዋና ከተሞች እንዲያሳዩና ከተሞቹም አንዱ ከሌላው በየት አቅጣጫ እንደሚገኙ እንዲገልጹ ጥያቄ አቅርቡላቸው፡፡

### ረ. ግምገማ ክትትል

#### *1. ግምገማ*

የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ለተማሪዎች አቅርቡ

- የአፍሪካ ቀንድ መገኛ የት ነው?
- የአፍሪካ ቀንድ ሀገራትን ስም ዘርዝሩ፡፡
- ከአፍሪካ ቀንድ ሀገራት በስፋት ትንሿ የትኛዋ ሀገር ናት?
- የአፍሪካ ቀንድ አጎራባች ሀገራትን ጻፉ፡፡
- የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ዋና ከተሞች እነማን ናቸው?

#### *2. ክትትል*

ተማሪዎች የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወናቸውን ይከታተሉ፡-

- የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ከተሞች፣ አጎራባች ሀገራት፣ ባሕሮችና ውቅያኖሶችን የሚያሳይ የአፍሪካ ቀንድ ንድፍ ካርታ /sketch map/ እንዲስሉ፡፡
- ከሚከተሉት ስለአንዱ በተመጠኑና በተመረጡ ቃላት አጭር መግለጫ እንዲጽፉ፡፡
  - የአፍሪካ ቀንድ አቀማመጥ
  - የአፍሪካ ቀንድ እስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ

## 1.2. የኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ሕዝቦች ታሪክና አሰፋፈራቸው

***የተመደበው ክፍለ ጊዜ:- 11***

### ሀ.ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ የሚኙትን ዋና ዋና ቅሪተ አካልና ቅሪተ ቁስ መገኛ ስፍራዎች ይለያሉ፡፡

- የቅሪተ አካላት ግኝቶችን የጊዜ ቅደም ተከተልና ጥቅማቸውን ለይተው ይናገራሉ፡፡
- በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ ዋና ዋና ሃይማኖቶች አመጣጥና ሽፋንን ይገልጻሉ፡፡
- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ ያለው የሃይማኖት መቻቻል የረጅም ጊዜ ታሪክ ያለው መሆኑን በመገንዘብ አድናቆቸታውን ይገልጻሉ፡፡
- ኢትዮጵያ የብዙ እምነት ተከታይ ሀገር መሆኗን መገንዘባቸውን ይገልፃሉ፡፡
- ለጥንታዊ የኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ መንግሥታት ያላቸውን አድናቆት ያሣያሉ፡፡
- ጥንታዊ የኢትዮጵያ መንግሥታት ታሪካዊና ፓለቲካዊ ክንዋኔዎችን ይለያሉ፡፡

## ሰ. ይዘቶች

- የሰው ልጅ ዘር መገኛና የቅሪተ አካልና ቅሪተ ቁስ መገኛዎች በኢትዮጵያና በኬንያ
- የክርስትናና የእስልምና ሀይማኖቶች አመጣጥ በአፍሪካ ቀንድ ሀገራት
- ጥንታዊ የኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ መንግሥታት
- ታሪካዊና ፖለቲካዊ ክንዋኔዎች

## ሐ. የትምህርቱ ጭብጥ

የመጀመሪያው የሰው ልጅ መገኛ ሥፍራ በአፍሪካ ቀንድ በተለይም በኢትዮጵያ ነው፡፡ በእነዚህም ስፍራዎች የቀድሞ ሰዎች ቅሪተ አካልና የድንጋይ መሳሪያዎቻቸው ቅሬቶች ተገኝተዋል፡፡ የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶች ወደ ኢትዮጵያ በመጀመሪያ ገብተዋል፡፡ የእነዚህም ሃይማኖቶች ተከታዮች ለምዕተ ዓመታት በሰላም አብረው ኖረዋል፡፡

በኢትዮጵያ በርካታ ጥንታዊ መንግሥታት ነበሩ። እነርሱም ፑንት፣ ዳኣማት፣ አክሱም፣ ዛግዌ፣ የሰለሞናዊ መንግሥት፣ የሙስሊም ሡልጣኔቶች፣ ዳሞት፣ ከፋ፣ ወላይታና የሐረር ኤምሬት ናቸው። እነዚህ ጥንታዊ የኢትዮጵያ መንግሥታት በርካታ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ስኬቶች ነበሯቸው። እነዚህ መንግሥታት ካከናወኗቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ በማበርከት ላይ ይገኛሉ።

**መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ**

*1. የተጠቀሙ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች*

- ፎቶግራፎች ወይም ምስሎች
- የአፍሪካ ቀንድ ካርታዎች

*2. የተጠቀሙ የማስተማር ሥነ ዘዴዎች*

- የቡድን ውይይት
- የአነስተኛ ቡድን ውይይት
- የመስክ ጉብኝትና ዘገባ ማጠናቀር
- ውስን ጥናት

*3. ቅድመ ዝግጅት*

- አግባብነት ያላቸው ካርታዎች፣ ፎቶግራፎችና ምስሎች ክፍል ውስጥ አስቀምጡ
- ለውይይት የሚሆኑና በሚገባ የተጠኑ መልመጃዎች ለውይይት አዘጋጁ

**ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት**

*1. መግቢያ*

ለተማሪዎች ሊቀርቡ የሚችሉ ጥያቄዎች

- በኢትዮጵያ የሚገኙ ዋና ዋና ሃይማኖቶች የትኞቹ ናቸው?
- ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው መቼ ነበር?
- እስልምና ወደ ኢትዮጵያ የገባው መቼ ነበር?

- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ ከነበሩ ጥንታዊ መንግሥታት መካከል ጥቂቶቹን ጥቀሱ፡፡
- ጥንታዊ መንግሥታት የነበሩበት አካባቢ የት ነበር?
- የዛግዌ መንግሥት መቀመጫ የት ነበር?
- የሙስሊም ሡልጣኔቶች መቀመጫ የት ነበር?

## 2. የትምህርቱ አቀራረብ

- ተማሪዎች የሚያውቁአቸውን ሉሲንና ሰላምን የመሳሰሉ ቅሪተ አካላት እንዲናገሩ ማበረታት፡፡
- ዋና ዋናዎቹን ቅሪተ አካላት በእድሜ ቅደም ተከተል ጽፈው በቡድን ከተወያዩ በኂላ ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡
- ተማሪዎች በኢትዮጵያ ስለሚገኙ ዋና ዋና ሃይማኖቶች በቡድን ተወያይተው ዘገባ በማጠናቀር አንኳር ነጥቦችን ለክፍል ውይይት እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡
- ተማሪዎች የኢትዮጵያን ካርታ ተጠቅመው በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጠሩ ዋና ዋና መንግሥታት መገኛዎች እንዲያሳዩ ማድረግ
- በዚህም ውይይታቸው ልዩነትን፣ መቻቻልን፣ ተከባብሮ በአንድነት መኖር ለአንድ ሀገር ሰላም መሠረት መሆኑን እንዲረዱ ማገዝ፡፡
- ሶስት ሶስት ተማሪዎች የሚይዙ ቡድኖች በመፍጠር የጥንት መንግሥታት በኢትዮጵያ የት የት እንደተፈጠሩ በወረቀት ላይ ጽፈው በቡድን ተወካያቸው አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡ ለዚህ ያመች ዘንድ የኢትዮጵያ ካርታን ለተማሪዎች ሁሉ በሚታይ መልኩ በጥቁር ሰሌዳው ላይ በተዘጋጀው መስቀያ ላይ መስቀል፡፡
- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ ስለተፈጠሩ የጥንት መንግሥታት አጭር ማብራሪያ መስጠት፡፡
- ተማሪዎች አክሱማውያን፣ ጎንደራዊያን፣ አገዎች፣ ኮንሶዎች፣ ሀረሪዎችና የገዳ ስርዓት ተከታይ የሆኑት ኦሮሞዎችና ሲዳማዎች ያከናወኗቸውን ዋና ዋና ክንዋኔዎችን በተመለከተ

ሪፖርት ፅፈው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ማድረግ። ይህ ተግባር በቡድን ቢሰራ ተማሪዎች ሀሳብ ለሀሳብ እንዲለዋወጡ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል።

**ረ. ግምገማና ክትትል**

*1. ግምገማ*

ለተማሪዎች ሊቀርቡ የሚችሉ የጥያቄ ዓይነቶች፡-

- በመጀመሪያ እስልምና ወደ ኢትዮጵያ የገባው እንዴት ነበር?
- የመጀመሪያዎቹ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ምን ተብሎ በሚጠራው የኢትዮጵያ ክፍል ሰፈሩ? ለምን?
- አክሱም የት ይገኛል?
- የጐንደር ግንብ ማን ገነባው?
- የገዳ ስርዓት ምንድን ነው?

*2. ክትትል*

- በኢትዮጵያ በክርስቲያኖችና በሙስሊሞች መካከል ተግባራዊ የሆነው በሰላም አብሮ የመኖር ባህል ስለአስገኘው ጥቅም አጭር ማስታወሻ እንዲያጠናቅሩ ንገሩአቸው።
- በኢትዮጵያ ከነበሩ ጥንታዊ መንግሥታት መካከል አንዱን መርጠው ታሪኩንና የነበራቸውን ስኬታማ ክንዋኔዎቹ ላይ አጭር የጽሑፍ ዘገባ እንዲያዘጋጁ ማድረግ።

## 1.3. አንድነትና ዘመናዊነት

***የተመደበው ክፍለ ጊዜ:- 5***

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

*ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ካጠናቀቁ በኋላ፡*

- የኢትዮጵያውያን ልበ ሙሉነትና አንድነት ለአድዋ ድል የነበረውን ጠቀሜታ ያብራራሉ።
- በኢትዮጵያ ዘመናዊ የአኗኗር ዘይቤ መጀመር ስላበረከተው አስተዋፅኦ ይወያያሉ።

## ሰ. ይዘቶች

- የኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድነት ለአድዋ ድል የነበረው ጠቀሜታ
- በኢትዮጵያ የዘመናዊነት አጀማመር

## ሐ. የትምህርቱ ጭብጥ

አሥራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት በኢትዮጵያ ሕዝቦች ታሪክ ውስጥ ሦስት አበይት ክንዋኔዎች የተፈፀሙበት ወቅት ነበር። አንደኛ በኢትዮጵያ የነበሩ በርካታ መንግሥታትና ሕዝቦች በአንድ ማዕከላዊ መስተዳድር ስር በመጠቃለል አንድነታቸውን የተጐናፀፉት በምዕተ ዓመቱ መገባደጃ ላይ ነበር። ሁለተኛ በዚሁ ምዕተ ዓመት ላይ በኢትዮጵያ ሕዝቦች ላይ የተቃጡ በርካታ የባዕዳን ወረራዎች መክቶ ከመመለስ ባሻገር ከኢጣሊያ የቅኝ ገዢዎች ወራሪ ሠራዊት ጋር በአድዋ ላይ በተደረገ ጦርነት ታላቅ ድል የተጐናፀፉበት ወቅት ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድነት ለአድዋ ድል ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው። በመጨረሻም በአሥራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት መገበዳጃና በሃያኛው ምዕተ ዓመት ላይ በርካታ ዘመናዊ ተቋማት ወደ ኢትዮጵያ የገቡበት ወቅት ነበር። የእነዚህ ተቋማት መግባት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ዘመናዊ አስተሳሰብና አሰራር እንዲስፋፋ በማድረጋቸው በሀገሪቱ ውስጥ ለማኅበራዊ ለውጦች መከሰት ከፍተኛ አስተዋፅዖ አበርክቷል።

## መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ

1. *የተጠቀሙ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች*
   - የኢትዮጵያ ታሪካዊ ካርታ
   - ምስሎችና ፎቶግራፎች
2. *የተጠቀሙ የማስተማር ሥነ ዘዴዎች*
   - የቡድን ውይይት
   - ጥቂት አባላት ያላቸው ቡድኖች ውይይት
   - የዘገባ ጥንቅር
   - አነስተኛ አውደ ርዕይ

### 3. ቅድመ ዝግጅት

- የሚነበቡ ርዕሶች በቤት ሥራ መልክ መስጠት
- በክፍል ውስጥ የሚነበቡ ምሳሌዎችና አነጋገሮች እንዲለዩ ማድረግ
- የተለያዩ መርጃ መሣሪያዎችን በማሰባሰብ ለተማሪዎች እይታ በሚያመች ሥፍራ ማስቀመጥ፡፡

## ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት

### 1. መግቢያ

ለተማሪዎች የሚቀርቡ የጥያቄ ዓይነቶች

- የኢትዮጵያ ሕዝቦች በጣሊያን ወራሪዎች ላይ ድል እንዲቀዳጁ የረዳቸው ምን ነበር?
- ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ ቀደምት ዘመናዊ ተቋማት መካከል የሶስቱን ስም ጥቀሱ?

### 2. የትምህርቱ አቀራረብ

- የኢትዮጵያ ሕዝቦች የጣሊያንን ወራሪ ኃይል አድዋ ላይ ለማሸነፍ እንዴት ሕብረት እንደፈጠሩ የሚያብራራ አጠር ያለ ፅሑፍ ፅፈው በዛ ላይ እንዲወያዩ ማመቻቸት፡፡ ይህንን በቡድን ማድረግ ጠቃሚ ነው፡፡ ለዚህ ማጠናከሪያ አንዳንድ ቡድን ግጥምና ዜማ እንዲያዘጋጅ ማበረታታት፡፡
- በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻና በ20ኛ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ ዘመናዊነት በኢትዮጵያ እንዴት እንደ ተጀመረ የሚያውቁትን ነገር በአጭሩ እንዲገልፁ ማበረ ታታት፡፡ ከዚህ በመቀጠል ተማሪዎች ዘመናዊነት በኢትዮጵያ መጀመሩ ያመጣውን ለውጥና ስኬት በቡድን ሆነው እንዲወያዩ ማድረግ፡፡ የተወያዩትን ሀሳብ በወረቀት ፅፈው ለክፍል ጓደኞቻቸው በተወካያቸው አማካይነት እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡

- በመጨረሻም ዘመናዊነት በኢትዮጵያ መጀመር ያለውን ጥቅምና ጉዳት በተመለከተ የሀሳብ ልዩነት ካለ ተማሪዎች እንዲከራከሩና መተማመን ላይ እንዲደረስ ማድረግ፡፡
- ዘመናዊነት በኢትዮጵያውያን አኗኗር ላይ ስለአሳደረው ተጽእኖ ማወያየት፡፡
- ተማሪዎች ስለዘመናዊነት ጉዳትና ጥቅም የሀሳብ ልዩነት ካለ በቡድን ተከፋፍለው እንዲከራከሩ ማድረግ፡፡

## ረ. ግምገማና ክትትል

### *1. ግምገማ*

ለተማሪዎች ሊቀርቡ የሚችሉ ጥያቄዎች

- አድዋ የት ይገኛል?
- ሌላ ስለ አድዋ ምን የምታውቁት አለ?
- ለዘመናዊ አስተሳሰብና አሰራር መስፋፋት ዋና መስሥኤ ምንድን ነው?

### *2. ክትትል*

- በ19ኛና በ20ኛ ምዕተ ዓመት ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ ዘመናዊ ተቋማት መካከል አንዱን መርጠው አጭር የጽሑፍ ዘገባ እንዲያዘጋጁ ማድረግ፡፡

## 1.4. የሕዝብ አሰፋፈርና የባህል ልዩነት እንዲፈጠር ጉልህ ሚና ያላቸው ምክንያቶች

***የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡- 3***

### ሀ.ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

*ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ካጠናቀቁ በኋላ፡-*

- በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል የሕዝብ አሰፋፈር ልዩነት እንዲፈጠር ጉልህ ሚና ያላቸውን ምክንያቶች ይጠቅሳሉ፡፡
- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ የሕዝብ አሰፋፈር ከአኗኗር ዘይቤ ጋር ያለውን ግንኙነት ያብራራሉ፡፡

- በኢትዮጵያ በከተማና በገጠር፣ በከፍተኛና ዝቅተኛ ስፍራዎች በሚኖሩ ሕዝቦች መካከል ያለውን የባህልና የአኗኗር ዘይቤ ተመሳሳይነትና ልዩነት ይገልጻሉ፡፡

**ሰ. ይዘቶች**

- የሕዝብ አሠፋፈር ልዩነት
- የባህልና የአኗኗር ዘይቤ ልዩነት
- የሕዝብ አሰፋፈር ሁኔታ በኢትዮጵያ

**ሐ. የትምህርቱ ጥብጥ**

የሕዝቦች አሰፋፈር ከቦታ ቦታ ይለያያል፡፡ ለአንድ አካባቢ ልማት ተስማሚ የአየር ንብረት፣ የተፈጥሮ ሀብትና የጎለበተ መከላከያ ዐቅም መኖር ወሳኝነት አላቸው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ነገሮችና ክስተቶች በዓለማችን የተለያዩ ክፍሎች በእኩል ደረጃ አልተሰራጩም፡፡ በዚህም የተነሳ የሕዝቦች አሰፋፈር፣ የአኗኗር ሁኔታና ባህል ከቦታ ቦታ ይለያያል፡፡

**መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ**

*1. የተጠቆሙ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች*

- ፎቶግራፎችና ምስሎች
- የኢትዮጵያ የአየር ንብረት ካርታ
- የኢትዮጵያ መልከአ ምድር ካርታ

*2. የተጠቆሙ የማስተማር ሥነ ዘዴዎች*

- የቡድን ውይይት
- ጥቂት አባላት ያሉት የቡድን ውይይት
- ዘገባ ማጠናቀር
- ጥያቄና መልስ

*3. ቅድመ ዝግጅት*

- ለክፍል መወያያ የሚሆኑ ሀሳቦች ማዘጋጀት፡፡
- አጋዥ የሆኑ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ለተማሪዎች እይታ በሚያመች ሥፍራ ማስቀመጥ፡፡

## ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት

### *1. መግቢያ*

ለተማሪዎች ሊቀርቡ የሚችሉ የጥያቄ ዓይነቶች፤

- የሕዝቦችን አሰፋፈር የሚገድቡ ዋና ዋና ምክንያቶች ምንድን ናቸው?
- ገጠር ከከተማ ወይም ከተማ ከገጠር በምን ይለያል፡፡
- የልዩነቱስ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው፡፡

### *2. የትምህርቱ አቀራረብ*

ተማሪዎችን በአራት ቡድን በመክፈል የሚከተለውን እንዲያከናውኑ ንገሩአቸው፡፡

ቡድን 1. የከፍተኛ ቦታ ገጠር ቡድን 3. የዝቅተኛ ቦታ ገጠር

ቡድን 2 የከፍተኛ ቦታ ከተማ ቡድን 4. የዝቅተኛ ቦታ ከተማ

***መመሪያ***

- ስለተጠቀሱት አካባቢዎች ጥናት አካሂዱ፡፡
- የቦታዎቹ የአየር ንብረት ወይም የቤቶች ሁኔታ፣ የሕዝቦች አለባበስ፣ የሚመረቱ ሰብሎች፣ ንግድና ባህል ያላቸውን ተጽእኖ አብራሩ፡፡
- ስለአገኛችሁት ውጤት የሚገልጽ ዘገባ በማጠናቀር ለክፍል ውይይት አቅርቡ፡፡

## ረ. ግምገማና ክትትል

### *1. ግምግማ*

ለተማሪዎች የሚቀርቡ የጥያቄ ዓይነቶች

- በደጋና በቆላ አካባቢዎች የሚኖሩ ሕዝቦች የአኗኗር ልዩነቶችን የሚወስን ዋንኛ ምክንያት ምንድን ነው?
- የገጠር ኑሮ ከከተማ ኑሮ አስቸጋሪ ነው? ለምን?

*2. ክትትል*

በኢትዮጵያ የዝቅተኛና ከፍተኛ ስፍራዎች በሰፈሩ ሕዝቦች መካከል የባህልና የአኗኗር ዘይቤ ልዩነት ምክንያቶችን የሚያብራራ አንድ ገጽ የጽሑፍ ዘገባ እንዲያዘጋጁ መንገር።

## የምዕራፍ አንድ የክለሣ ጥያቄዎች መልስ

### ሀ) የእውነት/ሐሰት ጥያቄዎች

1. ሐሰት
2. እውነት
3. ሐሰት
4. እውነት
5. ሐሰት

### ለ) የአዛምድ ጥያቄዎች

1. ተ
2. ለ
3. ሠ
4. ሸ
5. ሰ
6. ሐ
7. ረ

### ሐ) የምርጫ ጥያቄዎች

1. መ
2. ለ
3. ሀ
4. ሐ
5. ሀ
6. መ
7. ለ
8. ሀ
9. ለ
10. ሐ

### መ) ባዶ ሥፍራ የመሙላት ጥያቄዎች

1. የአየር ንብረት፣ የተፈጥሮ ሀብት፣ መልክዐ ምድር
2. ዲኪካ
3. የአቢሲኒያ ባንክ
4. የኢትዮጵያ ውሕደት፣ በውጪ ወራሪዎች ላይ የተገኘ ድል እና ዘመናዊነት

**ሠ) የአጫጭር ምላሽ ጥያቄዎች**

1. የጥንታዊ ዳኣማት ነገሥታት ማዕረግ፣
2. ትምህርት ቤት፣ ብሔራዊ የመገበያያ ገንዘብ፣ የባቡር ሐዲድ፣ ስልክና ቴሌግራም፣........
3. ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት ዋስትና መሆን
   - ለአፍሪካውያን የነፃነት ምሳሌ መሆን
   - አዲስ አበባ ለአህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ተቋማት መቀመጫ መሆን
4. ስለ ግለሰቦች ማንነት መግለፅ፣
   ሀ) የሐረር ኤሚሬት የመጨረሻ መሪ ናቸው፡፡
   ለ) በሐረር ከተማ ዙሪያ ግንብ ያስገነቡ የአዳል መሪ ናቸው፡፡
   ሐ) መላ የኢትዮጵያ አካባቢ በጦር ኃይል አሸንፎ ከ1529 እስከ 1535 ዓ.ም(እ.ኤ.አ 1528-1543 ዓ.ም) የገዙ የአዳል መሪ ናቸው፡፡
   መ) ኢፋትና አዳልን ሲገዛ የነበረ ሥርወ መንግሥት መሥራች ናቸው፡፡
   ሠ) የመጨረሻው የወላይታ ንጉሥ ናቸው፡፡
   ረ) የመጨረሻው የከፋ መንግሥት ንጉሥ ናቸው፡፡
   ሰ) የሐረር ኤሚሬት መሥራች ናቸው፡፡
5. እስልምና ወደ ኢትዮጵያ የተስፋፋው የመጀመሪያዎቹ የእስልምና ተከታዮች ወደ አክሱም ከመጡበት ከ615 ዓ.ም ጀምሮ ነበር፡፡
6. በአፋር ብሔራዊ ክልል ይገኛሉ፡፡
7. ሁሉም ዜጋ በጥበቃቸውና እንክብካቤያቸው ላይ ተሳታፊ ሲሆን ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር በምዝገባ፣ በሕግ ከለላና ኅብረተሰቡ ስለ ቅርሶች ጠቀሜታ ግንዛቤ እንዲያገኝ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## መሬትና አካባቢዋ

***ለምዕራፉ የተመደበው ጠቅላላ ክፍለ ጊዜ 10***

***የምዕራፉ ትምህርት ሲጠናቀቅ  የሚጠበቁ ውጤቶች***

**ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ይዘቶች ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

- በትምህርት ቤታቸው ዙሪያ ያሉትን ነገሮች የሚያሳይ ካርታ ደረጃ በደረጃ ያዘጋጃሉ (ይስላሉ)፡፡
- የመሬት መሽከርከር የሚያመጣውን ውጤት(ለውጥ) ያብራራሉ፡፡

***ርዕሶች***

2.1 መገኛችን

2.2 የመሬት ቅርፅ፣እንቅስቃሴና የእንቅስቃሴዋ ውጤቶች

2.3 የወቅቶች መፈራረቅ በእርሻና በከብት እርባታ ላይ ያለው ተፅዕኖ

### 2.1. መገኛችን

***የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡- 4***

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- የካርታን ጠቀሜታ ያብራራሉ፡፡
- ንድፍ ካርታ እንዴት እንደሚዘጋጅና እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል ይገልፃሉ፡፡
- የትምህርት ቤታቸውን መገኛ የሚያሳይ ንድፍ ካርታ ያዘጋጃሉ፡፡

**ለ. ይዘቶች**

- አቅጣጫንና መገኛን ለማሳየት ንድፍ ካርታ መጠቀም
- ተራ ንድፍ ካርታ ማዘጋጀት

**ሐ. የትምህርቱ ጭብጥ**

መገኛ ማለት አንድ ነገር ወይም ግለሰብ ከሌሎች ነገሮች አንፃር የያዘው ሥፍራ ማለት ነው። መገኛን በመሬት ላይ ወይም በካርታ ወይም በንድፍ ካርታ ላይ ማሳየት ይቻላል። ካርታ በመስፈርት አማካኝነት በመሬት ላይ የሚገኙ ነገሮችን በዝርግ ወረቀት ላይ የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ ነው። በሌላ በኩል ንድፍ ካርታ መስፈርትን በመጠቀም በተሰባሰበ መረጃ መሠረት የሚሳል የአንድ ውሱን ሥፍራ ንድፍ ወይም ፕላን ነው። ንድፍ ካርታ ያለምንም መሣሪያ እገዛ በእጅ ብቻ ይሣላል። ካርታ ግን በሰለጠኑ ባለሙያዎች ዘመናዊ መሣሪያዎችን በመጠቀም ይዘጋጃል። ካርታ መገኛንና አቅጣጫን ለማመላከት ያገለግላል።

**መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ**

1. ***የተጠቀሙ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች***
    - ንድፍ ካርታ
    - የአፍሪካ ተፈጥሮአዊና ፓለቲካዊ ካርታ
2. ***የተጠቀሙ የማስተማር ሥነ ዘዴዎች***
    - የቡድን ውይይት
    - ጥያቄና መልስ
    - ሠርቶ ማሳየት
3. ***ቅድመ ዝግጅት***
    - የሚነበቡ ርዕሶችን በቤት ሥራ መልክ መስጠት።
    - ለርዕሱ ለተጠቀሙ ቁልፍ ቃላት ተማሪዎች ትርጉማቸውን እንዲያፈላልጉ ማድረግ።
    - የመማር ማስተማር መርጃ መሣሪያዎችን ለእይታ ግልፅ በሆነ ስፍራ ማኖር።

- ዕለታዊ የትምህርት ዕቅዶችን ለማጣቀሻነት እንዲረዱ ዝግጁ ማድረግ፡፡

## ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት

### 1. መግቢያ

በምዕራፉ የመጀመሪያ ክፍለ ጊዜ ካለፈው ምዕራፍ ይዘት ጋር ትስስር እንዲኖረው ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ተማሪዎችን ባለፉት ክፍለ ጊዜያት የተማራችሁት ስለምን ጉዳይ ነበር ብሎ መጠየቅ ይቻላል፡፡ ከዚያም ወደ ዕለቱ የትምህርት ርዕስ በመግባት ለተማሪዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎች ማቅረብ ይቻላል፡፡

- መገኛ ምንድን ነው?
- ካርታ ምንድን ነው?
- ንድፍ ካርታ ምንድን ነው?

### 2. የትምህርቱ አቀራረብ

ከዚህ በላይ ለቀረቡ ጥያቄዎች ከተማሪዎች የሚቀርቡ ምላሾችን መሠረት በማድረግ ተማሪዎች በሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲጨብጡ በሚረዳ መልክ ግልፅ ማብራሪያ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡

- ካርታ
- ንድፍ ካርታ
- መስፈርት
- አቅጣጫ
- መገኛ

ከዚህ በማስከተል ተማሪዎች የመማሪያ ክፍላቸውን በመማሪያ መጽሐፋቸው በቀረበው መመሪያ መሠረት እንዲስሉ ያድርጉ፡፡

## ረ. ግምገማና ክትትል

### *1. ግምገማ*

ተማሪዎች የትምህርቱን መሠረተ ሀሳቦች ምን ያህል እንደጨበጡ ለማረጋገጥ የሚከተሉ ዓይነት ጥያቄዎችን መጠየቅ ይቻላል፡፡

- የንድፍ ካርታ መስፈርት ምንድን ነው?
- ንድፍ ካርታ ሊያካትታቸው የሚገቡ ገጽታዎች ወይም ነገሮች ምንድን ናቸው?
- በካርታ አማካኝነት መገኛን እንዴት ማመላከት ይቻላል?
- ንድፍ ካርታን ከካርታ ለየት የሚያደርጉ ነገሮች ምንድን ናቸው?

### 2. ክትትል

ቀጥሎ በቀረበው መመሪያ መሠረት ተማሪዎች የመኖሪያ መንደሮ ቻቸውን ንድፍ ካርታ እንዲስሉ ያደርጉ፡፡

1. ስለ መንደሮቻችሁ መረጃ አሰባስቡ፡፡
2. ባሰባሰባችሁት መረጃ መሠረት የመንደሮቻችሁን ንድፍ ካርታ ሣሉ፡፡
3. በንድፍ ካርታው ላይ እንደ መንገድ፣ ወንዝና ዋና ዋና ሕንፃዎችን አስፍሩ፡፡

## 2.2 የመሬት ቅርፅ፣ እንቅስቃሴዋና የእንቅስቃሴዋ ውጤቶች

***የተመደበው ክፍለ ጊዜ 4***

### ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃት

*ተማሪዎች የንዑስ ርዕሱን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡*

- የመሬትን ቅርፅና እንቅስቃሴ አይነቶችን ይለያሉ፡፡
- የመሬት እንቅስቃሴ የሚያመጣውን ለውጥ (ውጤት) ያብራራሉ፡፡

**ለ. ይዘቶች**

- የመሬት ቅርፅ
- የመሬት እንቅስቃሴና ውጤት
- የቀንና ሌሊት መፈራረቅ
- የወቅቶች መፈራረቅ
- የመሬት 23.5° ማጋደልና የወቅቶች መፈራረቅ

**ሐ. የትምህርቱ ጭብጥ**

የመሬት ቅርፅ ለበርካታ ሺህ ዓመታት አከራካሪ ሆኖ ቆይቶ ነበር፡፡ ነገር ግን ከክርስቶስ ልደት በኋላ ማለትም ከአንደኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ መሬት ሞላላ (ሉል) ቅርፅ እንደነበራት ይታመን ነበር፡፡ በርግጥ የመሬት ቅርፅ ፍጹማዊ ክብ አይደለም፡፡ ቅርፂ ሉል ይመስላል፡፡ መሬት ብዙ ዓይነት እንቅስቃሴዎች ታደርጋለች፡፡ ከእንቅስቃሴዎችዋ መካከል ግን በግልፅ የሚታዩት ሁለት ዓይነት እንቅስቃሴዎች ናቸው፡፡ እነዚህ እንቅስቃሴዎች ሽክርክሪትና ዙሪት በመባል ይታወቃሉ፡፡ እነዚህ ሁለት እንቅስቃሴዎች በመሬት ላይ የተለያዩ ክስተቶችን ያስከትላሉ፡፡ ሽክርክሪት የቀንና ሌሊትን መፈራረቅ ያስከትላል፡፡ ዙሪት ደግሞ ወቅቶች እንዲታዩና የቀንና ሌሊት ርዝማኔ የተለያየ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

**መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ**

1. *የተጠቀሙ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች*
   - ሉል(ግሎብ)
   - ፎቶግራፎችና ምስሎች
2. *የተጠቀሙ የማስተማር ሥነ ዘዴዎች*
   - የቡድን ውይይት
   - ጥያቄና መልስ
   - ሠርቶ ማሣየት
   - የግል ሥራ

*3. ቅድመ ዝግጅት*

- የሚነበብ ርዕስ በቤት ሥራ መልክ መስጠት፣
- በንዑስ ርዕስ ትምህርቱ ለተጠቀሙ ቁልፍ ቃላት ተማሪዎች ትርጉም እንዲያፈላልጉ ማድረግ፣
- የመማሪያ ማስተማሪያ መሣሪያዎችን ለእይታ ግልፅ በሆነ ሥፍራ ላይ ማኖር፣

## ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት

*1. መግቢያ*

በዕለቱ የትምህርት ርዕስ ላይ ተማሪዎች ምን ያህል ግንዛቤ እንዳላቸው ለመፈተሽ ያህል የሚከተሉ ዓይነት ጥያቄዎች መጠየቅ ይቻላል፡፡

- ቀንና ሌሊት የሚፈራረቀው በምን ምክንያት ነው?
- የመሬት ቅርፅ ምን ይመስላል?
- ከመሬት ቅርፅ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ቅርፅ ያለው የምታውቁት ነገር አለ ወይ?

*2. የትምህርቱ አቀራረብ*

ሉልን በመርጃ መሣሪያነት በመጠቀም ተማሪዎች ቀጥሎ በተዘረዘሩ ርዕስ ጉዳዮች ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲጨብጡ የሚያስችል ገለፃ ያድርጉ፡፡

- የመሬት ቅርፅ
- የመሬት እንቅስቃሴዎች፤ ሽክርክሪትና ዙሪት
- የመሬት እንቅስቃሴዎች የሚያስከትሉ ውጤቶች
    - የቀንና ሌሊት መፈራረቅ
    - የቀንና ሌሊት ርዝማኔ መለያየት
    - የወቅቶች መከሰት

ከገለፃው ቀጥሎ ከበስተምሥራቅ አቅጣጫ ብርሃን ወደ ሉል የሚረጭ የእጅ ባትሪ በመጠቀም ቀንና ሌሊት እንዴት እንደሚፈራረቁ ማሳየትና በመጨረሻም ተማሪዎች የሉል ሞዴል እንዲያዘጋጁና በሉሉ ላይ ቀጥ ያለና ወደ አንድ በኩል ዘመም ያለ ዛቢያ እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡

**ረ. ግምገማና ክትትል**

*1. ግምገማ*

በትምህርቱ ላይ ምን ያህል ግንዛቤ እንደጨበጡ ለማወቅ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች ዓይነት ለተማሪዎች ማቅረብ፡፡

- መሬት እንዴት ትንቀሳቀሳለች?
- የመሬት እንቅስቃሴ ምን ዓይነት ውጤቶች ያስከትላል?
- ወቅቶች ምንድን ናቸው?
- በመሬት ወደ አንድ አቅጣጫ ዘመም ማለትና በወቅቶች መካከል ያለው ትስስር ምንድን ነው?

*2. ክትትል*

በትልቅ የሥዕል መሳያ ወረቀት ላይ ተማሪዎች መሬት በፀሐይ ዙሪያ የምታከናውነውን ዙሪት ከተለያዩ ወቅቶች ጋር ስለው እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡

## 2.3. የወቅቶች መፈራረቅ በእርሻና በከብት እርባታ ላይ ያለው ተጽእና

***የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡- 2***

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

*ተማሪዎች የንዑስ ርዕሱን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፣*

- የወቅቶች መፈራረቅ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ (በእርሻና በከብት እርባታ)ያለው አሉታዊና አዎንታዊ ተጽእኖ ያዛምዳሉ፡፡

**ለ. ይዘቶች**

- ወቅቶች በኢትዮጵያ
- የወቅቶች መፈራረቅ በአርሻና በከብት እርባታ እንቅስቃሴ ላይ ያለው አሉታዊና አዎንታዊ ተጽእኖ

**ሐ. የትምህርቱ ጭብጥ**

ወቅቶች በመሬት ዙሪት (Revolution) የተነሳ የሚፈጠሩ ክስተቶች ናቸው፡፡ የሚፈጠሩትም መሬት የምትሽከረከርበት ዛቢያ ከመሬት ምሕዋር አንፃር ወደ አንድ አቅጣጫ ዘመም ያለ በመሆኑ ነው፡፡ የመሬት ዝመት

የሰሜን ዋልታ ለግማሽ ዓመት ያህል እንደዚሁም የደቡብ ዋልታ ደግሞ ለቀሪው ግማሽ ዓመት ወደ ፀሐይ አቅጣጫ እንዲያዘሙ ያደርጋል፡፡ በዚህ ሂደት ወደ ፀሐይ ዘመም ያለው ንፍቀ ክበብ ረዥም ቀን እንዲኖረውና ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ ከተዛመመው ንፍቀ ክበብ የበለጠ የፀሐይን ጨረር በቀጥታ ያገኛል፡፡ በስሜናዊ ንፍቀ ክበብ የክረምት ወቅት የሆነ እንደሆነ ይህ ንፍቀ ክበብ ወደ ፀሐይ አቅጣጫ ዘመም ብሏል ማለት ነው፡፡ በተመሣሣይ ወቅት በደቡብ ንፍቀ ክበብ የበጋ ወቅት ሲሆን ንፍቀ ክበቡ ከፀሐይ ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ ተዛሟል ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ወቅቶች በግልፅ የሚከሰቱት ከሐሩር ክልል ውጭ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ሙቀት ባለው የሐሩር ክልል ትገኛለች፡፡ በዚህ የተነሳ አንድ ዓመት በሁለት ማለትም በእርጥብና (ዝናባማ) ደረቅ ይከፋፈላል፡፡ ዳሩ ግን በተለምዶ በኢትዮጵያ አንድ ዓመት በአራት ወቅቶች ይከፋፈላል፡፡ እነዚህ ወቅቶች ክረምት፣ መኸር፣ በጋና በልግ ተብለው ይጠራሉ፡፡ ይህ አከፋፈል ከአገሪቱ ሕዝቦች ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ጋር ጥብቅ ትስስር ያለውና በእንቅስቃሴዎቹም ላይ ተጽእኖ ለማሳደር የሚችል ነው፡፡

**መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ**

***1. የተጠቀሙ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች***

- የኢትዮጵያ ተፈጥሮአዊና ፖለቲካዊ ካርታ፣
- የምድራችንን ወቅቶች በወራትና በንፍቀ ክበብ ከፋፍሎ የሚያሳይ ሠንጠረዥ፣
- ፎቶግራፎችና ምስሎች፡፡

***2. የተጠቀሙ የማስተማር ሥነ ዘዴዎች***

- የቡድን ውይይት
- ጥያቄና መልስ
- የግል ሥራ

### 3. ቅድመ ዝግጅት

- የሚነበብ ርዕስ በቤት ሥራ መልክ መስጠት፣
- የመማር ማስተማር መርጃዎችን ለእይታ ግልፅ በሆነ ሥፍራ ላይ ማኖር፣
- ዕለታዊ የትምህርት ዕቅዶችን ለማጣቀሻነት ዝግጁ ማድረግ፡፡

## ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት

### 1. መግቢያ

ቀጥሎ የተመለከቱ ጥያቄዎች ዓይነት ለተማሪዎች ያቅርቡ፡፡

- በኢትዮጵያ በአንድ ዓመት ስንት ወቅቶች አሉ?
- ወቅቶች በኢትዮጵያ የተለያዩ እንዲሆኑ የሚያደርገው ምንድን ነው?

### 2. የትምህርቱ አቀራረብ

- መሬትን በወራትና በንፍቀ ክበባት ከፋፍሎ የሚያቀርብ ሠንጠረዥ በመጠቀም እያንዳንዱ ወቅት በኢትዮጵያ ያለውን ስያሜ እንዲናገሩ ተማሪዎችን ይጠይቁ፡፡
- የክፍሉን ተማሪዎች በቡድን በመከፋፈል በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ወቅቶችን ተከትለው በሚከናወኑ ዋና ዋና የእርሻ ሥራዎች ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ ከውይይቱ በኋላ እያንዳንዱ ቡድን ዘገባ ማቅረብ እንዳለበት ሊዘነጋ አይገባም፡፡
- በኢትዮጵያ ቆላማና ደጋማ አካባቢዎች በክረምትና በበጋ በሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ላይ ያደረጉአቸውን ጥናት ለክፍል በማቅረብ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡
- በመጨረሻ የንዑስ ክፍለ-ትምህርቱን ርዕስ አብይ ጭብጦችን በመዳሰስ የዕለቱን ትምህርት መቋጨት ይቻላል፡፡

### ረ. ግምገማና ክትትል

*1. ግምገማ*

ቀጥሎ የቀረቡ ጥያቄዎች ዓይነት ተማሪዎችን መጠየቅ ይቻላል፡፡

- የከብት አርቢዎች መሠረታዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ምንን ያካትታሉ?
- በተለምዶ በኢትዮጵያ አንድ ዓመት በስንት ወቅቶች ይከፋፈላል፡፡
- ወቅቶች በኢትዮጵያ ውስጥ በእርሻ ሥራና በከብት አርቢነት እንቅስቃሴ ላይ ያላቸው ጫና ምንድን ነው?

*2. ክትትል*

ተማሪዎች የኢትዮጵያ ንድፍ ካርታ ስለው በእርሻ ሥራና በከብት አርቢነት በስፋት የሚታወቁ የኢትዮጵያ አካባቢዎችን በካርታው ላይ እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡

## የምዕራፍ ሁለት የክለሣ ጥያቄዎች መልስ

**ሀ) የእውነት/ሐሰት ጥያቄዎች**

1. እውነት
2. እውነት
3. ሐሰት
4. እውነት
5. እውነት

**ለ) የአዛምድ ጥያቄዎች**

1. ሠ 2. ሐ 3. ሀ 4. መ 5. ለ

**ሐ) የምርጫ ጥያቄዎች**

1. ሀ 2. ሐ 3. ሐ 4. ሐ 5. ሐ

**መ) ባዶ ሥፍራ የመሙላት ጥያቄዎች**

1. ካርታ
2. ሞላላ ክብ
3. በካርታ፣ በመሬት
4. ሽክርክሪት
5. ምሕዋር

**ሠ) የአጫጭር ምላሽ ጥያቄዎች**

1. ሥፍራዎች ለማግኘትና መገኛ ለማወቅ፣
2. መረጃ በማሰባሰብ በነፃ እጅ (ያለድጋፍ ሰጭ መሣሪያ) የሚሳል ፕላን ነው፡፡
3. መሬት ሞላላ ክብ ናት፡፡ ሁለት ዓይነት እንቅስቃሴዎች ታደርጋለች፡፡ አንደኛው ሽክርክሪት ይባላል፡፡ ይህ ሽክርክሪት መሬት በራሷ ዛቢያ ላይ የምትፈፀመው እንቅስቃሴ ነው፡፡ ሌላው ዙሪት ይሰኛል፡፡ መሬት በፀሐይ ዙሪያ የምታካሂደው እንቅስቃሴ ነው፡፡
4. የቀንና ሌሊት ርዝማኔ የተለያየ እንዲሆንና የወቅቶችን መፈራረቅ ያስከትላል፡፡
5. ቀንና ሌሊት በመሬት ሽክርክሪት ምክንያት ሲፈጠሩ የመሬት ዙሪት ደግሞ የወቅቶች መፈራረቅ እንዲኖር ያደርጋል፡፡
6. ክረምት፣ መኸር፣ በጋ እና በልግ ናቸው፡፡
7. የእርሻ ሥራ  ወቅትን ተከትሎ የሚከናወን ተግባር ነው፡፡ የዘር መዝሪያ፣ መኮትኮቻ፣ ማጨጃ ጊዜያቶች የተለያዩ ናቸው፡፡ ከብት አርቢውም የግጦሽ ሣር ለማግኘት ወቅቶች ወሳኝ ናቸው፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## አካባቢያችን

**ለምዕራፉ የተመደበው ክፍለ ጊዜ 19**

***የምዕራፉ ትምህርት ሲጠናቀቅ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-***

***ተማሪዎች የምዕራፉን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ***

- በአካባቢያቸው የሚገኙ ዋና ዋና እፅዋትና የዱር አራዊትን ያውቃሉ፣ተገቢው ጥበቃም ያደርጋሉ፡፡
- ከኢኮኖሚ እድገት ተመጣጣኝ ያልሆነ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር በአካባቢያችን በሚገኙ እፅዋትና የዱር አራዊት ላይ ያለውን አሉታዊ ተጽእኖ ይገነዘባሉ፡፡

***ርዕሶች***

3.1 የእፅዋት  ዓይነቶችና የዱር እንስሳት

3.2 የዱር እንስሳትና እፅዋቶች የሚሰጡት ጥቅም

3.3 ከኢኮኖሚ እድገት ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር

3.4 መጨመር እፅዋት ላይ የሚያመጣው አሉታዊ ተጽእኖ

3.5 የተፈጥሮ እፅዋትና የዱር እንሰሳት እንክብካቤ

### 3.1. ዋና ዋና የእፅዋት ዓይነቶችና የዱር እንስሳት

***የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡- 4***

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

***ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ካጠናቀቁ በኋላ***

- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ ዋና ዋና እፅዋትንና የዱር አራዊትን ይለያሉ፡፡

* በኢትዮጵያ የሚገኙ ዋና ዋና የዱር እንስሳትን ስም ይዘረዝራሉ፡፡
* በአፍሪካ ቀንድ በሁሉም ሀገሮች የሚገኙ እንስሳትንና በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙትን ይለያሉ፡፡

### ለ.ይዘቶች

* ደን፣ በሳር የተሸፈነ ምድርና የበርሃ ቁጥቋጦ
* በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ እፅዋት
* ዋና ዋና የዱር እንስሳት ዓይነቶች

### ሐ. የትምህርቱ ጭብጥ

እፅዋት አንድ አካባቢ ባለው የተፈጥሮ ሁኔታ መሠረት በአንድ ስፍራ እጅብ ብለው የሚበቅሉ ተክሎች ማለት ነው፡፡ ዋና ዋና የእፅዋት አይነቶች ደን፣ የሣር ምድርና የበረሃ ቁጥቋጦ ናቸው፡፡ እነዚህ ዋና ዋና የእፅዋት ዓይነቶች በተራቸው ወደተለያዩ ንዑሳን የእፅዋት ዓይነቶች ይከፋፈላሉ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ የመሬት ከፍታ፣ የዝናብና የሙቀት ሥርጭት ከስፍራ ስፍራ የተለያየ በመሆኑ ነው፡፡ ለምሳሌ ደን ዝናባማ ደን፣ የዝቅተኛ ሥፍራ ደንና፣ የከፍተኛ ሥፍራ ደን በመባል በሦስት ይከፋፈላል፡፡ እንደዚሁ ደግሞ የሣር ምድር የሐሩር ሣር ምድርና የወይናጌ ሣር ምድር በመባል በሁለት ይከፋፈላል፡፡ በአንድ አካባቢ የሚገኙ የዱር እንስሳት ዓይነት የሚወሰነው በአካባቢው ባለው የእፅዋት ዓይነት ነው፡፡ በጥቅጥቅ ደን አካባቢ ሊገኙ የሚችሉ የዱር እንስሳት በደኑ ውስጥ ተሹለክልከውና ተንጠላጥለው በቀላሉ መንቀሳቀስ የሚችሉ እንደ ዝንጀሮ፣ እባብና አእዋፍ ዓይነት ናቸው፡፡ የሣር ምድር ገላጣ ስፍራ በመሆኑ ለበርካታ ዓይነት የዱር እንስሳት መጠለያ ነው፡፡ በዚህ ስፍራ ሣር በልና ሥጋ በል የሆኑ በርካታ የዱር እንስሳት በጋራ ይኖራሉ፡፡ በበረሃ የሚገኙ የዱር እንስሳት ደግሞ ከአካባቢው ከፍተኛ ሙቀትና የውኃ እጥረት ጋር የተላመዱ ናቸው፡፡ ያለ ውኃ ለረዥም ጊዜ ለመቆየት የሚችሉም ናቸው፡፡ ብዙውን ጊዜ በበረሃ የሚገኙ እንስሳት እንደ ጊንጥና እባብ የመሳሰሉ መርዛማ ናቸው፡፡

**መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ**

*1. የተጠቀሙ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች*

- የአፍሪካ ተፈጥሮአዊ ካርታ
- ፎቶግራፎችና ምስሎች

*2. የተጠቀሙ የማስተማር ሥነ ዘዴዎች*

- የቡድን ውይይት
- ጥያቄና መልስ
- ሠርቶ ማሣየት

*3. ቅድመ ዝግጅት*

- የሚነበቡ ርዕሶች በቤት ሥራ መልክ ለተማሪዎች መስጠት፡፡
- በንዑስ ርዕሱ ለተጠቀሙ ቁልፍ ቃላት ተማሪዎች ትርጉማቸውን እንዲያፈላልጉ ማድረግ፡፡
- የመማሪያ ማስተማሪያ መሣሪያዎችን ለእይታ ግልፅ በሆነ ሥፍራ ማኖር፡፡
- ዕለታዊ የትምህርት ዕቅዶችን ለማጣቀሻነት ዝግጁ ማድረግ፡፡

**ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት**

*1. መግቢያ*

ተማሪዎች ያላቸውን ዕውቀት ለመፈተሽ የሚከተሉ ዓይነት ጥያቄዎች ማቅረብ ይቻላል፡፡

- እፅዋት ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ?
- ደን ምንድን ነው?
- ምን ዓይነት ደኖች አሉ?
- በረሃ ምንድን ነው?
- ስለ ዱር እንስሳት ምንነት ልትነግሩኝ ትችላላችሁ?

## *2. የትምህርቱ አቀራረብ*

የኢትዮጵያ ፊዝካዊ ካርታ ለእይታ በሚመች ሥፍራ በማንጠልጠል ተማሪዎች የሚከተሉትን እዲያሳዩ ይጠይቁ፡፡

- የቅጠለ ሰፋፊ ዝናባማ ደን ሥርጭት፡፡
- የከፍተኛ ስፍራ ደን ሥርጭት፡፡
- የዝቅተኛ ስፍራ ደን ሥርጭት፡፡

እንዲያነቡ በተነገራቸው መሠረት ተማሪዎች ቀጥሎ በተዘረዘሩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ተወያይተው የውይይታቸውን ዘገባ ለመላው የክፍሉ ተማሪዎች በተወካዮቻቸው አማካኝነት እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

- በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ የእፅዋት ዓይነቶችና ባሕሪያቸው፡፡
- በኢትዮጵያ የሚገኙ የእፅዋት ዓይነቶችና ባሕርያቸው፡፡
- የዱር እንስሳት፤ በዝቅተኛ ሥፍራ የሚገኙ፣ በየብስና በውኃ አካላት ውስጥ የሚኖሩ፡፡
- በኢትዮጵያ ለዱር እንስሳት መጥፋት መንስኤ፡፡
- የትም ተገኝ፣ ብርቅዬና ብቸኛ እና ሊጠፉ በአደጋ ላይ የሚገኙ የዱር እንስሳት፡፡

*ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል የሚከተሉ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ያድርጉ፡፡*

- የኢትዮጵያ ንድፍ ካርታ በመሳል የሚከተሉትን እንዲያሳዩ፣
    - የከፍተኛ ሥፍራ ደን ሥርጭት
    - የዝቅተኛ ሥፍራ ደን ሥርጭት
    - የቅጠለ ሰፋፊ ዝናባማ ደን ሥርጭት
    - የቅምብብማ ደን ሥርጭት

**ረ. ግምገማና ክትትል**

*1. ግምገማ*

የሚከተሉ ዓይነት ጥያቄዎችን ለተማሪዎች ማቅረብ ይቻላል፡፡

- ቅጠለ ሰፋፊና ቅምብብማ ደኖች በየትኛው የኢትዮጵያ አካባቢ ይገኛሉ?
- የከፍተኛ ስፍራ ደኖች በየትኛው የኢትዮጵያ አካባቢ ይገኛሉ?

*2. ክትትል*

ተማሪዎች በሚከተለው ርዕሰ ጉዳይ ላይ አጫጭር ፅሑፎች እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

- በኢትዮጵያ የከፍተኛ ስፍራ እፅዋትና የከፍተኛ ስፍራ ደን መካከል ያለው ልዩነት፡፡

## 3.2. የዱር እንስሳትና እፅዋት የሚሰጡት ጥቅም

***የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡- 4***

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

*ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ካጠናቀቁ በኋላ*

- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ የተፈጥሮ እፅዋትና የዱር እንስሳት ጥቅም ያስረዳሉ፡፡
- ስለዱር እንስሳት የተፈጥሮ መኖሪያቸው ጥበቃ ማድረግ ያለውን ጥቅም ያብራራሉ፡፡
- የዱር እንስሳትንና እፅዋትን መንከባከብ ለምን ጠቃሚ እንደሆነ በዙሪያቸው ለሚገኙ ማኅበረሰቦች ያስረዳሉ፡፡

**ለ. ይዘቶች**

- በዱር እንስሳትና እፅዋት መካከል ተፈጥሮአዊ ሚዛንን መጠበቅ
- የአርሶ አደሮችና የዱር እንስሳት ተስማምተው መኖር
- ቱሪዝም ለኅብረተሰቡ ፣ ለዱር እንስ ሳትና ለአርሶ አደሮች ያለው ጥቅም

## ሐ. የትምህርቱ ጭብጥ

በሰዎች፣ በእፅዋትና በዱር እንስሳት መካከል እጅግ ጠንካራ የሆነ ትስስር አለ፡፡ እንስሳት በአጠቃላይ ለሕይወታቸው በተክሎች ላይ ጥገኛ ናቸው፡፡ የሰዎች ሕይወት ደግሞ የተመሠረተው በተክሎችና በእንስሳት ላይ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ደን ለሰዎችና ለእንስሳት ሕይወት ወሳኝ የሆነውን ኦክስጅን ወደ ከባቢ አየር ይለቃሉ፡፡ በሦስቱ ትስስር ውስጥ ግን ሰዎች የበለጠ ተጠቃሚ ናቸው፡፡ ምክንያቱም እፅዋትና እንስሳት ለሰዎች እጅግ ሰፋ ያለ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ፣ ፓለቲካዊና ሥነ-ውበታዊ አገልግሎት ስለሚያበረክቱ ነው፡፡

## መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ

1. ***የተጠቀሙ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች***
   - ፎቶግራፎችና ምስሎች
   - ንድፍ ካርታ

2. ***የተጠቀሙ የማስተማር ሥነ-ዘዴዎች***
   - የቡድን ውይይት
   - ጥያቄና መልስ
   - ሰርቶ ማሣየት

3. ***ቅድመ ዝግጅት***
   - የሚነበቡ ርዕሶች በቤት ሥራ መልክ ለተማሪዎች መስጠት፣
   - በንዑስ ርዕሱ ለተጠቀሙ ቁልፍ ቃላት ትርጉም እንዲያፈላልጉ ማድረግ፣
   - የመማሪያ ማስተማሪያ መሣሪያዎችን ለእይታ ግልፅ በሆነ ሥፍራ ማኖር፣
   - ዕለታዊ የትምህርት ዕቅዶችን ለማጣቃሻነት ዝግጁ ማድረግ፡፡

## ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት

### *1. መግቢያ*

የርዕሱን ትምህርት ለማስተዋወቅ ተማሪዎች ከዚህ በፊት ስለተማሩት ርዕስ ምላሽ እንዲሰጡ መጠየቅ ጥሩ ነው። ይህ ዘዴ የርዕሱን ትምህርት ካለፈው ርዕስ ጋር ለማስተሳሰር ያመቻል። ከዚህ በማስተከተል ተማሪዎች በዕለቱ ርዕስ ላይ ምን ያህል ግንዛቤ እንዳላቸው ለመፈተሽ የሚከተሉ ጥያቄዎችን መጠየቅ።

- ሥነ-ምሕዳር ምንድን ነው?
- የተለምዶ ቱሪዝም ምን ዓይነት ቱሪዝም ነው?
- የሰሜን ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ በቱሪስቶች በስፋት የሚጎበኘው ለምን ይመስላችኃል?
- በእፅዋትና በዱር እንስሳት መካከል የተፈጥሮ ሚዛን ስለመጠበቅ።
- አራሽ ገበሬዎችና የዱር እንስሳት እንዴት ተጣጥመው መኖር እንደሚችሉ።
- ቱሪዝም ለማኅበረሰብ፣ ለእንስሳትና ለአራሽ ገበሬዎች ያለው ጠቀሜታ።

### 2. የትምህርቱ አቀራረብ

የክፍሉን ተማሪዎች በቡድን ከፋፍለው ቀጥሎ የቀረቡ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ተወያይተው ለክፍሉ ተማሪዎች የውይይታቸውን ዘገባ እንዲያቀርቡ ያድርጉ።

- የተፈጥሮ ሚዛን ለመጠበቅ ተክሎችና እንስሳት በአንድ አካባቢ እንዴት በጋራ ሊኖሩ ይችላሉ?
- እፅዋትና የዱር እንስሳት በቱሪስት መስህብነታቸው ለኢትዮጵያ ያላቸው ጠቀሜታ።

በመጨረሻ በእፅዋትና በዱር እንስሳት ጠቀሜታ ላይ የማጠቃለያ ሀሳብ በማቅረብ የዕለቱን ትምህርት ማጠናቀቅ ይቻላል።

ረ. ግምገማና ክትትል

*1. ግምገማ*

ተማሪዎች የርዕሱን ትምህርት ምን ያህል እንደጨበጡ ለመፈተሽ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይቻላል፡፡

- በአንድ ሣርማ ምድር አካባቢ የሚኖሩ ሥጋ በልና ሣር በል የዱር እንስሳት እርስ በርስ ምን ያህል ጥገኛ ናቸው?
- የተፈጥሮ ሚዛን ለመጠበቅ ተክሎችና እንስሳት በአንድ አካባቢ በጋራ እንዴት ሊኖሩ ይችላሉ?

*2. ክትትል*

ተማሪዎች በሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ አጭር የጽሑፍ ዘገባ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

- በመኖሪያ አካባቢያችሁ እፅዋትና የዱር እንስሳት መካከል የሚታይ የእርስ በርስ ጥገኝነት፡፡
- ሥነ ምሕዳራዊ ቱሪዝም ከተለምዶ ቱሪዝም ስላለው የበለጠ ጠቀሜታ፡፡

## 3.3. ከኢኮኖሚ እድገት ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር እፅዋት ላይ የሚያመጣው አሉታዊ ተጽእኖ

*የተመደበው ክፍለ ጊዜ:- 4*

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

*ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ካጠናቀቁ በኋላ*

- ከኢኮኖሚ እድገት ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር በአካባቢያችን በሚገኙ እፅዋትና የዱር እንስሳት ላይ የሚያመጣውን አሉታዊ ተጽእኖ ተንትነው ያስረዳሉ፡፡

## ሰ. ይዘቶች

- *የእፅዋት መመናመን*
- *የዱር እንስሳት መሰደድ*
- *የደን ሀብት መመናመን*

## ሐ. የትምህርቱ ጭብጥ

ኢትዮጵያን በመሳሰሉ በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ፈጣን የሕዝብ ዕድገት የተፈጥሮ አካባቢ ችግር ዋነኛ ምንጭ በመሆን ላይ ይገኛል፡፡ የሕዝብ ዕድገት  ፈጣን ከሆነ የተፈጥሮ አካባቢ የመሸከም አቅም እያነሰ ይሄዳል፡፡ ሰዎች ለተለያዩ የተፈጥሮ ሀብቶች ያላቸው ፍላጐቶች ይጨምራሉ፡፡ የተፈጥሮ ሀብት በጥቅም ላይ የሚውልበት ፍጥነት እየጨመረ ይሄዳል፡፡ ለተለያዩ የቤት ቁሳቁሶች ሲባል ጥንቃቄ የጐደለው የደን ዛፍ ጭፍጨፋ ይከሰታል፡፡ ይህ ደግሞ ለእፅዋት  መጥፋት መንስኤ ይሆናል፡፡ የእፅዋት መጥፋት ደግሞ የዱር እንስሳት አካባቢውን ጥለው እንዲሰደዱ ያደርጋል፡፡ ከዚህም በላይ የእፅዋት መጥፋት የመሬት መሸርሸርን በማስከተል በሂደት ለድርቅና ለረሀብ ይዳርጋል፡፡

## መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴ

### *1. የተጠቀሙ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች*

- ንድፍ ካርታ
- ፎቶግራፎችና ምስሎች

### *2. የተጠቀሙ የማስተማር ሥነ ዘዴዎች*

- የቡድን ውይይት
- ጥያቄና መልስ

### *3. ቅድመ ዝግጅት*

- የሚነበቡ ርዕሶች በቤት ሥራ መልክ መስጠት፡፡
- በንዑስ ርዕሱ ትምህርት ለተጠቀሙ ቁልፍ ቃላት ተማሪዎች ትርጉም እንዲያፈላልጉ ማድረግ፡፡

- የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለእይታ ምቹ በሆነ ሥፍራ ማኖር፡፡
- የታረሙ የቤት ሥራዎችና ተግባራትን ለግብረ መልስ ዝግጁ ማድረግ፡፡
- ዕለታዊ የትምህርት ዕቅዶችን ለማጣቀሻነት ዝግጁ ማድረግ፡፡

**ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት**

*1. መግቢያ*

የሚከተሉት ዓይነት ጥያቄዎችን ለተማሪዎች ማቅረብ ይቻላል፡፡

- የእፅዋት መጥፋት እንዴት ይከሰታል?
- የዱር እንስሳት ስደት መንስኤ ምንድን ነው?
- የእፅዋት መጥፋት  የሚያስከትላቸው ውጤቶች ምንድን ናቸው?

*2. የትምህርቱ አቀራረብ*

የክፍሉን ተማሪዎች በቡድን ከፋፍለው በሚከተሉ ርዕስ ጉዳዮች ላይ ተወያይተው የውይይታቸውን ውጤት ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

- ፈጣን የሕዝብ ዕድገት በእፅዋትና በዱር እንስሳት ላይ የሚያስከትለው ተጽእኖ
- የእፅዋት  መጥፋትን አንዴት መቆጣጠር ይቻላል?
- የደን ሀብት መመናመን መንስኤዎች፡፡

በመጨረሻ የርዕሱን ዋና ዋና ጭብጦች በማጠቃለያ መልክ በማንሳት የዕለቱን ትምህርት መቋጨት ያስፈልጋል፡፡

**ረ. ግምገማና ክትትል**

*1. ግምገማ*

ተማሪዎችን የሚከተሉ ዓይነት ጥያቄዎች መጠየቅ ይቻላል፡፡

- የእፅዋት መጥፋት የዱር እንስሳትን ስደት የሚያስከትለው ለምንድን ነው?

- ለደን ሀብት መመናመን  መንሥኤዎች ምንድን ናቸው?
- የእፅዋት መጥፋት በሰዎች ሕይወት ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ምንድን ነው?

## 2. ክትትል

ከዚህ ቀጥሎ በሁለት ምድብ ተከፍለው ከተሰጡ ተግባራዊ ክንውኖች ከእያንዳንዱ ምድብ አንዳንድ መርጠው እንዲያከናውኑ ለተማሪዎች ይንገሩአቸው፡፡

ሀ) የማጣቀሻ ምንጮችን በማፈላለግ በሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ አጭር የጽሑፍ ዘገባ አቅርቡ፡፡

- የእፅዋት መጥፋት
- የዱር እንስሳት ስደት
- የደን ሀብት መመናመን

ለ) የሚከተሉ የተፈጥሮ ሀብቶችን ከጥፋት ለማዳንና ለመጠበቅ ያስችላሉ በምትሉአቸው ዘዴዎች ላይ አጫጭር የጽሑፍ ዘገባ አቅርቡ፡፡

- የእፅዋት መጥፋት
- የዱር እንስሳት ስደት
- የደን ሀብት መመናመን

## 3.4 የተፈጥሮ እፅዋትና የዱር እንስሳት እንክብካቤ

***የተመደበው ክፍለ ጊዜ:- 7***

***ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት***

*ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ካጠናቀቁ በኋላ*

- የተፈጥሮ እፅዋትንና የዱር እንስሳትን እንዴት መንከባከብ እንደሚችሉ ያስረዳሉ፡፡
- የዱር እንሰሳትንና እፅዋትን የመንከባከቢያ ዘዴዎችን ይገልፃሉ፡፡
- የመንከባከቢያ ዘዴዎቹን ከአካባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማዛመድ የዱር እንስሳትንና እፅዋትን ለመጠበቅ በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ በንቃት ይሳተፋሉ፡፡

- በአፍሪካ ቀንድና በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ የዱር እንስሳት ለሚሰጡት ጥቅም አድናቆታቸውን ይገልፃሉ፡፡

**ሰ.ይዘቶች**

- ድነና፣መልሶ ድነና ፣የደን ቃጠሎ መቆጣጠር
- ሕገ ወጥ የሆነ አደንን ማስቆም
- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ፓርኮችና ተንከባካቢ ተቋማት

**ሐ. የትምህርቱ ጭብጥ**

እንክብካቤ ተክሎች፣ እንስሳት፣ ማዕድናት፣ አፈር፣ ንፁሕ ውኃ፣ ንፁሕ አየር፣ የቅሪተ አካል ነዳጅ የሆኑ የድንጋይ ከሰል፣ ነዳጅ ዘይትና የተፈጥሮ ጋዝ የመሳሰሉ የተፈጥሮ ሀብቶችን ዘለቄታነት ሳለው ጠቀሜታ ሊውሉ እንዲችሉ መጠበቅና መንከባከብ ማለት ነው፡፡ የእፅዋትና የዱር እንስሳት እንክብካቤ የተለያዩ ዘዴዎች አሉት፡፡ ከዘዴዎቹ መካከል ዋና ዋናዎቹ ድነና፣ መልሶ ድነና፣ የሰደድ እሳትን መቆጣጠርና ሕገ-ወጥ አደንን ማገድ ናቸው፡፡ የእንክብካቤ ተግባራት የአቅም ግንባታና የተቋማዊ የዕድገት ሥራዎችን ያጠቃልላል፡፡ ከአቅም ግንባታና ተቋማዊ የዕድገት ሥራዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ ብሔራዊ ፓርኮች፣ የዱር እንስሳት መጠለያዎችና የተከለሉ ሥፍራዎች ማቋቋም ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ በርካታ ብሔራዊ ፓርኮች፣ የዱር እንስሳት መጠለያዎችና የተከለሉ ሥፍራዎች ይገኛሉ፡፡

**መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴ**

*1. የተጠቀሙ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች*

- የኢትዮጵያ ተፈጥሮአዊና ፓለቲካዊ ካርታ
- ፎቶ ግራፎችና ምስሎች
- ንድፍ ካርታ

*2. የተጠቀሙ የማስተማር ሥነ ዘዴዎች*

- የቡድን ውይይት

- ጥያቄና መልስ
- ሠርቶ ማሳየት

*3. ቅድመ ዝግጅት*

- የሚነበብ ርዕስ በቤት ሥራ መልክ ለተማሪዎች መስጠት፡፡
- በንዑስ ርዕሱ ለተጠቆሙ ቁልፍ ቃላት ተማሪዎች ትርጉም እንዲያፈላልጉ ማድረግ፡፡
- የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለእይታ አመቺ በሆነ ሥፍራ ማኖር፡፡
- የታረሙ የቤት ሥራዎችና ተግባራት ካሉ ለግብረ መልስ ዝግጁ ማድረግ፡፡
- ዕለታዊ የትምህርት ዕቅዶችን ለማጣቀሻነት ዝግጁ ማድረግ፡፡

**ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት**

*1. መግቢያ*

የዕለቱን የትምህርት ርዕስ ከባለፈው የትምህርት ርዕስ ጋር ለማስተሳሰር ተማሪዎችን ቀደም ሲል ስለምን ርዕስ እንደተማሩ መጠየቅ፡፡

*2. የትምህርቱ አቀራረብ*

ለርዕሱ ከተመደቡ ክፍለ ጊዜያት በአንዱ ትምህርቱን በጥያቄና መልስ ዘዴ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ለዚህ ደግሞ ቀጥሎ የተዘረዘሩ ዓይነት ጥያቄዎች ጠቃሚ ሲሆኑ በመማር ማስተማር ሂደት በተማሪዎች ምላሽ ላይ በመመስረት አልፎ አልፎ ጣልቃ በመግባት ማብራሪያዎችን ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡

- እንክብካቤ ምንድን ነው?
- የእንክብካቤ ዘዴዎች ምንድን ናቸው?

ከዚህ በማከታተል ተማሪዎች በቡድን ተከፋፍለው በሚከተሉ የእንክብካቤ ዘዴዎች ላይ ተወያይተው የውይይታቸውን ዘገባ ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

- ድነና
- መልሶ ድነና
- የሰደድ እሳትና መቆጣጠሪያ ዘዴዎቹ
- ሕገ ወጥ አደንና እንዴት ማገድ እንደሚቻል

ከተማሪዎች ዘገባ በኃላ የማጠቃለያ ማብራሪያ በመስጠት የዕለቱን ትምህርት መቋጨት ይቻላል፡፡

**ረ. ግምገማና ክትትል**

*1. ግምገማ*

ለተማሪዎች የሚከተሉ ዓይነት ጥያቄዎችን ማቅረብ ይቻላል፡፡

- እንክብካቤ ምንድን ነው?
- ከእንክብካቤ ዘዴዎች ዋና ዋናዎቹን ዘርዝሩ፡፡
- በድነናና በመልሶ ድነና መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
- ከኢትዮጵያ ብርቅዬና ብቸና አዕዋፍና የዱር እንስሳት መካከል ጥቂቶቹን ዘርዝሩ፡፡
- ሕገ ወጥ አደንን ማገድ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው?

***2. ክትትል***

ተማሪዎች የሚከተሉ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ያድርጉ፡፡

- በሚከተሉት ርዕስ ጉዳዮች ላይ አጭር የጽሑፍ ዘገባ አቅርቡ፡፡
  - ብሔራዊ ፓርኮችንና የእንስሳት መጠለያዎችን በማነፃፀርና በማወዳደር አስረዱ፡፡
  - የኢትዮጵያን ንድፍ ካርታ በመሳል ዋና ዋና የአገሪቱን ብሔራዊ ፓርኮችና የእንስሳት መጠለያዎችን አሳዩ፡፡

## የምዕራፍ ሦስት የክለሣ ጥያቄዎች መልስ

### ሀ) የእውነት/ሐሰት ጥያቄዎች

1. እውነት
2. ሐሰት
3. እውነት
4. ሐሰት
5. እውነት

### ለ) የአዛምድ ጥያቄዎች

1. ረ ና ለ 2. መ 3. ሰ 4. ሐ 5. ቀ 6. ሸ

### ሐ) የምርጫ ጥያቄዎች

1. ሀ
2. ለ
3. ለ
4. መ
5. ለ
6. ሀ
7. ለ
8. ሀ

### መ) የባዶ ሥፍራ መሙላት ጥያቄዎች

1. ሥነ ምኅዳር
2. እንስሳት
3. 179
4. ዋልያና የሰሜን ቀበሮ

### ሠ) የአጫጭር ምላሽ ጥያቄዎች

1. ድነና፣ መልሶ ድነና፣ ሰደድ እሳት መቆጣጠር፣ ሕገ ወጥ አደን ማስወገድ፣ ብሔራዊ ፓርኮችና መናኸሪያዎችን ማቋቋም ናቸው።
2. የተፈጥሮ አካባቢ የመሸከም አቅም ይቀንሣል፤ ተጨማሪ የተፈጥሮ ሀብት ጥያቄ ያስነሳል፤ ኃላቀር የሆነ የመሬትና የሌሎች ሀብቶች አጠቃቀም የተስፋፋ ይሆናል።
3. በአንድ በተወሰነ ሥነ-ምኅዳር ውስጥ ከሚገኙ እንስሳት እፅዋት በል አንዱ ናቸው። ሥጋ በል እንስሳት እፅዋት በሎችን ይመገባሉ። ሰዎች እፅዋትንና እንስሳትን ይመገባሉ። እንደዚሁም የአካባቢውን ሚዛን ለመጠበቅ የተፈጥሮ ሀብትን በአግባቡ ይጠቀማል፣ ይጠብቃል፤ ይንከባከባል። ይህ ደግሞ የደን ሽፋንና የአፈር ለምነትን ጠብቆ ለማቆየት ያስችላል። ይህ በአጭሩ በአንድ በተወሰነ ሥነ-ምኅዳር ውስጥ በሚገኙ ሰዎችን ጨምሮ በእንስሳት፣ በተክሎችና ሕይወት በሌላቸው ነገሮች መካከል ከፍተኛ ትስስርና የእርስ በርስ ጥገኝነት እንዳለ ያመለክታል።

# ምዕራፍ አራት

## ሕዝባዊ ጉዳዮች

**ለምዕራፉ የተመደበው ክፍለ ጊዜ:- 16**

***ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች***

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ**

- በኢትዮጵያ ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሚያጋልጡ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና የሚያመጡትን አሉታዊ ተጽእኖ ያብራራሉ፡፡
- ከኢኮኖሚ እድገት ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነው ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት ያለውን ተጽእኖ ይተነትናሉ፡፡
- የመልካም አስተዳደርና የሕፃናት መብት መከበር መገለጫዎችን ይገልፃሉ፡፡
- የአደጋ መከላከያና የጥንቃቄ መርሆዎችን ይገነዘባሉ፡፡

**ርዕሶች**

4.1 ሕዝብ ነክ ጉዳዮች

4.2 ፈጣን የሕዝብ ቁጥር  እድገትና አሉታዊ ተጽእኖዎቹ

4.3 መልካም አስተዳደር፣ የሕፃናት መብትና ደህንነት

### 4.1 ሕዝብ ነክ ጉዳዮች

***የተመደበው ክፍለ ጊዜ:- 4***

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

***ተማሪዎች የንዑስ ርዕሱን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ***

- ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሚያጋልጡ ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ላይ ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡
- ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ለምሳሌ ጠለፋ፣ የሴት ልጅ ግርዛት እና ንቅሳት የሚያመጡትን አሉታዊ ተጽእኖ ተንትነው ያስረዳሉ፡፡

### ለ. ይዘቶች

- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስና ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች
- ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መስፋፋት
- የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መስፋፋት መንስኤና የሚያስከትለው ተጽእኖ፤ ለጎዳና ተዳዳሪነት መጋለጥ፣ ወላጅ ማጣት

### ሐ. የትምህርቱ ጭብጥ

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በአሁኑ ጊዜ የአፍሪካ ቀንድ አገሮችን በእጅጉ እየተፈታተነ የሚገኝ ሕዝብ ነክ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ተላላፊ በሽታ በክልሉ ለሚታዩ ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ ችግሮች አብይ መንስኤ ነው፡፡ ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መስፋፋት አስተዋፅዖ ከሚያበረክቱ ነገሮች አንዱ ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በክልሉ በስፋት የሚፈፀሙ መሆናቸው ነው፡፡ ስለዚህ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመግታት የሚደረግ ትግል ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን የማስወገድ ሥልቶች ያካተተ መሆን አለበት፡፡

### መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ

1. *የተጠቀሙ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች*
   - ፎቶግራፎችና ምስሎች
   - ፖስተሮች

2. *የተጠቀሙ የማስተማር ሥነ ዘዴዎች*
   - የቡድን ውይይት
   - ጥያቄና መልስ

3. *ቅድመ ዝግጅት*
   - ፎቶግራፎችን፣ ምስሎችንና ፖስተሮችን ለእይታ ግልፅ በሆነ መልኩ ማኖር፡፡
   - የሚነበብ ርዕስ ለተማሪዎች በቤት ሥራ መልክ መስጠት፡፡

- በንዑስ ርዕሱ ለተጠቀሙ ቁልፍ ቃላት ተማሪዎች ትርጉም እንዲያፈላልጉ ማድረግ፡፡
- ዕለታዊ የትምህርት ዕቅዶችን ለማጣቃሻነት ዝግጁ ማድረግ፡፡

**ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት**

ለዚህ ንዑስ ርዕስ የተመደበው 4(አራት) ክፍለ ጊዜ ነው፡፡ እነዚህን ክፍለ ጊዜያት በአግባቡ በመጠቀም የንዑስ ርዕሱን ትምህርትና ለተማሪዎች የተሰጡ ተግባራትን ለማጠናቀቅ መሞከር አለብዎት፡፡ የትምህርቱ አቀራረብ ቀጥሎ በቀረበው ጥቆማ መሠረት ማካሄድ ይቻላል፡፡

*1. መግቢያ*

ትምህርቱን ለማስተዋወቅ ተማሪዎችን የሚከተሉ ዓይነት ጥያቄዎች መጠየቅ ይቻላል፡፡

- ልማዳዊ ድርጊቶች ምንድን ናቸው?
- ልማዳዊ ድርጊቶች ጉጂ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው?
- ኤች.አይ.ቪ. እና ኤድስ ልዩነታቸው ምንድን ነው?
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ከሰዎች ወደ ሰዎች የሚተላለፈው በምን ዓይነት መንገድ ነው?

*2. የትምህርቱ አቀራረብ*

የክፍሉን ተማሪዎች በቡድን በመከፋፈል በሚከተሉ ጥያቄዎች ላይ ተወያይተው የውይይታቸውን ውጤት ለአጠቃላዩ ክፍል ዘገባ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ በስፋት የሚፈፀሙ ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለይታችሁ ዘርዝሩ፡፡
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እንዴት ለኢኮኖሚያዊና ለማኀበራዊ ችግሮች መንስኤ ይሆናል?
- በክልሉ የሚፈፀሙ ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለማስቆም የሚያስችሉ ምን ዓይነት መፍትሔዎች ታቀርባላችሁ?

- ጉዷ ልማዳዊ ድርጊቶች ሰዎችን ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እንዴት ሊያጋልጡ ይችላሉ?

ከዚህ በላይ ከቀረቡት ውጭ ሌሎች ርዕስ ጉዳዮች ለውይይት ማቅረብ ይቻላል፡፡ ከዚህም በላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች በአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት አዳብሮ መጠቀም ሌላ ስልት ነው፡፡ ለማንኛውም ግን የተማሪዎች ውይይትና ዘገባ ከተጠናቀቀ በኋላ የተጠቆሙ መርጃ መሣሪያዎችን በመጠቀም የንዑስ ርዕሱን ትምህርት ማጠቃለል ያስፈልጋል፡፡

**ሠ. ግምገማና ክትትል**

*1. ግምገማ*

የተማሪዎች ግምገማ ተከታታይ መሆን እንደሚገባ ይታወቃል፡፡ የዚህ ዓይነቱ ግምገማ የተለያዩ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ ይፈፀማል፡፡ ነገር ግን በመማር ማስተማር ሂደት ብዙውን ጊዜ የቃል ጥያቄዎችን በማንሳት ተማሪዎች የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደጨበጡ የመፈተሽ ግምገማ ይከናወናል፡፡ አሁንም የዚህ ዓይነት ግምገማ ለማካሄድ የሚከተሉ ዓይነት ጥያቄዎችን መጠቀም ይቻላል፡፡

- ከጋብቻ ሥርዓት ጋር የተያያዙ ጉዷ ልማዳዊ ድርጊቶች የትኞቹ ናቸው?
- ከሕፃናት አስተዳደግና እንክብካቤ ጋር የተቆራኙ ጉዷ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለይቶ የሚነግረኝ አለ?
- የሴት ልጅ ግርዛት እንዴት በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ቫይረስ ለመያዝ ሊያበቃ ይችላል?
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ከሰዎች ወደ ሰዎች በምን ዓይነት መንገድ ሊተላለፍ ይችላል?
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምን ዓይነት ኢኮኖሚያዊ ጫና ያስከትላል?
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሚያስከትለውን ማኅበራዊ ጫና ግለፁ፡፡

## *2. ክትትል*

ተማሪዎች ቀጥሎ ከቀረቡ ርዕሰ ጉዳዮች መካከል በአንዱ ላይ አጭር የፅሑፍ ዘገባ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

- በክልላችን በስፋት የሚፈፀሙ ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፡፡
- ቀጥሎ የቀረቡ ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በግለሰቦች ላይ እንዴት ይከናወናሉ፣ ምን ጉዳት ያስከትላሉ?
  - እንጥል ማስቀረጥ ወይም ማስቧጠጥ፡፡
  - ገላን መተልተል ወይም ንቅሳት፡፡
  - ግግ(ወተቴ ጥርስ) ማስነቀል፡፡

## 4.2. ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገትና አሉታዊ ተጽእኖዎቹ

***የተመደበው ክፍለ ጊዜ:- 4***

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

*ተማሪዎች የንዑስ ርዕሱን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፣*

- የኢትዮጵያ የሕዝብ ቁጥር እድገት ለእርሻ መሬትና ለማህበራዊ ግልጋሎቶች እጥረት እንዴት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ይገልፃሉ፡፡

**ለ. ይዘቶች**

- የማህበራዊ ግልጋሎቶች እጥረት
- የእርሻ መሬት እጥረት

**ሐ. የትምህርቱ ጭብጥ**

ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት የአፍሪካ ቀንድ ሕዝቦችን እየተፈታተኑ ካሉ ችግሮች አንዱ ነው፡፡ የክልሉ አገሮች ይህን ችግር መቋቋም እየተሳናቸው ይገኛል፡፡ ምክንያቱም ኢኮኖሚያቸው ከሕዝባቸው ቁጥር መጨመር ፍጥነት ጋር በተጣጣመ መልኩ ለማደግ ባለመቻሉ ነው፡፡ በዚህ የተነሳ ለሕዝቦቻቸው በቂ ማህበራዊ ግልጋሎቶች ሊያቀርቡ አልቻሉም፡፡ ስለዚህ

በክልሉ የማህበራዊ ግልጋሎቶች እጥረት በስፋት ይታያል፡፡ ከዚህም በላይ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት በአፍሪካ ቀንድ የእርሻ መሬቶችን እጥረት እያስከተለ ይገኛል፡፡

## መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴ

### *1. የተጠቀሙ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች*

- የማህበራዊ ግልጋሎት ተቋማትን የሚያሳዩ ፎቶግራፎችና ምስሎች፡፡
- የተመጣጠነና ያልተመጣጠነ ቁጥር ያላቸው ቤተሰቦችን የሚያሳዩ ፎቶግራፎች፡፡

### *2. የተጠቀሙ የማስተማር ሥነ ዘዴዎች*

- የቡድን ውይይት
- ጥያቄና መልስ
- የጽሑፍ ዘገባ ማቅረብ

### *3. ቅድመ ዝግጅት*

- የሚነበብ ርዕስ በቤት ሥራ መልክ ለተማሪዎች መስጠት፡፡
- ተማሪዎች በንዑስ ርዕሱ ለተጠቀሙ ቁልፍ ቃላት ትርጉም እንዲያፈላልጉ ማድረግ፡፡
- ዕለታዊ የትምህርት ዕቅዶችን ለማጣቀሻነት ዝግጁ ማድረግ፡፡

## ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት

***መግቢያ***

ለዚህ ንዑስ ርዕስ የተመደበው ክፍለ ጊዜ 4(አራት) ነው፡፡ ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት የንዑስ ርዕሱን ትምህርት ማቅረብ አስፈላጊ ነው፡፡ በትምህርቱ አቀራረብ ላይ ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፎቻቸው የተጠቀሙ ተግባራዊ ክንውኖችን ሰርተው ማጠናቀቃቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል የመማር ማስተማር ሂደት ከዚህ በታች በተጠቀመው መልኩ ሊከናወን ይችላል፡፡

የመማር ማስተማር ሂደትን ለማከናወን ሁለት ዓይነት ተግባራት እንደ መግቢያ ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡ ይኸውም ያለፈውን ትምህርት ርዕስ በአጭሩ በማንሳት ወይም የዕለቱን ትምህርት አብይ ጭብጦችንና ዓላማዎቹን በማስተዋወቅ ይሆናል፡፡ ለዚህ ደግሞ ከዚህ ቀደም የተማራችሁት ርዕስ ስለምን ጉዳይ ነው? በማለት ተማሪዎችን መጠየቅ ይቻላል፡፡ ወይንም ደግሞ በዕለቱ የትምህርት ርዕስ ላይ ምን ያህል ዕውቀት እንዳላቸው ለመፈተሽ የሚከተሉ ዓይነት ጥያቄዎች ማንሳት ጠቃሚ ነው፡፡

- ማህበራዊ ግልጋሎት ምንድን ነው?
- በመኖሪያ አካባቢያችሁ ምን ዓይነት ማኅበራዊ ግልጋሎት ሰጭ ተቋማት አሉ?

## 2. የትምህርቱ አቀራረብ

- ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፋቸው በትምህርት ቤታቸው ማኅበረሰብ ዕድገት ላይ መረጃ እንዲያሰባስቡ ተጠይቀዋል፡፡ ይህን መረጃ ካሰባሰቡ በኋላ የትምህርት ቤታቸው ማኅበረሰብ ቁጥር በተከታታይ እየጨመረ መሄድ ምን ዓይነት ጫናዎችን በትምህርት ቤቱ ላይ እንዳስከተለ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡
- በአካባቢያቸው የማህበራዊ ግልጋሎት ያለመኖር ስለሚያስ-ከትላቸው ችግሮች ከቤተሰቦቻቸው ጋር ያካሄዱትን ቃለ ምልልስ ለክፍሉ በዘገባ መልክ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡
- ለንዑስ ርዕሱ ትምህርት የተጠቆሙ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በመጠቀም ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት እንዴት የማኅበራዊ ግልጋሎትና የእርሻ መሬቶች ላይ እጥረት እንደሚያስከትል ገለፃ ያድርጉ፡፡

ሯ. ግምገማና ክትትል

*1. ግምገማ*

የሚከተሉ ዓይነት ጥያቄዎችን ለተማሪዎች ማቅረብ ይቻላል፡፡

- *ምጣኔ ሕዝብ ምንድን ነው?*
- *ማኅበራዊ ግልጋሎት ምንድን ነው?*
- *ዋና ዋና ማኅበራዊ ግልጋሎቶችን ለይታችሁ ተናገሩ፡፡*

*2. ክትትል*

ተማሪዎች ቀጥሎ ከቀረቡ ርዕሰ ጉዳዮች መካከል በአንዱ ላይ አጭር የጽሑፍ ዘገባ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

- የሕዝብ ቁጥር እድገት የማኅበራዊ ግልጋሎቶችና የእርሻ መሬቶች እጥረት መንስኤ ስለ መሆኑ፡፡
- በ1976 ዓ.ም እና በ2000 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ምን ያህል እንደነበረ በማስረዳት በ2000 ዓ.ም የነበረው በ1976 ዓ.ም ከነበረው በምን ያህል እንደሚበልጥ አብራሩ፡፡

## 4.3. መልካም አስተዳደር፣ የሕፃናት መብትና ደኅንነት

***የተመደበው ክፍለ ጊዜ 8***

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

**ተማሪዎች የንዑስ ርዕሱን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኂላ**

- የትምህርት ቤታቸውን ሕግጋት ደንቦችንና አላማዎች ይገልፃሉ፡፡
- የመልካም አስተዳደር መገለጫዎችን ያብራራሉ፡፡
- የግልፀኝነት፣ተጠያቂነት፣የሀላፊነትና ከሙስና የፀዳ አሰራር ትርጉም ይገልፃሉ፡፡
- የተባባሩት መንግስታት የትምህርት፣የሳይንስና የባሕል ድርጅት ለሕፃናት መብት ጥበቃ እንደሚያደርግ ያስረዳሉ፡፡

- መሰረታዊ መብቶቻቸውን ለይተው በማወቅ ያብራራሉ፡፡
- በአካባቢያቸው ሊከሰቱ የሚችሉ ከባድ አደጋዎችን ይለያሉ፡፡
- የጥንቃቄ ደንቦችን ጽፈው ያብራራሉ፡፡
- በአካባቢያቸው የሚገኙ ሰዎች እራሳቸውን እንዴት ከአደጋ መከላከል እንደሚችሉ የምክር አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡

**ለ. ይዘቶች**

- የመልካም አስተዳደር መገለጫዎች (ተጠያቂነት፣ ግልፀኝነት፣ የሀላፊነት ስሜት፣ ሕግን ማክበር፣ ከሙስና የፀዳ አሰራር)
- የህፃናት መብት(የማንነትና የመጠሪያ ስም መያዝ፣ የመማር መብት፣ ከአደጋ በሕግ የመጠበቅ መብት)

ድንገተኛ አደጋና ደህንነት

- የእሳት አደጋ
- የጎርፍና የውኃ ሙላት አደጋ
- የእንሰሳት ትንኮሳ

**ሐ. የትምህርቱ ጭብጥ**

የዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በሁለት የተለያዩ ጭብጦች ላይ ያተኩራል፡፡ አንደኛው ጭብጥ ስለ መልካም አስተዳደር ነው፡፡ መልካም አስተዳደር ተቋማዊና መንግሥታዊ ተግባራት በምን ዓይነት መልኩ እንደሚከናወኑና ተፈፃሚ እንደሚሆኑ የሚገልፅ ጽንሠ ሀሳብ ነው፡፡ ለዜጎች አገልግሎት እንዴት እንደሚሰጥና በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ምን ዓይነት አያያዝ እንደምደረግላቸው ያመለክታል፡፡ መልካም አስተዳደር አራት መሠረታዊ ገጽታዎች አሉት፡፡ እነርሱም ተጠያቂነት፣ ግልፅነት፣ የሕግ የበላይነትና ከሙስና የፀዳ አሠራር ናቸው፡፡ ሁለተኛው ጭብጥ የሕፃናት መብቶችና ደህንነት የሚል ርዕስ አለው፡፡ ሕፃናት በአገራቸው መንግስትና እንደ የተባበሩ መንግሥታት ድርጅት፣ ዩኔስኮና ዮኒሴፍ በመሳሰሉ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጥበቃ የሚደረግላቸው በውል ተለይተው የሚታወቁ መሠረታዊ

መብቶች አሏቸው፡፡ ከዚሁ ጐን ለጐን ሕፃናት በአካባቢያቸው ለአደጋ አጋላጭ ከሆኑ ነገሮች እንዴት መቆጠብ እንዳለባቸውና በአደጋ ጊዜም ከአደጋው ለመራቅ ጥንቃቄ፣ በቂ ግንዛቤና ክሕሎት እንዲጨብጡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ**

*1. የተጠቆሙ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች*

- የ1987 የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ሰነድ፣
- ያጋጠሙ አስከፊ አደጋዎችን የሚያሳዩ ፎቶግራፎችና ምስሎች፡፡

*2. የተጠቆሙ የማስተማር ሥነ ዘዴዎች*

- የቡድን ውይይት
- ጥያቄና መልስ
- የጽሑፍ ዘገባ ማቅረብ

*3. ቅድመ ዝግጅት*

- በንዑስ ርዕሱ ትምህርት ለተጠቆሙ ቁልፍ ቃላት ተማሪዎች ትርጉማቸውን አፈላልገው በማምጣት ለክፍላቸው እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡
- በመማሪያ መጽሐፍ ስለ ትምህርት ቤት ደንብ የተሰጠውን ተግባራዊ ክንውን በቤት ሥራ መልክ ለተማሪዎች መስጠት፡፡
- የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ሰነድና ሌሎች የትምህርት መርጃዎችን በክፍሉ ውስጥ በግልፅ ስፍራ ቦታ ቦታቸውን ማስያዝ፡፡
- ዕለታዊ የትምህርት ዕቅዶችን ለማጣቀሻነት ዝግጁ ማድረግ፡፡

**ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት**

*1. መግቢያ*

ለዚህ ንዑስ ርዕስ የተመደበው 8(ስምንት) ክፍለ ጊዜ ነው፡፡ በዚያው መጠን ተማሪዎች አከናውነው ለክፍል ዘገባ እንዲያቀርቡ የሚጠበቅባቸው

በርካታ ተግባራዊ ክንውኖች አሉ። ስለዚህ የተመደበውን ክፍለ ጊዜ አብቃቅቶ መጠቀም ያስፈልጋል። የርዕሱን ትምህርት ቀጥሎ በቀረበው ጥቆማ መሠረት ማቅረብ ይቻላል።

ተማሪዎችን ቀጥሎ የተመለከቱ ጥያቄዎች ዓይነት ይጠይቁ።

- መልካም አስተዳደር ምንድን ነው?
- ሕግና የትምህርት ቤት ደንቦች ዓላማ ምንድን ነው?

## 2. የትምህርቱ አቀራረብ

- ተማሪዎችን በቡድን አከፋፍለው የትምህርት ቤታቸውን ርዕሰ መምህር፣ ፈረቃ አስተባባሪና የክፍል ኃላፊ መምህራን ኃላፊነታቸውንና በሚፈጽሟቸው ተግባራት ላይ ተወያይተው ለክፍሉ ዘገባ እንዲያቀርቡ ያድርጉ።
- በትምህርት ቤታቸው የተማሪዎች መብትና ግዴታ በሚገልፅ ደንብ ላይ ተወያይተው መብቶቻቸውንና ግዴታዎቻቸውን ለይተው እንዲዘረዝሩና እንዲያብራሩ ያድርጉ።
- በተማሪዎች ውይይት ላይ በመመሥረት ስለ መልካም አስተዳደር ምንነት ማስረዳትና መሠረታዊ ገጽታዎቹንም መግለፅ ያስፈልጋል።
- ተማሪዎች በሚከተሉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ተወያይተው ለክፍላቸው እንዲዘግቡ ያድርጉ።
  - መሠረታዊ የሕፃናት መብቶች።
  - የሕፃናት መብቶች ጥበቃ ተግባራት የሚያከናውኑ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች።
  - መንግሥት የሕፃናት መብቶችን ከመጠበቅ አንፃር ምን ዓይነት ተግባራት ያከናውናል?
- በውይይታቸው መሠረት የርዕሱን መሠረታዊ ጭብጦች በማጠቃለያ መልክ ማንሣት ይቻላል። ይህን ለመፈፀም የሕገ መንግሥት ሰነድን በመርጃ መሣሪያነት መጠቀም ተገቢ ነው። በአጠቃቀሙ ላይ ተማሪዎች የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ

36 ላይ ስለ ተደነገጉ የሕፃናት መብቶች እንዲያውቁ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

- ለንዑስ ርዕሱ ከተመደበው ክፍለ ጊዜ በአንዱ ተማሪዎች በሚከተሉ ጉዳዮች ላይ እንዲከራከሩ ያድርጉ፡፡
  1. አደጋ ሊያጋጥም የሚችለው ከመኖሪያ አካባቢ ውጭ ብቻ ነው፡፡
  2. አደጋ ከሰዎች ቁጥጥር ውጭ አይደለም፤ እንዳይደርስም መከላከል ይቻላል፡፡
- ተማሪዎች በተሽከርካሪ ጐዳናዎች ላይ ጉዞ በሚያደርጉበት ወቅት መከተል ስላለባቸው መሠረታዊ የትራፊክ ደንቦች እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፡፡
- ተማሪዎችን በቡድን ከፋፍለው የሚከተሉ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ያድርጉ፡፡
  - በመኖሪያ አካባቢዎች፣ በትምህርት ቤት ግቢና በተሽከርካሪ ጐዳናዎች ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ አደጋዎችን ለይታችሁ ዘርዝሩ፡፡
  - በዝርዝር ለተለዩ አደጋዎች መወሰድ ስላለበት የጥንቃቄ መርሆ የሚያብራራ ሠንጠረዥ አዘጋጁ፡፡

**ረ. ግምገማና ክትትል**

***1. ግምገማ***

የሚከተሉ ዓይነት ጥያቄዎች ለተማሪዎች ያቅርቡ፣

- መልካም አስተዳደር ምን ማለት ነው?
- የመልካም አስተዳደር መሠረታዊ መገለጫዎች ምንድን ናቸው?
- ከመሠረታዊ የሕፃናት መብቶች መካከል ጥቂቶቹን ተናገሩ፡፡
- በመኖሪያ አካባቢዎች ለእሳት አደጋ መንስኤ የሚሆኑ ነገሮች ምንድን ናቸው?

## *2. ክትትል*

ይህ ንዑስ ክፍለ ትምህርት በርካታ ክንውኖች አሉት። ተማሪዎች የተጠቀሙ ክንውኖችን በሙሉ ማጠናቀቃቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ይሆናል። ተማሪዎችን ለመገምገም ክንውኖችንና በመማር ማስተማር ሂደት በተደረጉ ውይይቶች ላይ የነበራቸውን ተሳትፎ መሠረት ማድረግ ያሻል። በመጨረሻ ተማሪዎች ቀጥሎ በቀረቡ የአደጋ መንስኤዎችና መወሰድ ስለሚገባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች ላይ አጭር የጽሑፍ ዘገባ እንዲያቀርቡ ያድርጉ።

- የተሽከርካሪ አደጋ
- የእሳት አደጋ
- ጐርፍና የውኃ ሙላት አደጋ
- የእንስሳት ትንኮሳ

### የምዕራፍ አራት ክለሣ ጥያቄዎች መልስ

**ሀ) የእውነት/ሐሰት ጥያቄዎች**

1. ሐሰት
2. እውነት
3. ሐሰት
4. ሐሰት
5. ሐሰት

**ለ) የአዛምድ ጥያቄዎች**

1. መ 2. ረ 3. ሀ 4. ለ 5. ሐ

**ሐ) የምርጫ ጥያቄዎች**

1. ሀ 2. ሐ 3. ሀ 4. ለ 5. መ

**መ) የአጫጭር ምላሽ ጥያቄዎች**

1. ቫይረሱ በደማቸው የሚገኙ ሰዎች ጋር መጨባበጥ፣ አብሮ መቀመጥ ወይም የምግብ ዕቃዎች አብሮ መጠቀምና ሽንት ቤትን በጋራ መጠቀም።

2. ልቅ የሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት፣ ያልተመረመረ ደም መስጠት ወይም መቀበል፣ ከእናት ወደ ሕፃን በማሕፀንና በማጥባት መተላላፍና ስለታም ነገሮችን በጋራ መጠቀም፡፡
3. ከተወለዱ ጀምሮ ስምና ዜግነት ማግኘት፣ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት በነፃ ማግኘት፣ ከጭካኔያዊ ተግባራት መጠበቅና ከአካላዊ ቅጣት ነፃ መሆን፣ ያለዕድሜ ለሥራ ያለመቀጠር፡፡
4. ተጠያቂነት፣ ግልፅነት፣ የሕግ የበላይነትና ከሙስና የፀዳ አሠራር፡፡
5. መንግሥት ለዜጎቹ በሞላ በጋራ የሚያቀርባቸው እንደ ጤና እና የትምህርት አገልግሎት ናቸው፡፡
6. በሀገሪቱ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ ጉልህ ድርሻ ያላቸውን አምራችና የሰለጠኑ ሰዎችን ገዳይ ከመሆኑም ባሻገር ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝ ዜጎች እጅግ ውድ የሆኑ መድሃኒቶችን በውጭ ምንዛሪ ገዝቶ ማቅረብ የአገራትን ኢኮኖሚ ይጎዳል፡፡
7. የሕዝብ ቁጥር መጨመር የደን መመንጠርን ያስከትላል፡፡ ይህ ደግሞ ለመሬት መሸርሸርና ለድርቅ ይዳርጋል፡፡
8. የማኅበራዊ ግልጋሎት ተቋማትና፣ የሠለጠነ የሰው ኃይልና፣ ቁሳቁስ እጅግ ውድ በመሆኑ ሀገራት በፈጣን ሁኔታ ቁጥሩ ለሚያድገው ሕዝባቸው ለማቅረብ አቅም አይኖራቸውም፡፡

# ዋቢ መጻሕፍት


- Bahru Zewde, **A History of Modern Ethiopia. 1855-1991**, Second Edition (Addis Ababa: Addis Ababa University Press, 2002).
- _________ (ed.), "Ethiopia and the Horn II", Department of History, Addis Ababa University.
- _________, **Pioneers of Change in Ethiopia, the Reformist Intellectuals of the Early Twentieth Century** (Addis Ababa: Addis Ababa University Press, 2002).
- Richard Pankhurst, **The Ethiopians** (Oxford: Blackwell Publishers, 1998).
- Adam Arnel and Andy Brown, **The Ultimate Study Guide,** Revised K53 Geography.
- H. Bobins, **Geography for Business Studies**, Third Edition, 1979,
- W. Moore, **The Penguin Dictionary of Geography**.
- የትራንስፓርትና መገናኛ ሚኒስቴር፣ ***የመንገድ ሥነ ሥርዓትና የማሽከርከር ስልት መመሪያ*** (አዲስ አበባ፤ አፍሪካ ማተሚያ ቤት 1995)።
- የማስታወቂያ ሚኒስቴር፣ ***የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ትግልና አብዮታዊ ዴሞክራሲ*** (አዲስ አበባ፤ ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር፣ 1999)።
- Robert J.Lowenherz, **Population** (Mankato: Creative Education Press, 1970).
- Roy O.Billet and J.Wendell Yeo, **Growing Up** (Boston: D.C. Heath and Company, 1958).
- Sir Kenneth Blaxtre, **People, Food and Resources** (Cambridge: Cambridge University Press, 1986).
- The 1995 Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.